

‘ክርስቲያናዊ’

ኢትዮጵያኝነት

ከዘላለም መንግሥቱ



ማውጫ

መንደርደሪያ 3

ቅንጫቢ 5

ኢትዮጵኝነት 7

- ኢትዮጵኝነትና ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት
- መነሻ፤ "እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ምን ተናገረዎት?"
- አገር መውደድና ለቃሉና በቃሉ መቆም
- ዶሚኒየን ቲዮሎጂ
- ኢትዮጵኛ ዝማሬዎች

ኢትዮጵኛ ትንቢቶች 23

- "እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ምን ተናገረዎት?"

ኢትዮጵያና ኢትዮጵኝነት በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ 59

- ብዙ ጥቅስ?
- ዐውድ የሚሉት ነገር
- ያኔ እዚያና ያ
- ለቅሞ የመጣል ጣጣ

ኢትዮጵያ ወይስ ዩቶፒያ 71

- ኢትዮጵያ ወይስ ዩቶፒያ
- ተርታሪ፥ ጠርጣሪ፥ በርባሪ

መግቢያ

ዕዝራ ቁጥር 31 ከተሰራጨ በኋላ ለዕዝራ ቁ. 32 ከሚሆኑት መጣጥፎች ከተከታታዮቹ ተጨማሪ የሚሆነው ስለ ኢትዮጵኝነት እንዲሆን በማሰብ ልጽፍ ጀመርኩ። ከ6 ወይ 7 ገጾች እንዳይበልጥ ያሰብኩት ይህ ጽሑፍ ያሰብሁለትን የገጽ መጠን ሲያልፍ በማቆም ፈንታ እንዲሄድ ተውኩት። እናም ይህን ትንሽ መጽሐፊት ሆነ።

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝን የቪድዮ ዝግጅት በዩቲዩብ ከተሳፈረ 3 ዓመታት፥ እኔ ካየሁት ደግሞ አያሌ ወራት አልፈውታል። አጭር ምላሽ ለመስጠት ባስብም በዚህ ርእስ ላይ ከቪድዮው መውጣት በፊት ከጻፍኩት አንድ አጭር መጣጥፍ ያለፈ አልሠራሁም። ይህን ጽሑፍ ከጨረስኩ በኋላ ልማዴ እንደሆነው ለንባብና ለእይታ ለቪድዮው አዘጋጆች ልኬ ነበር። ከአገልግሎቱ ድረ ገጽ ያገኘሁት የኢሜይል አድራሻ ግን የማይሠራ ስለሆነ ልሰድደው አልቻልኩም።

ሕጻናት በሕፃንነት መልካቸው የዋኖች፥ ንጹሐን፥ ማራኪዎች፥ ውቦች፥ ለስላሳዎች ናቸው። ለምሳሌ፥ እነዚህን ጨቅላዎች ተመልከቷቸው፤







እነማን መሆናቸውን በመጨረሻው ገጽ ተመልከቱ። ኢትዮጵኝነትም በጨቅላነት ዕድሜው ነው ባይባልም የሕፃን በሚመስል መልኩና ገጽታው ነው አሁን የሚታየው። ግን ይህ መልክ አሳሳች ነው። ይህንን አሳብ ነው እዚህ ለማካፈል የምሞክረው።

የዚህ ጽሑፍ ግብ በኢትዮጵኛ ትምህርቶች ላይ እስካሁን በተሰጡ በጣም ጥቂት መመከቻዎች ላይ እንዲጨመርና ሰዎች የኢትዮጵኝነትንና 'ክርስቲያናዊ' ኢትዮጵኝነትን እውነተኛ መልክና አደጋውን እንዲያውቁት ነው። "Those who have the previlege to know have the duty to Act." Albert Einstein. አይንስታይን ይህን ያለው ከቃሉ አንበቦ ሳይሆን አይቀርም። . . . አንድ ነገር አይቶ እንደ ሆነ ወይም አውቆ እንደ ሆነ ባይናገር፥ ኃጢአት መሥራቱ ነውና በደሉን ይሸከማል። ዘሌ. 5፥1።

እግዚአብሔር ከአርያም ይባርካችሁ።

ዘላለም መንግሥቱ። ኅዳር ፳፻፰ (November 2015) ezralit@gmail.com

መንደርደሪያ

ማንም ሰው አገሩንና ሕዝቡን መውደድ ተገቢው ነውን? ይህ ጥያቄ ጥያቄ ብቻ እንጂ አጠያያቂ አይመስለኝም። ለአንድ ዜጋ ይህ ተገቢው ነው። የአገሩን ጥቃት መጥላትና መከላከል፥ ልማቷን መውደድ እንዲሁም የአገሩን ሕዝብ ምኞት መፈለግ ተገቢው ነው? ተገቢውና ልኩ ነው። ተነጻጻሪ ጥያቄ ልጠይቅ፤ ማንም ሰው አገሩ ከማንም ሌላ አገር በላይ እንደሆነች፥ ሕዝቡንም ከዓለም ሕዝብ ሁሉ ይልቅ ልዩ እንደሆነ ሊያምን ይገባዋል? ይህ ስሕተት ነው፤ አይገባውም። ይህንን 'አይገባውም' የምለውን መልስ ከሁለት አቅጣጫ ላሳይ፤

<u>አንደኛ፥</u> እንኳን ባለንበት ሉላዊ መንደርተኝነት ዘመን ቀርቶ ሉላችን መንደር ባልሆነችበት ዘመንም ይህ ከልክ ያበጠ ስሜት ኩራትን፥ ዕብሪትን፥ ዘረኝነትን፥ ወራሪነትንና ጨቋኝነትን፥ ቅኝ አገዛዝንና እጅ አዙር ቅኝ ገዢነትን ወልዶ ያውቃል። ሩቅ ሳንሄድ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ቀስቃሽ የሆነውን የጀርመን ናዚ መንግሥት ወይም የአርያን የበላይነትን መውሰድ እንችላለን። ሂትለር ጀርመንን ከነበረችበት እረንቋ ለማውጣት በፊጠረው በዚህ ፍልስፍና የተለከፈና ያበደ ሰው ነበረ። የአውሮጳ ቅኝ ገዥዎች አፍሪቃንና ደሴት አገሮችን ሲወስዱ በስግብግብነት ላይ የበላይነት ጥንዋቴ ይዟቸው ነው። የጦርነትና ጠብ አጫሪነት ምንጭ ሁሌም የበላይነት ስሜት ባይሆንም ትልቅነኝነት ጉልሁ አቀጣጣይ ነው። አንዳንዶቹ ትልቅነኞች ይህንን 'ትልቅነት' እንደ ቅዱስ ኃላፊነት አድርገውም ያዩታል።[1]

<u>ሁለተኛው፤</u> ሰው ሁሉ ሲፈጠር ምንጩ፥ ሲወድቅም ውድቀቱ አንድ ላይ መሆኑ ማንም ራሱን ከማንም የተለየ የበላይ አድርጎ ከቶም እንዳያስብ ያስገድደዋል።[2]

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ አገር (አገር ከማለት ይልቅ ሕዝብ ማለቱ ይመረጣል) አንድ ሕዝብ ልዩ ሆኖ ያውቃል? አዎን ያውቃል። ይህ የሆነው እግዚአብሔር ይህችን የወደቀች ዓለም በዚያ ሕዝብ አማካይነት ለመታደግ ያንን ሕዝብ መንገድ ወይም መሳሪያ አድርጎ ሊገለገል ስለፈለገና በዚያ ሕዝብ ሌላውን ሁሉ ሊመልስ ስለወደደ ነው። እንዲያም ሆኖ ያ መንገድ ጊዜያዊ ብቻ ነበር። ደግሞም፥ ያ ሕዝብ የራሱ የሆነ ውስጣዊ የማንነት የበላይነት ትምክህት እንዳይኖረው፥ የተመረጠው ሕዝቡ አልነበረም። የተመረጠው አንድ ሰው ነበረ፤ ሕዝቡ የዚያ ሰው ዘር ነው። ሕዝቡ የሚያስመርጥ ብቃት ያለው ሕዝብ አልነበረም። ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን የተመረጠው የሕዝቡ አባትም አኩሪ ውስጣዊ ብቃት ያለው ሰው አልነበረም። ትምክህትን እንደገና ለመስበር ሕዝቡ ሕዝብ ሆኖ የተሠራው ደግሞ በውርደትና በባርነት ውስጥ ነበር። ያ ሕዝብ የእግዚአብሔር ወዳጅና የእምነት ምሳሌ የተባለው የአብርሃም ዘር የሆነው (በይስሐቅና በያዕቆብ በኩል) እስራኤል ነው።

[1] ይህ የትልቅነኝነት ጥንዋቴ Rudyard Kipling "The White Man's Burden" ብሎ ርእስ በሰጠው ግጥሙ ይታያል። ይህ የ1899 ግጥም በቀጥታ የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም ቢመለከትም ስሜቱ በግልጽ በጥቅሉ ነጮች ኋላ ቀር ጥቁሮችን የማሰልጠን 'ሸክም' እንዳለባቸው ይዘክራል።

[2] ይህንን የምለው እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስቲያን ነው። በፈጣሪ የማያምኑ ዝንጀሮ-ወለዶችም ቢሆኑ የመትረፈ ምርጦች (survival of the fittest) አዙሪት ጥሎአቸው ትልቁ ትንሹን ውጦ ለመወፈር ካልወደዱና ራሳቸውን ካላሳመኑ በቀር ምንጫቸው አንድ መሆኑን አይክዱም።

እስራኤላውያን ሌላውን ሕዝብ የመድረስና የሞዴልነት ኃላፊነት መወጣት ቀርቶ ራሳቸውም በዙሪያቸው ያሉትን አሕዛብ ሁሉ በመምሰላቸው ይህ ዓለምን የማዳን ወይም አርዓያ ሆኖ እግዚአብሔርን የማሳየት ተልእኮ ከሰመ። ራሳቸውም ለአብርሃም በተስፋ ከተሰጠው ምድር ተተፍተው ወደ አሦርና ባቢሎን ተማርከው ተጋዙ። ኋላም በሮማውያን ብታኔያቸው ተፈጸመ። ቀድሞም የመዳን መንገድ በእምነት ቢሆንም ኋላ መዳን በነጠላና በእምነት ሆነ። አምላክ ሥጋ ለብሶ ሰው ሆኖ የሰውን ኃጢአት በመስቀል ላይ ተሸክሞ ምትካዊ ሞትን ሞተ። እርሱም ክርስቶስ ነው። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትንና የእግዚአብሔርን ልጅነት ይቀዳጃል። መዳንና መባረክ እንደ ሕዝብ ሳይሆን በግል ሆነ።

ዛሬ እስራኤል ያቺ ሞዴል አይደለችም። ዛሬ ሞዴል አገር ወይም የአንድ ክልል ናሙና ሕዝብ የለም። በሮሜ 9-11 እንደምናየው የዚህ ሕዝብ፥ የእስራኤል፥ መጎብኘት ወደፊት እንደሚሆን ይጠበቃል። ሲሆንም፥ ይህ የሚፈጸመው ዛሬ እኛ ሁላችን በዳንንበት በክርስቶስ አማካይነት በሚሆነው የመዳን ጉብኝት ብቻ ነው። ትምክህት የለም። የግልም የብሔርም ትምክህት የለም። የአይሁድና የአሕዛብ ወገን የሚባል ሁለት ሕዝብም የለም። የጥልን ግድግዳ አፍርሶ ሁለቱን አካላት አንድ አድርጎ ያዋሃደው የክርስቶስ መስቀል ነው፤ ኤፌ. 2፥13-16።

እግዚአብሔር ዛሬ የአንድ አገር ወይም የአንድ ምድራዊ ዘር ሕዝብ የለውም። ይሁን እንጂ ሕዝብ ወይም ወገን የለውም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ዛሬ አንድ ሕዝብ አለው፤ አንድ ብቻ ሕዝብ አለው። ያም በ1ጴጥ. 2፥9 *እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤* ተብሎ የተጻፈልት ሕዝብና ወገን ነው። ይህ ሕዝብ ማን ስለመሆኑ በጴጥሮስ መግቢያ ስንመለከት፥ ይህ ሕዝብ በክርስቶስ ደም ይረጭ ዘንድ የተመረጠ በየአገሩ የተበተነ መጻተኛ ሕዝብ ነው፤ 1ጴጥ. 1፥1-2። በሌላ አገላለጽ ይህ ሕዝብ በክርስቶስ ደም የተዋጀችው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ናት።

ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ግልጽ ነው። ይህ ሆኖ ሳለ ግን ዛሬ በጥቂት ኢትዮጵያውያን አማካይነት አንድ አጉል መወድስ በአጉሊ መነጽር እንዲታይ ተደርጎ እየናኘ ይገኛል። ያም፥ ኢትዮጵያ ልክ በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤል እንደነበረችው ያለች ብርቅ አገር መሆኗ፥ ከዚያም የበለጠችና እርሷን የተካች መሆኗ፥ ሕዝቧም ለዘር የሚፈለግ ምርጥ ዘር መሆኑ፥ የዘመናት ፍጻሜ ሥራውን የሚያከናውንበት ተጫራች የሌለው ብቸኛ ሕዝብ መሆኑ ነው።

ይህ ሲደረግ ግን ምንጩ ቃሉ ነው ወይስ ሰዎች? ብለን ስንጠይቅ መልሱ ምንጩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልሆነ ሕዝባዊ ትንቢት ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን ዘለቅ ስንል በስፋት እናየዋለን። የጽሑፌ ዋና አሳብ በዚህ ሙግሳ-ኢትዮጵያና ኢጋኖ-ኢትዮጵያ ላይ ሆኖ የጽሑፍ እይታዬ ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አንጻር ነው። አንድን ዘር፥ ጎሳ፥ ሕዝብ ወይም አገር፥ ለይቶ መለጠጥ ስሕተት ብቻ ሳይሆን ቅሌትን በጀርባው ያዘለ ስሕተት ነው። ይህን ስሕተት ጥፋትም ይከተለዋል።

ለአንድ ክርስቲያን ኢትዮጵያን መውደድና ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት መቆም ለውድድርና ለውርርድ መቆም የለባቸውም። ይህ በጣም ግልጽ ነው። አገራዊ ስሜት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ጋር ለመቆም ብቃትና አቅም የለውም። ይህ የሁለቱ ነገሮች ለውርርድ የመቆም ጥያቄ

ለአንዳንዶች እንደ ውኃና ዘይት የማይደባለቁና የማይቀያየጡ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ለጥቂቶች ደግሞ እንደ ውኃና ወተት የተደባለቁ ሊሆኑ ይችላሉ። አገራዊ ስሜትንና ሕዝባዊ ትንቢቶችን ከቃሉ እኩል ለሚያዩ ሰዎች ይህ ጽሑፍ ሊያስቆጣ ይችል ይሆናል። ለማስቆጣት ስል አልጽፍም፤ ስለሚያስቆጣ ደግሞ ከመጻፍ አላፈገፍግም። ላለማስቆጣት ሲባል ዝም ማለት እውነትን የማቀጨጭ ብቻ ሳይሆን፥ ስሕተትን የማፋፋትም ድርብ ጥፋት ነው።

ብዙ ስሕተቶች ገና ከጅምራቸው ቢቀጩ ኖሮ ዓለማችን ከብዙ ጉዳቶች በዳነች ነበር። አንዳንድ ስሕተቶች በመጀመሪያ ስሕተት ካለመምሰላቸው የተነሣ በየዋኅነት ታለፉ። አንዳንዶች ደግሞ ከግድ የለሽነት፥ ከፍርሃትና ከይሉኝታ የተነሣ ፋፉ። ሌሎች ከጥቅማ ጥቅሞች የተነሣ በዝምታ ገዘፉ።

ኢትዮጵኝነት (ትርጉሙን በቀጣይ ገጾች አብራራለሁ) አሁን የቆየ ስሕተት ነው። ሰዎችን በትንበያ ሳይሆን በቃሉ ለማስታጠቅ ግን ጊዜው አላለፈም። ከዚህ መነሻና መንደርደሪያ ነው ይህን የማካፍለው።

ቅንጫቢ

ወደ ሙግቴ ከመግባቴ አስቀድሞ ከላይ ያልኩትን ኢጋኖ-ኢትዮጵያ የሚያንጸባርቁ ወደ 30 በሚያህሉ የአብያተ ክርስቲያናት እና የክርስቲያን አገልግሎቶች መሪዎች ተነግረው ከተቀነባበሩበት የቪድዮ ዝግጅት ውስጥ የተወሰዱ ትንበያዎችን እንይ። ትንበያዎቹ ኢትዮጵያ በቀጣዮቹ ጥቂት ዓመታት ምን እንደምትመስል የሚናገሩ ናቸው።

- ኢትዮጵያን አገራችን ኃያላን ከሚባሉት አገሮች መካከል አንዷ፥ እንዲያውም ዋናዋ ትሆናለች፤ ኢትዮጵያ በመንፈሳዊም፥ በምድራዊም፥ ሁለንተናዊ በረከትና በነገር ሁሉ ወደላይ ትነሣለች። . . . በ30 ዓመት ኢትዮጵያ የአሁኗን ጃፓን ትደርሳለች። . . . የፖለቲካው ሥርዓት የተረጋጋ ይሆናል፤ ሶሻል እስትራክቸሩ ውብ ይሆናል፤ ልመናን እናባርረዋለን፤ ገለል እናደርገዋለን።

- ከሃብቷ ብዛት፥ ከክብሯ ብዛት፥ ይህቺ ምድር በጣም ትልቅ አገር ነው ምትሆነው፥ በጣም። ምድሪቱ ሳትታረስ ኃይሏን ስለምትሰጥ ሳይዘራ እህል ይመረታል፤ አዝመራው እጅግ ከመባረኩ የተነሣ፥ እህል ከመብዛቱ የተነሣ፥ አህያ ጥራጥሬ እስኪንቅ ድረስ ጠግቦ ምድር ተዝረክርካለች በበረከት። አንዳንድ ጊዜ፥ 'እግዚአብሔር ኢትዮጵያዊ ነው ወይ?' እላለሁ።

- ዓለም በሙሉ ኢትዮጵያን ይጠብቃል፤ የዓለም ሁሉ መፍትሔ ከኢትዮጵያ ነው፤ የእግዚአብሔር ፑልፒት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። . . . የኢትዮጵያ 90% ሕዝብ ክርስቲያን ይሆናል፤ መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን በጀት ይመድባል፤ በሽታዎች ይጠፋሉ፤ ከሊኒኮች ቤተ ክርስቲያን፥ ሆስፒታሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ይሆናሉ።

- ማመን እስከሚያቅተው ሰው ሁሉ፥ 'እውነት እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ወይ?' ይላል። ጤና የሚሰጥ አየር ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኗል በሚል ነጩም ጥቁሩም ከኢትዮጵያ ውጪ ከአራቱም ማዕዘን ወደ ኢትዮጵያ ይጎርፋል። የሚገባው የሰው ሕዝብ ብዛት ለመቁጠር ያታክታል። . . . እግዚአብሔር የሚያስነሳቸውን ሰዎች ቅባት ፍለጋ፤ ይኼን ጸጋ ፍለጋ ብዙዎች ይመጣሉ፤ ነጮች ጥቁሮች ይመጣሉ፤ በጣም ከፍተኛ ዝግጅት እግዚአብሔር ጨርሷል።

- የብዙ አገር ሰዎች፥ ነጮች ጥቁሮች ቢጫ ሕዝቦች መጥተው፥ ዜግነታቸውን ይለውጣሉ፤ ሞታቸውን እዚህ ያደርጋሉ፤ ብዙ የዓለማችን ሰዎች፥ ብዙ ትልልቅ የተባሉ ሃብታሞች፥ ብዙ ትልልቅ የተባሉ አዋቂዎች መቃብራቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ ያደርጋሉ። እዚህ ለመሞት፥ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለመሞት፥ እራሳቸውን ይለውጣሉ። . . . እጅግ ብዙ ሰዎች በምድራችሁ ከማያርገው ከፍተኛ ለውጥና በረከት የተነሣ ወደ ምድራችሁ መጥተው ለማየት ወረፋ ይዘው ይጠባበቃሉ፤ የምድራችሁም አፈር ለመድኃኒት እስኪፈልጉት ድረስ አደርጋለሁ።

- በዚህ በኔ ትውልድ ዘመን፥ የኔ ትውልድ ሳያልፍ፥ እግዚአብሔር ይህቺን ምድር በመንፈሳዊ፥ በቁሳዊ፥ በኢኮኖሚ ሁኔታ፥ በፖለቲካ፥ በሁሉ ረገድ ይጎበኛል።

- አፍሪካ ራሷ የምትጠብቀው እኛን ነው፤ አገራችን የእግዚአብሔር ብዙ የተሰፋ ቃል ያላት ምድር ናት፤ ብዙ ጊዜ ከ50 በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰች አገር ናት። . . . የኢትዮጵያ መኖርነት ለምድር ነገሥታት ወይም በአጠቃላይ ለምድር ወደ እግዚአብሔር መመለስ ምክንያት የሚሆን ትልቅ ንቅናቄ፥ . . . መጀመሪያ ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ ከዚያ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ፤ የዚህ መገዛት፥ የጠላቶች መመታት ምንጩ የኢትዮጵያ በፊቱ መስገድ ነው።

- ኢየሩሳሌምን ምሳሌ ማድረግ እንችላለን፤ መጀመሪያ ኢየሩሳሌም ለዓለም ሁሉ ለሚሄደው የትንሣኤ ምስክርነት የመነሻ ቦታ ነበረች፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ለትንሣኤው የመጠቅለያ አካል የመነሻ ቦታ እንደሆነች እግዚአብሔር በነቢያት አፍም እንደዚሁም በትንቢት መጽሐፎች ላይ አስረግጦ ተናግሮናል።

- እነዚህ የኢትዮጵያ አገልጋዮች በተነሡ ጊዜ ነው የክርስቶስ ምጽአት ሚመጣው። የኢትዮጵያ አገልጋዮች በዓለም ደረጃ፥ ዓለምን ሲሞሉ የክርስቶስ ምጽአት ይመጣል። የክርስቶስን ምጽአት የሚያቀርበው አለኝ እግዚአብሔር፥ የዚህ ምድር አገልጋዮች ናቸው።

እነዚህ ከላይ ተቆንጽለው የተወሰዱት ከታች ከምናገኘው ምንጭ የተወሰደ ነው። እየቀነጫጨቡ መውሰድ ዐውደ ወጥነት ሊሆን ስለሚችል ይህ እንዳይሆን ጠቅላላውን ክፍል ዘለቅ ስንል እናገኛለን። ከዚያ ባለፈ ደግሞ ከምንጩ መስማትና ማየት የተሻለ ነውና ያ የሚቻልበትን መንገድ አመለክታለሁ።

በዚህ ዝግጅት ሦስት ዋና ዋና ነገሮችን አካፍላለሁ። እነዚህም፥

1. ኢትዮጵኝነትና ምንነቱ፤

2. ኢትዮጵኛ ትንቢቶች፤

3. ኢትዮጵኝነትና ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ናቸው።

የመጀመሪያው ክፍል የኢትዮጵኝነት ምንነት የተብራራበት ነው። ሁለተኛው ክፍል በቪድዮው የተቀነባበሩት ወደ 30 ያህል ኢትዮጵያውያን የአብያተ ክርስቲያናትና ክርስቲያን አገልግሎት መሪዎች ትንቢያዎችና አጫጭር ምላሾቼ ናቸው። ሦስተኛው ክቃሉ አንጻር ይህንን እውነትና ኢትዮጵኝነትን ራሱን የምንፈትንበት ነው።

1. ኢትዮጵኝነት

ኢትዮጵኝነትና ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት

ከአምስት ዓመታት በፊት 'ኢትዮጵያ እጆቿን ምን?' በሚል ርዕስ ስለ ኢትዮጵኝነት አንዲት መጠነኛ መጣጥፍ ጽፌ ነበር።[3] መጀመሪያ የተጠቀምኩት ቃል ኢትዮጵና የሚለው ነበር። የማውቀውን ወካይ ቃል ስላላገኘሁ ነው ያንን ቃል የተጠቀምኩት። ኢትዮጵና ስልም ቅስና፥ ጵጵስና፥ ምንኩስና እንደሚባለው ቃል ዓይነት ነው። ኋላ ኢትዮጵኝነት የሚለውን ቃል አገኘሁ። ያገኘሁት መጣጥፉን ካነበበ በኋላ አከሊሉ ሙላቱ የተባለ ጓደኛዬ ሰንዝሮት ነው።

ኢትዮጵኛ እንደ አርበኛ፥ ወደረኛ፥ ወገኛ፥ የመሰለ አገባብ ነውና የተሻለ አጣጣል ነው። መጀመሪያ መጣጥፉ በእንግሊዝኛ ስለነበር የተጻፈው የአማርኛውን ስሥራው ኢትዮጵኛ የሚለውን ቃል ወደድኩትና ሁለቱንም እያለዋወጥሁ ጻፍሁ። እዚያ ቃላቱን በልውውጥ ብጠቀምም እዚህ ኢትዮጵኛ እና ኢትዮጵኝነት የሚለውን ነው የምጠቀመው። ሁለቱንም የአማርኛ ቃላት ከዚያ በፊት ሰምቼ ወይም አንብቤ ስለማላውቅ የኛው ፈጠራ ሊሆን ይችላል። ላይሆንም ይችላል።[4] ካልሆነ ደግሞ ቀድሞ ከተባለው የተለየ ትርጉም እንዳይኖረው በማለት እዚያ ተርጉሜው እንደ ነበር እዚህም ቃሉን በመተርጎም እጀምራለሁ።

በአጭሩ ኢትዮጵኝነት፥ Ethiopianism የሚባለው የእንግሊዝኛ ቃል አቻ ነው።[5] ቃሉ የኢትዮጵያን ልዩና ውድ የመሆን አሳብን የሚያንጸባርቅ ቃል ነው። ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ስለሆነች ብቻ ከማንም አገር የተለየች ሆና እንደምትቆጠር የሚያስቡ ሰዎች ናቸው ኢትዮጵኞች። ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት ያልኩት ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እየወጡ ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ልዩ፥ ክብርት፥ ውድ፥ ምርጥ፥ አገር መሆኗን፥ የገዘፈ ምድራዊ በረከት ከሰማይ ሊወድቅባት አናቷ ላይ የተንጠለጠባት አገር መሆኗን፥ ሕዝቧም ልዩ፥ ከማንም በምድር ከሚገኝ ሕዝብ ይልቅ መለኮታዊ ትኩረትን የሳበ፥ በዘመን መጨረሻ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ብቸኛና ምርጥ ሕዝብ መሆኑን የሚሰብክ ትምህርት ነው። ኢትዮጵኝነት ከልክ ያለፈ ሙግሳ-ኢትዮጵያ እና ኢጋኖ-ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵኝነትና ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት በአጭሩ ይህ ነው።

ኢትዮጵኝነት ከኢትዮጵያዊነት የገነነ ስነ ልቡና ነው። ጽንፈኝነትን የተቃባ የበላይነት ስሜት ነው። ሆን ብለው ወይም ሳያውቁ የሚገቡበት ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች፥ ኢትዮጵያውያንም ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ የላቁ፥ የተለዩ፥ የገነኑ፥ የተወደዱ፥ የተመረጡ መሆናቸውን የሚቀበልና ይህንኑ ፕሮፓጋንዳ የሚያበጋ እና የሚነዛ ንቅናቄ ነው። ሰዎቹ ጽንፈኛ ሲሆኑ ኢትዮጵያዊ የበላይነት ወይም ኢትዮጵያዊ ምዕከልና (Ethiocentrism) የተጠናወታቸው ይሆናሉ።

[3] መጀመሪያ የተጻፈው *Ethioopia Shall Soon What?* እና የአማርኛውን ኢትዮጵያ እጆቿን ምን? ይመልከቱ።

[4] መጣጥፉን ካነበቡ ሰዎች መካከል ኢትዮጵኛ ወይም ኢትዮጵኝነት የሚለው ቃል ቀድሞም የነበረ ነው ያሉኝ ጥቂት ሲኖሩ ቃሉ የተጻፈበትን ምንጭ እንዲጠቁሙኝ ወይም እንዲልኩልኝ ጠይቄ መልስ አላገኘሁም።

[5] የእንግሊዝኛው Ethiopianism የሚለው ቃል የተለያዩ ጽሑፎች ተጠቅመውበት አንበሌአለሁ። ትርጉሙ ግን በዚህ ጽሑፍ ከተጻፈው ኢትዮጵኝነት ጋር አንድ አይደለም። ያገኘኋቸው የተለያዩ ትርጉሞች በግርጌ ማስታወሻ ቀርበዋል።

ታሪክ እየተሻሙ ሁሉን ኢትዮጵያዊ ማድረግ በሌሎችም የተባለና የተጻፈ ጉዳይ ነው። አንዳንድ ኢትዮጵኞች፥ እዚህ እንደምንመለከተው ወደ ፊት በኢትዮጵያ በሚሆነው ላይ ሲያተኩሩ አንዳንዶች ደግሞ ወደ ኋላ ሄደው ታሪክን ሁሉ የኢትዮጵያ ሊያደርጉ ይመኛሉ። አንድ መጽሐፍ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን፥ ለምሳሌ፥ እንበረምን፥ ዮቶርን፥ ባሮክን፥ የጌታችንን እናት ማርያምን፥ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስንም ሳይቀር ኢትዮጵያዊ አድርጎ ያቀርባል።[6] የሌላ አንድ መጽሐፍ ጸሐፊ የሁሉን ምንጭ ኢትዮጵያዊ ያደርጋል። አዳምና ሔዋን አበሾች ናቸው፤ ቋንቋቸውም ግዕዝ ነው፤ ኖኅ ከመርከብ የወጣው አራራት ሳይሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፥ ሔኖክ ኢትዮጵያዊ፥ መልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ ነው፤ ወዘተርፈ።[7] ለነገሩ አዳምና ሔዋን ኢትዮጵያውያን ከሆኑ ሌላውን ኢትዮጵያዊ እያሉ መዘርዘር ለምን አስፈለገ? አዳምና ሔዋን ኢትዮጵያውያን ስለሆኑ በድፍኑ አቼቢም፥ ማከዶናልድም፥ ቻንግም ኢትዮጵያውያን ናቸው። ደግሞ፥ እነ አዳም ኢትዮጵያውያን ከሆኑ ኢትዮጵያ ከነአዳም ትቀድማለች ማለትም ነው።

ሌላ አንድ መጽሐፍ፥ "በሰሜን ኢትዮጵያ ትግራይ ትግሮት ትግራይ ትግሪኛ ትግራይ ትግሪት የሚባሉ የነገዶችና የቦታ ስሞች ይገኛሉ። በቴግሮስና በኤፍራጥስ አካባቢ የሰፈሩት የሐም ነገዶች በራሳቸው ስም ወንዙን ቴግሮስ /ቲግሪት ትግሮት ብለው ሰይመውት ይሆናል።"[8] በራሳችን ማንነት ራሳችንን ጥቅጥቅ አድርገን የሞላን ሰዎች ከሆንን ሌላውን ከራሳችን ወይም ራሳችንን ከሌላው አስተከከለን ማየት ይሳነናል። በፊደል እያቆላለፍን ጤግሮስ ትግራይ ነው ካልን አሜሪካ አማራ ነው፤ ካምቦዲያ ከምባታ ነው ከማለት ምን ሊያግደን ነው?! ኢትዮጵኝነት ይህንም ማድረግ ይሞክራል። ከመሬት ተስፈንጥሮ ታሪኮችን ሁሉ የራስ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ወደ ኋላም ወደ ታሪክ፥ ወደ ፊትም ወደ ትንቢት እየሄዱ ማቀላበስ ለኢትዮጵኝነት ትልቅ ነገር አይደለም።

የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ ኋላ የሚወስደውና ክብርን የሚያላብሰው ከዓለማዊው ይልቅ ሃይማኖታዊው ትምህርት ነው። ክብረ ነገሥትን ወደ እንግሊዝኛ የመለሰው ዋሊስ በጅ በመጽሐፉ መግቢያ ገፅች እንዲህ ብሎአል፥ *ክብረ ነገሥት የተመረጡት የአይሁድ ሕዝብ የታመኑ ሆነው ባለመገኘታቸው ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ አገራቸው በልዩ ሁኔታ የመንፈሳዊቱና የሰማያዊቱ ጽዮን መኖሪያ ልትሆን በእግዚአብሔር የተመረጠች መሆኗን እንዲያምኑ የተጻፈ መጽሐፍ ነው።*[9] ሕዝቡ አይሁድን የተካ ልዩ ሕዝብ፥ አገሪቱም እስራኤልን የተካች ሆና እንድትታይ ተብሎ የተደረሰ መጽሐፍ ነው ማለት ነው። እንዲህ የሚያምኑ ሰዎች በዘመናችንም ቢኖሩ አያስገርምም። ወደ ክብረ ነገሥት በመጠኑ እመለስበታለሁ።

በጥቅሉ ሲታይ Ethiopianism የሚለው ቃል ኢትዮጵያዊ የነፃነት ስነ ልቡናን የሚጋራ አፍሪቃዊ ስሜት ነው። እዚህ ኢትዮጵኝነት ካልኩት በጥቂቱ ብቻ የተቀራረበ ራሱን የቻለ

[6] ንቡረ እድ ኤርምያስ ገጽ 10፥ 106፥ 134፥ 137።

[7] አማረ አፈለ ብሻው፤ ገጽ 36፥ 44፥ 80።

[8] ዶ/ር ሀብተማርያም አሰፋ፤ ገጽ 41።

[9] Budge p. xli.

የተለየ አመለካከት ነው። በፊተኛው መጣጥፍ የEthiopianismን ትርጉም ሌሎች ካዩበት አንጻር ጽፌ የነበረውን ትርጉሞቹን ከግርጌ አስቀምጫለሁ።[10]

ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነትን ክርስቲያናዊ ሊያደርግ የሚሞክረው ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በመጽሐፍ ቅዱስ የመጠቀሳቸው ጉዳይ ነው። ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ 43 ጊዜያት ተጠቅሰዋልና ይህን መጠቀስ በማውሳት ኢትዮጵያን ልዩ የማድረግና በእግዚአብሔር የቀን መቁጠሪያ ሰሌዳ ውስጥ ደምቆ የተጻፈ ቀጠሮ የተያዘላት አገር መሆኗን ከሕዝባዊ ትንቢቶች ጋር ገምዶ የሚያስተምር ትምህርት ነው።

ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት ከስብከትነት እና ትምህርትነት ባለፈ መልኩ አሁን የአገር አምልኮት እየሆነ ነው። ነገሩን አምልኮት ያስመሰለው ወይም ያደረገው ፖለቲካው ሳይሆን ሃይማኖታዊ ደበሎ ያለበሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ የወጣ ትምህርት ነው። ኢትዮጵኝነት ከታማኝ ዜግነትና ከአገር መውደድ ስሜት ወደ ብሔራዊ ኩራት፥ ከብሔራዊ ኩራት ወደ አገራዊ ስካር፥ ከአገራዊ ስካር ከላይ እንዳልኩት ወደ አገር ጣዖትነት ያለፈ ሆኖአል። ይህንን ለኢትዮጵያ መለኮትን እያላበሰ (demigod እያደረጋት ያለ) ጉዳይ ነው ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት ያልኩት።

[10] http://www.blackpast.org/?q=gah/ethiopianism እንዲህ ይገልጠዋል፤ ኢትዮጲያኒዝም የአፍሮ አትላንቲክ የስነ ጽሑፍና ሃይማኖታዊ ባህል ሲሆን የመነጨውም በ18ኛውና 19ኛው የእንግሊዝ ቅኝ አገሮች የጋራ ከሆነ የፖለቲካና የሃይማኖት ተሞክሮ ሲሆን ይህም በ19ኛው መቶ ኢትዮጵያ ነጻ አፍሪቃዊት መሆኗ ራስን የማስተዳደር ችሎታ መግለጡና የጥቁር ብሔራዊ ስሜት ማዳበሩ መሆኑን ይጽፋል። ይህ ትርጉም ከአፍሪቃና በቅኝ አገዛዝና በባሪያ ንግድ ከአፍሪቃ ከተፈናቀሉ ጥቁሮች እንጂ ከኢትዮጵያ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የለውም።

http://en.wikipedia.org/wiki/Ethiopian_movement ደግሞ ይህ ጽንሰ አሳብ ግልጽ ካለመሆኑ የተነሣ ለመፍታት አስቸጋሪ መሆኑን በማውሳት ጀምሮ እንዲህ ይፈታዋል፤ "በእውነቱ ርዕዮት አይደለም፤ ስነ መለኮታዊ አቋምም አይደለም፤ የፖለቲካ መርሐ ግብርም አይደለም። ብቻ ከ1890-1920 የሚገኙ ክርስቲያን መሪዎች በአፍሪቃ ውስጥ ሆኖ ክርስቲያን ስለመሆን ያሏቸው የአሳቦች፥ የልምዶችና የይሁንታዎች ስብስቦች ናቸው።

http://encyclopedia2.thefreedictionary.com/Ethiopianism ይህኑ ስያሜ ከሰሐራ በታች ያሉ አፍሪቃውያን አገሮች አብያተ ክርስቲያናት በ19ኛው መቶ መጨረሻ ከነበራቸው የቅኝ አገዛዝ ጥላቻ የተነሣ ለአፍሪቃና አፍሪቃውያን የሚመች ክርስትናን ለመለማመድ ሲባል የተፈጠረ ንቅናቄ መሆኑንን ያስረዳል።

http://www.aksum.org/ ወይም http://www.ReligiiousConsultants.com/ ይህንን ቃል ethiopianism የሚያስተዋውቀው የድረ ገጽ ክፍል የሁሉ ነገር ቅይጥ ስለሚያደርገው ብዕር የሚሞላ ነገር አይገኝበትም። ይህ ገጽ ስለ ኢትዮጵያ ከልክ የገዘፉ ነገሮች የጻፈ ሲሆን፥ ግሪካውያን አምላክ ከኢትዮጵያውያን ጋር ልዩ ቁርኝት አለው ብለው ያምናሉ። ኢትዮጵያ ዲበ አካላዊ (Metaphysical) የሆኑች መንፈሳዊውና አካላዊው የሚገናኝባት ስፍራ ናት። ኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱሱም የሳይንሱም ዔድን ገነት መኖ ስፍራ ናት። የሕይወት ዛፍ ስፍራና የመጀመሪያው ኃጢአትም የተፈጸመባት ቦታ ናት። ንቅናቄአው የ300 ዓመት ዕድሜ ቢኖረውም የ3000 ምስጢራዊ ታሪክ እንዳለው፥ ኢትዮጵያ ለአይሁድ፥ ከክርስቲያንና ለሙስሊሞች ልዩ አገር ነች ይላል።

ለኢትዮጵኝነት ክርስቲያናዊ ካባ የደረቡለትና መንፈሳዊ ያስመሰሉት ክርስቲያን ኢትዮጵኞች ናቸው። እነዚህ ክርስቲያን ኢትዮጵኞች የኢትዮጵያን ልዩ ስፍራነትና የኢትዮጵያውያንን ልዩ መሆን (አገሪቱንም ሕዝቡንም) ያለ ልክ ከፍ አድርገው የሚከቡ ንግርቶች የሚናገሩ፥ ስብከቶችን የሚሰብኩ፥ በቃሉ ብርሃን ያልተፈተሸ፥ ቃሉ ስለ ጠቅላላው የወደፊት ትንቢት ከሚያስተምረው አስተምህሮ ጋር ምንም ያልተነጻጸረ ትምህርት የሚያስተምሩ፥ ለሰዎች ስሜት የሚመቹና ጆሮ የሚሰቡ ሕዝባዊ ትንቢቶችን የሚተነብዩ ሰዎች ናቸው። ሕዝባዊ ትንቢቶች የምላቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት የሌላቸው፥ የሰዎችን ስሜት የሚያሞቁ፥ ብዙኃኑን የማያስቆጡ፥ የሕልም እንጀራ እያጎረሱ የሚያስገሱ ትንቢያዎች ናቸው።

ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት በኢትዮጵያዊ ክርስትና ላይ የተደገፈ ነው። ምንም የክርስትና ምስሉና ምሣሌው ክርስቶስ፥ መታወቂያው መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም ክርስትና በሕዝቡ አመለካከት፥ ኑሮ፥ ኅሊና ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ የመኖሩን ያህል ሕዝቡና ሕዝባዊው ባሕልም በክርስትና ላይ የሚያሳድረው ጫና፥ የሚያሳርፈው ጥላ ወይም ድባብ አለ። ስለዚህ አሜሪካዊ ክርስትና ከፓኪስታናዊ ክርስትና በቁርበቱ ቢለያይ አያስገርምም። ኢትዮጵያዊ ክርስትናም የራሱ ቁርበት አለው። ይህ ደግሞ በጥቅሉ በክርስትና ላይ፥ በተለይ ደግሞ፥ በክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት ላይ ጫና እንደሚያደርግ የታወቀ ነው። ዓይናችን ጤናማ ቢሆንም የምናይበት የተበላሸ መነጽር የምናየውን ነገር መልክም ቅርጽም ሊለውጥብን ይችላል። ዓይናችን ራሱ ችግር ካለበት ደግሞ የእይታው ብልሽት የባሰ የከፋ ይሆናል።

ለኢትዮጵያ ያለን አመለካከት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ላይ ራሳችን የምንጨምርበትና ይህን የጨመርንበትን ቃል እየቀባነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲመስል የምናደርገው ከሆነ፥ ደግሞም ትውፊታችንን እና አገር በቀል ተረቶቻችንና እየደራረትንና ንግርቶችን እንደ እውነት እየተቀበልን ያንን የሚደግፍ ጥቅስ እየመዘዝንና እያለበስነው የምናመናፍሰው ከሆነ ኢትዮጵያዊው ክርስትናችን በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ክርስትናችን ላይ መጥፎ ጫና ይፈጥራል።

"እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ምን ተናገረዎት?"

ከአምስት ዓመታት በፊት 'ኢትዮጵያ እጅጉን ምን?' የተሰኘውን መጣጥፍ እንድጽፍ ያነሳሣኝ Ethiopia: The God Factor የተባለው መጽሐፍ ነበር። መጽሐፉ ኢትዮጵኛ ነበርና ጽሑፉ የመጽሐፉ ምላሽ ባይሆንም መንደርደሪያው ነበረ። በየጊዜው በዚህ ርዕስ ላይ ጥቃቅን ነገሮችን ብጽፍም ይህንን እንዳዘጋጅ ያንደረደረኝ ደግሞ ሳክርድ ኢንተርናሽናል ሚኒስትሪ በተባለ አዘጋጅ እኤአ በ2009፥ What is GOD Saying About Ethiopia? የሚል ርእስ ተሰጥቶት በአማርኛ የተዘጋጀ ቪድዮ ነው።

የቪድዮ ዝግጅቱ ወደ 30 ያህል ኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፥ እና የክርስቲያን አገልግሎቶች መሪዎች የተናገሩበትና በቀጣዮቹ ጥቂት ዓመታት አገሪቱ ምን እንደምትመስል የተነበዩበት ነው።

የቪድዮ ዝግጅቱ ዋና ዓላማና ግብ በመግቢያው ላይ እንደተነገረው እግዚአብሔር በቃሉና በመንፈሱ ስለ ኢትዮጵያ የተናገረውን በማቅረብ ሕዝቡን ማንቃትና ማስታጠቅ መሆኑ ተገልጦአል።[11]

አንዱና ዋናው ተጠያቂዎቹ የተጠየቁት ጥያቄ እንደ ቪድዮው ርዕስ፥ 'እግዚአብሔር በግልዎ ስለ ኢትዮጵያ ምን ተናገረዎት?' የሚል ነው። መልሶቹን ቀደም ሲል በቅንጭብ ተመልክተናል። ዝቅ ብለንም እንመለከታለን። ጥያቄው በግልጽ እግዚአብሔርን ተናጋሪ፥ ሰዎቹን ሰሚና ተቀባይ፥ አቀባበሉን ድምጻዊና ራእያዊ፥ ርዕሱን ኢትዮጵያን ያደረገ ነው። የዘመን አቆጣጠሩ ግልጽ ተደርጎ ባይቀመጥም ከሚናገሩት ሰዎች ገለጣ የዘመኑ አቆጣጠር በፈረንጆቹ መሆኑ ይስተዋላል። የሰዎቹ ትንቢትና ራእይ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሳይሆን የግለ ሰቦች መረዳት ነውና ስሕተት ነው ወይም እውነት ነው ማለቱ ተጨባጭነት በሌለው ጎሊናዊ (subjective) ጉዳይ ክርክር ብቻ ነው የሚሆነው። እንደተባለው በአንጻራዊ አጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ የተነገሩት መፈጸማቸው ይታያል። ብዙዎቹ የጉብኝት ዘመኑን በድፍን ነው የሚናገሩት፤ በአጭር ጊዜ፥ በጥቂት ዓመታት፥ በኔ ትውልድ ዘመን፥ በኔ ጀነሬሽን ውስጥ፥ ወዘተ ነው ቋንቋቸው። ከተናጋሪዎቹ አንዱ በ30 ዓመታት ውስጥ ያዩት ራዕይ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተንብየዋል።

እዚህ የማወሳው ጉዳይ በጠቅላላው የቪድዮው ሥራና በተጠየቁት አገልጋዮች ምላሽ ላይ ቢሆንም ትኩረቴ ሰዎቹ ሳይሆኑ ጉዳዩ መሆኑን ከወዲህ ላስረዳ እሻለሁ። በቪድዮው ዝግጅት ውስጥ የተላለፉት ትንቢያዎችና በአጠቃላይ ስለ ኢትዮጵያ የተነገሩት ነገሮች፥ እንዲሁም ኢትዮጵኝነት ራሱ የተሳሳተ ትምህርት መሆኑን ነው የምሞግተው። የሰዎቹን ግፊት (motive) አላውቅም። ያንን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻውን ነው። የሚታየውንና የሚደመጠውን ቀድሞውኑ በተጻፈልንና ሌላውን ሁሉ በምንፈትሽበት ቃሉ መፈተሸና ከቃሉ ጋር ይስማማል፤ ወይም ይጣላል ማለት እንችላለን።

"በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ይናገራል ወይ?' ተብለህ ብትጠየቅ መልስህ ምንድርነው?" የሚል ጥያቄ ቀድሞውኑ በአንባቢዎች ውስጥ ሳይጫር አይቀርም። መልሴ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ተናግሮአልና ከተጻፈው ቃሉ ጋር እኩያ ሥልጣን ያለው፥ እንደተጻፈው ቃሉ አድርገን ልንጠቅሰው የምንችለውን ነገር አይናገርም የሚል ነው። ስለዚህ ማንም፥ '. . . ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር' የሚል ሰው የሚናገረው ያ ነገር በተጻፈው ቃሉ ውስጥ ያለ ቃል ከሆነ ቃሉ ነው መነበብና መሰበክ ያለበት። ያ ደግሞ ቀድሞውኑ ተጽፎአል። የሚጋጭ ከሆነ ደግሞ ያ ሰው ሐሰተኛ ተንባይ ነውና አሁን ደግሞ የአዲስ ኪዳን ዘመን ነውና እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን በድንጋይ ባይወገርም ከመበረታታት ይልቅ በቤተ ክርስቲያን መገሰጽ አለበት። ይህ ማለት መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ሕይወት ውስጥ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሠራው የአብርሆትና የምሪት ነገር የለም ማለቴ ነው? አይደለም። ይህ የአብርሆትና የምሪት ነገር

[11] በሦስት ክፍል የተዘጋጀው ቪዲዮ ከዚህ ይጀምራል፤ https://www.youtube.com/watch?v=jbjTXM-s5C0። ከዚያ ክፍል ሁለትን እና ሦስትን ማየት ይቻላል። ይህን ጽሑፍ የምታነብቡ የተናጋሪዎቹ ቃላትና አሳብ ለማግኘት ምንጩን እንድታዩት አበረታታለሁ።

መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ውስጥ እየኖረና እየሞላው የሚሠራው ሁነኛ ሥራው ነው። ነገር ግን ቃሉ እንዲጻፍ ያደረገውና የጻፉትን ሰዎች የነዳው መንፈስ ቅዱስ ካስጻፈው ቃሉ ጋር የሚጻረር ነገር አይናገርም።

ከእግዚአብሔር እንደተቀበሉት ቃል አድርገው ከተናገሯቸው ትንቢያዎች ወደ 90%ው ምድር፥ አገር፥ ቁስ፥ ምጣኔ ሃብት፥ እና ፖለቲካ ተኮር ናቸው። የበርካቶቹ ትንቢቶች ቅደም ተከተሉም ራሱ ኢኮኖሚ፥ ፋይናንስ፥ ፖለቲካ ብሎ ከዚያ በኋላ ነው መንፈሳዊው የሚነሣው። መንፈሳዊው ጉዳይ እንዲያውም ተጨማሪ ምርቃት እና የእግረ መንገድ አሳብ ብቻ ይመስላል። እነዚህ ቁሳውያን ትንቢቶች ቢፈጸሙ የተፈጸሙት ነገሮቹ የትንቢት ወይም ራእይ መልስ ሆነው ነው? ወይስ አገሪቱ በኢኮኖሚ መንገድ በተቀደደላት ፈር ሄዳ ነው? የሚለው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች፥ የትንቢት መፈጸምን ብቻውን የእውነተኛ ነቢይነት መስፈሪያ ማድረግ እንደሌለብንም ማስተዋል አለብን። የተአምር መፈጸም ብቻውን የእውነተኛ ነቢይ መታወቂያ ወረቀት አይደለም። ስለዚህ ጉዳይ ዘዳ. 13፥1-3 እንዲህ ሲል ያስረዳናል፤

በመካከልህም ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሣ፥ ምልክትም ተአምራትም ቢሰጥህ፥ እንደ ነገረህም ምልክቱ ተአምራቱም <u>ቢፈጸም፥</u> እርሱም፦ ሄደን የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንከተል እናምልካቸውም ቢልህ፥ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትወድዱት እንደ ሆነ ያውቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትሰማ።

እዚህ ላይ ይህንን ጥቅስ መጥቀሴ በ2030 በነፍስ ወከፍ የአንድ ኢትዮጵያዊ አማካይ ገቢ 40 ሺህ የአሜሪካ ዶላር ቢሆን እንኳ ይህ ትንቢት ከእግዚአብሔር ነው የሚል ግዴታ ውስጥ እንዳንገባ ቃሉ እንደሚያስተምረን ለማሳየት ነው።

አንድ አገር በኢኮኖሚ መምጠቋና ሕዝቧ በቁሳቁስና በገንዘብ መበልጸጉ ከእግዚአብሔር ሞገስን ማግኘት ነው ብለን የተሳሳተ ሚዛን ላይ ተቀምጠን እንዳናስቀምጥ አደራ። የትልቁ በረከት፥ ማለትም፥ እግዚአብሔርን የማወቅና የእርሱ ተከታይ የመሆን ጸጋ አድርገንም አንይ። እንዲህ አስበን ዛሬ የዓለምን የመጀመሪያዎቹን ትልልቅ ሀብታም አገሮች በቅደም ተከተል ብናይ ሚዛናችን ይሰበርብናል። <u>ኳታር</u> የእስላም አገር ሆና ክርስትና ከ10% ያነሰ፤ <u>ሉግዘምበርግ</u> የካቶሊክ አገር ሆና ወንጌላዊ ክርስትና ከ3% ያነሰ፤ <u>ሲንጋፖር</u> 50% በላይ የምሥራቅ ሃይማኖቶች ሆኖ ክርስትና ከ18% ያነሰ፤ <u>ኖርዌይ</u> ሉተራዊ ሃይማኖት የመንግሥት ሃይማኖት ሆኖ 43%ውን ሕዝብ ይይዛል፤ ቤተ ክርስቲያን በየሳምንቱ የሚሄደው አንጡራ ክርስቲያን ግን 1% ብቻ ነው። ከቀረው ሕዝብ ከ45% ግማሹ እስላም ሲሆን የቀረው የተለያየ ሆኖ ጥንቆላና ሰይጣናዊ ሃይማኖት በእጅጉ በፍጥነት እያደገ ነው። <u>ብሩኔይ</u> እስላም የበላይ፥ የምሥራቅ ሃይማኖቶች ተከታይ ሆነው ክርስትና ከ10% ያነሰ ነው። <u>የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬት</u> እስላም አገር ሆና ክርስትና ከ7% በታች ነው። ምድራዊ ብልጽግና የመንፈሳዊ ብልጽግና ነጸብራቅ አይደለም።

የምንም በጎ ነገር ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ሳንረሳ የእነዚህን የመጀመሪያ ትልልቅ ሃብታም አገሮች ሥጋዊና መንፈሳዊ ሚዛን ስናይ ኢኮኖሚያዊ ቅንጦትን ከሰማያዊ በረከት ጋር

ማቆራኘት ክፉ ስሕተት ሆኖ እናገኘዋለን። ኢኮኖሚያዊና ምድራዊ ሃብትን ከመንፈሳዊነትና ከእግዚአብሔር ሞገስን የማግኘት መስፈሪያ አድርጎ ማቅረብ እግዚአብሔርን መምሰልን ምድራዊ ማትረፊያ ማድረግ ነው። ኢትዮጵያ እጆቿዋን ማንሳቷን መንፈሳዊ ዝንባሌ፥ ይህንንም ዝንባሌ የምድራዊና ሥጋዊ ድሎትና ቅንጦት መቀበያ አድርገን ምድራዊ ትልቅነትን መጠበቅ መስመር መሳትና እግዚአብሔርን የመምሰልን ትርጉም ማዛባት ነው።

ዘዳ. 13፥1-3ን ስትጠቅስ ተናጋሪዎቹን የሐሰት ነቢይ ማለትህ ነው፤ መቼ ሌሎች አማልክት አስመለኩ? የሚል ጥያቄም ሊነሣ ይችላል። ኢትዮጵኝነት እኮ የአገር አምልኮ እየሆነ መጥቶአል። ሕዝባችን በፍጥረቱ አምላኪ ነው። 'ድል የነሳው ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ' (ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ) ብለው የክርስቶስን ማዕረግ ለራሳቸው ሹመት የሰጡ ንጉሥን ሳይጠይቅ ተቀብሎ የሚሰግድ ሕዝብ ኖሮን ያውቃል። ንጉሡ ዛሬም ይመለካሉ። እውነት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ራእ. 5፥5 ላይ የተጻፉት 'አንበሳ' ናቸው? ብሎ መጠየቅን ነውር ብሎ የሚቆጥር አምላኪ ሕዝብ ኖሮ ያውቃል፤ አሁንም አለ። የይሁዳ አንበሳ ታሪክ ወደ ሰሎሞንና የሳባ ንግሥት፥ ከዚያም ዘልሎ በዘፍ. 49፥9 ያዕቆብ ይሁዳን ወደ መረቀበት ቃል የሚሄድ ቢሆንም ራእ. 5፥5 የክርስቶስ ማዕረግ ነው። ራስታዎች ኢትዮጵኞች ናቸው። ስለ ራስታዎች እምነት፥ በተለይም ራስታፋሪያኒዝም ውስጥ ስላለው ኢትዮጵኝነትና ስለ ኢትዮጵያ ጽዮንነት በጻፈችው ጽሑፍ ጆኒፈር እስኮዌራ እንዲህ ብላለች፥

> . . . ሌላው ነገር፥ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ኢትዮጵያውያን የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆኑ ብቻ ሳይሆን መንግሥታቸው ለዘላለም የሚገዛ ጠንካራና ኃያል ሕዝብ እንደሆኑም ነው። በዘፍ. 49 ይሁዳ በአንበሳ ተመስሎአል፤ ይህም የራስታዎች ንቅናቄ ዋና ምልክት የሆነውን [ኃይለ] ሥላሴን የሚወክለው የይሁዳ አንበሳ ነው። ይህ የዘፍ. 49፥9-12 (ተጠቅሶአል) ምንባብ የሚያሳየው የይሁዳ አንበሣ [ኃይለ] ሥላሴ ኃያል እንደሚሆንና እንደሚከበር ግዛቱ ኢትዮጵያ እና ነገዱ የሆኑት ኢትዮጵያውያን ጠንካራና ማንም የማይነካቸው እንደሚሆኑ ነው። ይህ ምንባብ በጥብቅ የሚያሳየው [ኃይለ] ሥላሴ፥ ዙፋኑና ኢትዮጵያ በዓለም አሸናፊው ኃይል (dominant force) እንደሚሆኑ ነው።[12]

ኢትዮጵኞች ኢትዮጵያውያን ብቻ አይደሉም።[13] በእውነቱ እንዲህ ያለው የኢትዮጵኝነት ትንቢት ዓለም አቀፋዊ ተጋቦት የያዘ ትንቢያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነ ወይም የፍጻሜ ዘመናት መለኮታዊ ዕቅድ የታሰረበት ከሆነ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ የዓለም ተንባዮችም የሚያወሩት ጉዳይ መሆን ነበረበት። ቢስቱም እንኳ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ ቃሉን ሳይመረምሩ የሚናገሩ ሁሉ መሳት ነበረባቸው። የኢትዮጵኞችን ትንቢያ የመሰለ ነገር ግን ከራስታዎች በቀር ሌሎች ሲናገሩት ተሰምቶና ተጽፎ አይታይም።

[12] Skowera, Jennifer; Holy Zion! A Study of Ethiopianism in Rastafarianism with a Focus on the Concept Of Ethiopia as Zion; online version.

[13] በተጨማሪ በራስታዎች ላይ የጻፍኩትን ራስታዎችና እምነታቸው ይመልከቱ።

አገር መውደድና ለቃሉና በቃሉ መቆም

ኢትዮጵያን መውደድና ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት መቆም ለውድድርና ለውርርድ መቆም የለባቸውም። ኢትዮጵኝነት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ጋር ለመቆም ብቃትና አቅም የለውም። በደስ አለኝ 'እግዚአብሔር ተናገረኝ' የሚሉ ሰዎች ከምንም ነገር በፊት ስለ እግዚአብሔር መናገር ማወቅና ማጤን ያለባቸውን አንድ ዐቢይ ነገር መናገር እፈልጋለሁ። ይህ ማወቅ ያለባቸው አንድና አንድ ብቻ የሆነ ትልቅ ነገር እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ ስለ ወደፊቱ የሚናገረው ነገር ሳይሆን አስቀድሞ ስለ አሁኑና ስለወደፊቱም የተናገረው ነገር ነው። ይህ አስቀድሞ የተናገረው ደግሞ የተጻፈልን ቃሉ ነው። ስለ ወደፊቱ ለማወቅ መሄድ ያለብን ወደ ፊት ሳይሆን ወደ ኋላ ነው። ወደ ተጻፈው ቃል ነው መሄድ ያለብን።

የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ ነው። ድጋፍም፥ ምርኩዝም፥ ድጎማም አይፈልግም። እግዚአብሔር አስቀድሞ የተናገረውን ነገር ካወቅን ስለ ወደፊቱ የተናገረውም በዚያ ውስጥ ነው የሚገኘው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚጨመር የወደፊቱን ነገር የሚናገር ትንቢት የለም። አስፈላጊው በሙሉ ተነግሮአል። መንፈስ ቅዱስ የተጻፈውን ነው የሚያበራልን እንጂ አዲስ ቃል አይጨምርም። ኢትዮጵያን በተመለከተ አስቀድሞ የተነገረ ነገር ካለ (42ቱ ወይም 43ቱ ጥቅሶች ማለት ነው) እንደ ስንደዶ አንዴ ተመዝዛ ሳይሆን <u>በሙሉ</u>፥ ከስፍራው ተሸንጥሎ ሳይሆን <u>በዐውዱ</u>፥ በዘመናችን ሳይሆን <u>በዘመኑ ርዕይ</u>፥ በተጻፈለት ሳይሆን <u>በተጻፈበት ቋንቋ</u> ነው መታየት ያለበት። እነዚህን ነጥቦች በመጨረሻው ላይ አነሣቸዋለሁ። እዚህ ላይ ግን ይህን ልበል፤ ያንን አስቀድሞ የተጻፈውን ሙሉና ያልጎደለ፥ በራሱ የሚቆምና ሥልጣን ያለው ቃል ያላወቀ ወይም አውቆ ስፍራ ያልሰጠ ተንባይ ሲዘላብድ ራሱን ያገኛል። ይህ መዘላበድ ደግሞ ብዙ (ቢያንስ ሁለት) ትልልቅ ችግሮች አሉበት።

<u>አንደኛውና</u> ዋናው ችግር ከተጻፈው ቃል ጋር መጋጨቱ ነው። ስለ ኢትዮጵያ የሚነገሩት ትንቢቶች ከታች እንደምንመለከታቸው አገሪቱን፥ 'በሞቴ፤ ወደ ፎቴ!' የሚል በምድር ጉዞዋ አንደኛ ማዕረግ ላይ የሚያስቀምጥ ግብጣ ነው። ኢትዮጵያ በዓለም ላይ የተረፈች አንድና ብቸኛ፥ እግዚአብሔር የመጨረሻው የክፉ ቀን የዓለም መጎብኛ አድርጎ ሊጠቀምባት ደብቆ ያስቀመጣት የቁጠባ ገንዘብ፥ የመጨረሻ መሳሪያ፥ የብርድ ቀን ጋቢ፥ የዝናብ ቀን ጃንጥላ ተደርጋ ቀርባለች። ይህ ከትልቅ ድፎ ላይ ሳያሳንሱ ለራስ የቆረሱት መብል ነው።

ጌታና ሐዋርያቱ የተናገሩት የመጨረሻው ዘመን ምን እንደሚመስል የተጻፉልን ግልጽና ጉልህ ትምህርቶች በገሃድ የሚነበቡ ናቸው። ከክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት በፊት የዓለማችን መልክ እየተዋበ፥ ፖለቲካው ፍጹምና መለኮታዊ ፍርሃትን እየተላበሰ፥ ምድር ከጦርና ከጦር ወሬ ነጻ እየሆነች፥ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር፥ መንግሥትም ከመንግሥት ጋር ስምም እና ሰላም እየሆኑ፥ ራብና ቸነፈር ከምድረ ገጽ እየጠፉ፥ የምድር መናወጥ እየከሰመና ስነ ምሕዳር እየታደሰ፥ የስሕተት ትምህርቶች፥ ሐሳውያን ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሶች ደብዛቸው እየጠፋ፥ ፍቅር እየሞቀችና እየጋለች ይሄዳሉ አልተባለም። ይህ የቃሉ እውነታ እንጂ የጸለምተኛ እይታ አይደለም። ከታች የዶሚኒየን ቲዮሎጂን በምጠቅስበት ክፍል ይህን እንደገና አነሣለሁ።

<u>ሁለተኛው</u> ችግር የትንቢቶቹ አለመፈጸም የራሳቸውንም የሌሎችንም መንፈሳዊ ሕይወት የሚረብሽ መሆኑ ነው። ሰዎቹና ስሚዎቻቸው ከቃሉ ጋር፥ እርስ በርስም የሚሸካከሩበት

ሁኔታ ሊኖር ይችላል። እነዚህ የተባሉት ነገሮች ሳይፈጸሙ ቢቀሩ ተናጋሪዎቹ ያፍሩ ይሆናል። ከእግዚአብሔር ጋር ቅያሜ ውስጥ ይገቡ ይሆናል። ተሳስቻለሁ ይቅርታ አድርጉልኝ ማለት ይኖርባቸው ይሆናል። ሰሚዎች ደግሞ ከቀድሞው ያላነሰ መደናገጥና መደናገር ይውጣቸው ይሆናል። ቃሉን መብላት ትተው ትንቢት እያሸተቱ፥ ያልበሉትን፥ ግን ያሸተቱትን ትንቢት እያገሱ የሚኖሩ ይበዙ ይሆናል። አየር የተጠቀጠቁ ቀፎ ክርስቲያኖች በበዙበት በዚህ ዘመን ቱባ ተንባዮች የሚሰጣቸው የገነነ ስፍራ ኋላ ከሁለቱም አቅጣጫ ኩምሸሽ ማለትን ይፈጥር ይሆናል።

እነዚህ ሁለት ችግሮች እንደ ዋዛ ብቻ መታየት የለባቸውም። ስለ ኢትዮጵያ የሚተነብዩ ተንባዮች የሚናገሩትን ነገር መጠርጠር ወይም አለመቀበል *መንፈስ ቅዱስን መቃወም* ተደርጎ በአንዳንዶች ተወስዶ ያውቃል። እንዲህ ትንቢቶቹን የሚጠረጥሩና የማይቀበሉ በቃል ድንጋይ ይወገራሉ። አዲስ ኪዳን ሆነና ነው እንጂ በብሉይ ዘመን ነቢያቱ ነበሩ ያልተፈጸመ ትንቢት ሲናገሩ ይወገሩ የነበሩት። ውግራቱ ደግሞ በቃል ድንጋይ ሳይሆን በድንጋይ ድንጋይ ነው።

እንደገና ልበል፤ አገርን መውደድና ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት መቆም ለውርርድና ለውድድር መቆም የለባቸውም። አገርንና ሕዝብን መውደድ አንድ ነገር ነው። ከመውደድ የተነሣ ግን ከቃሉ ጋር የሚፋለስ ትንቢያ ውስጥ መግባት ሌላ ነገር ነው። ጥቁር መውደድን ከነጭ ምኞት ጋር ለውሰን ጠይም የሆነ ነገር ፈጥረን ያ ጠይም ነገር እውነት ነው ብንል እውነት አይደለም፤ ስሕተት ነው። መውደድ ሲደመር ምኞት እኩል አይሆንም እውነት። እውነት ብንወድደውም ብንጠላውም እውነት ነው።

ጥላቻ የተጣጋው ሰው ካልሆነ በቀር፥ ማንም ስለ ትውልድ ቀየውና ስለ ትውልድ አገሩ መልካምነት፥ ስለ ሕዝቡም በጎ የማይሻ የለም። መሪም ከሆነ የገዘፈ የራስ መውደድ በሽታ የተጠናወተው ካልሆነ በቀር ሕዝቡን የሚግጥና አገሩን የሚያወድም ሰው አይኖርም። እንደ ክርስቲያን ለአገራችንና ለሕዝባችን መማለድ ተገቢያችን ነው። ጤናማ የአገርና የሕዝብ ፍቅር መኖሩ መልካም ነው። ጤናማ የዜግነት ግዴታን መወጣት ማለፊያ ነው። ለምድራዊ መንግሥት ስለመገዛት በሮሜ 13 አጽንቶ ያስተማረው ሐዋርያው ጳውሎስ በፊል 3፥30 ደግሞ፥ *እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን*፤ ብሎአል። በዚህ 'አገራችን' የተባለው ቃል πολίτευμα ፖሊቲውማ የሚል ነው። ፖለቲካ የሚለው ቃል ከዚህ የተያያዘ ነው። ከምድራዊ ስፍራ ያለፈ መታወቂያን፥ አኗኗርን፥ ዜግነትን ያቀፈ ቃል ነው። አንዳንድ ትርጉሞች ዜግነታችን ሲሉ ተርጉመውታል። አገራችን በሰማይ ነው ማለት ምድራዊ ዜግነት የለንም ማለት አይደለም። ወይም ከአገራዊ መብት፥ ኃላፊነትና ግዴታ የጸዳን ሰዎች ነን ማለት አይደለም። እንደ ክርስቲያን ዜጋዎች ኃላፊነታችንን ሳንታክት የምናከናውን ሰዎች መሆን ይጠበቅብናል። ነገር ግን እኛ የአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በምድራዊ አገር የተጠፈርን አለመሆናችንም ሊገባን ያስፈልጋል።

<u>በብሉይ ኪዳን ዘመን</u> እስራኤል ብለው የሚጠሯትና የሚመኩባት አገር ነበረች። ብሔራዊ ትምክህት ልዩ ስፍራም ነበረው። ቢሆንም የእግዚአብሔር ግንኙነት ከሳር ከቅጠሉና ከአፈሩ፥ ከተራራና ሸንተረሩ ጋር አልነበረም። ጉዳዩ ከሕዝቡ ጋር ነበር። የእግዚአብሔር ርስት ሕዝቡ ነው። ይህንንም ሕዝብ እንኳ አሳልፎ መስጠቱና ለአያሌ ዘመናት አገሪቱ ወናና ባድማ

እንድትሆን መፍቀዱ ጉዳዩ ከመሬቱ ብቻ ሳይሆን፥ ከሕዝቡ ሕዝብነት (nationhood) ጋርም ሳይሆን፥ ከሕዝቡ መንፈሳዊነት ጋር መሆኑን በገሃድ ያሳያል።

<u>የመጀመሪያዎቹ የአዲስ ኪዳን አማኞች</u> ከምድር ጋር የታሰሩ ሰዎች አልነበሩም። በአዲስ ኪዳን ዘመን የመጀመሪያዎቹ አማኞች በነበሩበት ዘመን አይሁድ (የመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት በሙሉ አይሁድ ነበሩ) ቅኝ ተገዢዎች ነበሩ። 40 ዓመታት እንኳ ሳይሆን ያ ቅኝነትም ቀርቶ አገር የለሽና የተበተኑ ሕዝብ ሆኑ። እንደገና አገር የሆኑት በ1948 እኤአ ነው። ጳውሎስ አገራችን በሰማይ ነውና ያለው ይህ ብታኔ ከመሆኑ ጥቂት ቀደም ብሎ ቢሆንም የቃሉ እውነትነት ክርስቲያኖች ከምድር ጋር ያለመታሰራቸው ጉዳይ ነው።

<u>እኛ የዚህ ዘመን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት</u> በሥጋ ምድራዊ አገርና ዜግነት ቢኖረንም ከምድርና ከምድራዊ አገር ወይም ምድራዊና ዓለማዊ ሥርዓት ጋር የታሰርን ሰዎች አይደለንም። ከላይ እንዳልኩት ጤናማ የአገርና የሕዝብ ፍቅር መኖሩና ጤናማ የዜግነት ግዴታን መወጣቱ መልካም ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያን ተገቢም ነው። በተለይም፥ ማንም መንግሥታዊም ሆነ ማኅበራዊ፥ አካዳሚያዊና ፖለቲካዊ ተቋማት ሊቆሙበት በማይችሉት በዚህ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ከፍተት ይህንን ተቃውሶ መቅረፍ የክርስቲያኖች ብቸኛ ተግባር ነው። ቃሉን የሚሰብኩ ሁሉ የመሰበክ፤ የሚያስተምሩ ሁሉ እንደ ቃሉ የማስተማር ግዴታ አለባቸው።

ዶሚኒየን ቲዮሎጂ እና የነገ ተስፈኝነት

ይህን ጽሑፍ እየጻፍኩ ለዕዝራ ቁ. 32 እያዘጋጀሁ ሳለሁ የፌስቡክ ገጼን ስከፍት ወንድም ስሜ ታደሰ የጻፈውን አንድ ጽሑፍ አገኘሁ። ጽሑፉ 'የወፍ ማስፈራሪያ እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች' በሚል ርዕስ በሚካኤል ሽፈራው ተደርሶ ከታተመው መጽሐፍ የወፍ ማስፈራሪያን ታሪክ በአጭሩ በመዳሰስ ከክርስቲያናዊና አገራዊ ግምጋሜ ጋር ያገናዘበበት ጽሑፍ ነው። እዚህ ላይ ከስሜ ጽሑፍ ሁለት አናቅጽ ልውሰድ፤

> "የወፍ ማስፈራሪያ" ገለፃዬን በሌላ መሰረታዊ መረጃ ልደግፈው፤ ሁላችን ሀገራችንን ኢትዮጵያ ልንወዳት፣ ልናከብራትና ልናገለግላት ይገባል የሚል ፅኑ አቋም አለኝ። ከዚህም የተነሳ ኢትዮጵያዊነቴን ልቀይረው ወይም ላሻሽለው አልችልም እንዲህም ቢሆን ግን የመሰለ ግን ደግሞ አሳች የሆነ ኢትዮጵያ ተኮር እምነትን የነሪጥ መመልከት አለብን የሚል ፅኑ አቋም አለኝ። በመሰረቱ በነሪጥ ሊታይ የተገባውን ይህን እምነት በመላው ወይም በአብዛኛው ዜጋ አስተሳሰብ ውስጥ ያሳደገችው ቤተክርስቲያን ናት ብዬ በግሌ አምናለሁ።
>
> በ1996 ዓ.ም "ኢትዮጵያና አርባ ሁለት ጥቅሶቿ" በሚል ርዕስ በአውደ ትንቢት ጥናታዊ መጽሔት ላይ ቀርቦ የነበረው ፅሑፍ ለዛሬው የማስፈራሪያ ወፍ" ገለፃ ሌላኛው መነሻዬ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ አርባ ሁለት ስፍራዎች ላይ ኢትዮጵያ ተኮር መግለጫዎች ተፅፈዋል ከዚህም የተነሳ በርካቶች ኢትዮጵያ በስፋት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመወሳቷ ብቻ ከማንም ሀገር በበለጠ የተባረከች፣ ለእግዚአብሔር በልዩ ማዕረግ የተመረጠች፣ ለልምላሜ እንጂ ለድርቅ ያልታሰበች፣ ለእድገት እንጂ ለውድቀት ያልታሰበች፣ ሀገር ሆና ተቆጥራለች። ከዚህም የተነሳ አልፎ አልፎ ድርቅ ቢገጥማት፣ አልፎ አልፎ በጦርነት ውስጥ ብታልፍ "ነገ ተስፋው ይመጣል እግዚአብሔርም የገባላትን ቃል ሁሉ

> ይፈፅማል" በማለት ምኞትን እንደ እንጀራ በመቁጠር በርካታ ኢትዮጵያውያን ዛሬን ሳይኖሩበት የነገ ተስፈኞች ሆነው ቀርተዋል።[14]

"ምኞትን እንደ እንጀራ በመቁጠር በርካታ ኢትዮጵያውያን ዛሬን ሳይኖሩበት የነገ ተስፈኞች ሆነው ቀርተዋል።" እውነተኛ አባባል ነው። ዛሬን እንዳይኖሩ የሚያደርገው ጉዳይ ደግሞ ተመሳቅለው በቀረቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና በሰው ትንቢቶች አማካይነት የተገነባ ኢትዮጵኛ ተስፋ ነው። ይህ ሃይ መባል አለበት። ይህ ሃይ ማለት ዋጋ የሚያስከፍል ሊሆን ይችላል። ከላይ የተጠቀሰው የወፍ ማስፍራሪያ የተባለው ታሪክ ለወፎች ማስፈራሪያ የተተከለው ሰው መሳይ ማስፈራሪኞ (scarecrow) ማስፈራሪኞ ብቻ እንጂ ሰው አለመሆኑን ያረጋገጠውን ወፍ ሌሎቹ ወፎች አናምነውም ብለውት፤ እንዲያውም ይባስ ብለው ሰዎች ከሚባሉት ጋር ተሻርኮ ሊያስፈሯን ነው ብለው ወፎች ተሰብስበው በጣጥቀው ቆራርጠው እንደገደሉት ያወሳል። ጸሐፊ ስሜ አሳቡን ሲደመድመው፥

> ከዚህም የተነሣ እስከዛሬ ድረስ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተሸጋገረልን መገለጫ ሁሉ በድግግም ሊፈተሽ ይገባዋል። የሌለ ተስፋ እና ቃል ኪዳን ሀገርን አያለማም፤ እግዚአብሔርንም አያስከብርም፤ ይልቅስ "የወፍ ማስፈራሪያ" ሆኖብናልና ተጠግተን ልናወቅ፣ ልናይና ተግባራዊ ልናደርገው የሚገባ መለኮታዊ መመሪያ እያለ ትውልድ በቅብብል በተቀባበለው ልማድ ላይ ብቻ መጽናት ጥፋትን ጋባዥ ይሆናል የሚል ስጋት አለኝ።

ብሏል። እውነት ነው፤ <u>የሌለ ተስፋ እና ቃል ኪዳን</u> ሀገርን አያለማም፤ እግዚአብሔርንም አያስከብርም። ዛሬ ኢትዮጵኞች የሚያቀብሉን የሌለ ተስፋ ነው። ተስፋ ከምኞት የተለየ ቢሆንም የሌለ ከሆነ ከምኞትም ያነሰ ነገር ነው።

ኢትዮጵያ በአንድና በሁለት የጥንት ወቅቶች ስልጡንና ዘበናይ ነበረች። ከግብጽ ጋር ወግና እስራኤልንም እንኳ የወጋ ጦር ነበራት። ባሕር ተሻግራ ገዝታ ታውቃለች፤ በጎዥዎችም ተረግጣ ታውቃለች፤ ከነአርጤክስስ እስከነ ሙሶሊኒ። በልጥጋና ጠግባ ታውቃለች፤ አጥታና ተርባም ታውቃለች። የወደዷት መሪዎች ኖረዋት ያውቃሉ፤ የጋጧትም እንዲሁ። ይህ የአገሮች ሁሉ ጣፈንት ነው። ከአገሮችና ሕዝቦች በነዚህ ዐደቶች ያላለፈ የለም። ስለዚህ ኢትዮጵያን አንቆለጳጵሰንና አሸብርቀን፥ የዕንቆጳ ዘውድ በራሷ ጭነን ግምጃ ነስንሰን ዙፋን ላይ የምናስቀምጣት ልዩና፥ አንድያና ብቸኛ አገር አድርገን ማየት ተራ ሽንገላ ነው።

በጥረትና በሥራ አድጎ ብሩህ ነገን በምናብ ማየት መልካም ነው። ነገን በተስፋ ማየቱ መልካም ቢሆንም በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታት ስታንቀላፋ የኖረችን አገር በ30 ዓመት ጣራ በርቅሳ እንድትወጣ ማለም አሁንም ገና ከእንቅልፍ ያለመንቃት ምልክት ነው። በዝብዙና አጭበርብሮ መበልጠግ ሙስናና ሌላውን ማቆርቆዝ ነው። ይህንን አድርጎ እንጣጥ ብሎ ሽቅብ መውጣት ይቻላል። ብዙዎችም ሲያደርጉ ይታያል። እንዲህ ያሉ ሙሰኞች በዓለም እንዳሉ ሁሉ ሙሰኛ ክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሉም ማለት የዋኅነት ነው። በንጽህና ንጹሑን ቃል የሚሰብኩ የመኖራቸውን ያህል የቤተ ክርስቲያን መድረክን እንደ መደብር የሚያዩና የሚያሳዩ የደለቡ ገንዘብተኞችና ምንደኞችም አሉ። መሥራትና መታተር መበረታታት የሚገባውን ያህል

[14] የጽሑፉ ምንጭ የአቶ ስሜ ታደሰ የፌስቡክ ገጽ።

ተወዝፎ መና መጠበቅ ግን ስንፍና መሆኑ ሊነገር የተገባው ጉዳይ ነው። ብዙዎቹ ክርስቲያን ኢትዮጵኞች ከዚህኛው የመና ናፋቂዎች ጎራ የሚመደቡ ናቸው። መና ጊዜያዊና የመከራ ስንቅ እንጂ ቋሚ መብል እንዳልነበረም ያወቁ አይመስሉም።

ነገን በብሩህ ተስፋ ማየት አንድ ነገር ነው። ነገ ምንም ይሁን ነገን የያዘ እግዚአብሔር እንዳለ በመረዳት በዚህ አምላክ እጅ ውስጥ ራስን መጣል ትክክለኛና ጤናማ ውሳኔ ነው። ነገር ግን ነገን በተመለከተ ከፍታና ተራራ እንጂ ሸለቆ የለም፤ ብርሃን እንጂ ጨለማ የለም፤ ማግኘት እንጂ ማጣት የለም፤ ሕይወት እንጂ ሞት የለም፤ መግዛት እንጂ መገዛት የለም የሚል አስገዳጅ ትምህርት ውስጥ መግባትና ማስገባት ሐሳዊ ትምህርት ነውና ስሕተት ነው። ይህ ስሕተት የኢትዮጵኞች አንድ ትምህርት ነው።

ነገ ኀዥነት እንጂ መገዛት የለም የሚለው ትምህርት ዋና አቀንቃኝ የሆነው Dominion Theology (የግዛት ስነ መለኮት) ከዚህ ተርታ ከሚኮለኮሉት ቀዳሚ የስሕተት ትምህርቶች አንዱና ትልቁ ነው። ዶሚኒየን ቲዮሎጂ የሚባለው የስሕተት ትምህርት በተለያዩ ስሞች ይታወቃል። Kingdom ወይም Kingdom Now Theology የመንግሥታሁን (መንግሥት አሁን) ስነ መለኮት፥ Latter Rain Movement የኋላኛው ዝናብ ንቅናቄ፥ The Manifest Sons of God የተገለጡት የእግዚአብሔር ልጆች፥ The Five Fold Ministry አምስት እጥፍ አገልግሎት፥ The New Apostoloc Reformation አዲሱ ሐዋርያዊ ተሐድሶ እየተባለም ይጠራል። ከመጨረሻዎቹ ሁለት ስያሜዎች የተነሣ ነው ነቢያትና ሐዋርያት የሚባሉት ሹመቶች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በጅምላ እየተገለበጡ የተቸረቸሩት። ሌሎችም ከዚህ የሚመሳሰሉ ንቅናቄዎች ቢኖሩም ጠቅልለን ግን በአንዱ ስም በዶሚኒየን ቲዮሎጂ እንጥራው። ንቅናቄዎቹ በስም ይለያዩ እንጂ ስነ መለኮታቸው በመሠረቱ አንድ ነው፤ ያም፥ የግዛት ስነ መለኮት ነው።

አዲሶቹ የሐዋርያትና ነቢያት ሹመቶችና ሹመኞች ከዚህ ትምህርትና በተለይም ከFive Fold Ministry ጋር የተቆራኙ ናቸው። ይህም የዶሚኒየን ቲዮሎጂ አንድ ገጽታ ነው። በቅርብ አንድ አሳች የሆነ ጽሑፍ ጽፎ ካስነበበና ከወቀስኩት ሰው ጋር ኢሜይል እንደገና ተለዋውጠን ነበር። በመጨረሻ በጻፈልኝ ኢሜይል ይህ ሰው ከመቅጽበት ከስሙ በፊት Apostle Prophet ብሎ ጽፏል። በአማርኛ እንዴት እንደሚጠሩት አላወቅኩም። ቀድሞ ስንጻጻፍ ወንድም እገሌ ነበር። ዛሬ እየሆነ የመጣው ማታ አቶ እገሌ ሆኖ ተኝቶ ጠዋት ሲነሡ ሐዋርያው ነቢዩ እገሌ ሆኖ መነሣት ይመስላል። ኤልዳድና ሞዳድ በሰፈር ትንቢት ሲናገሩ የሰማው ኢያሱ ሄዶ ለሙሴ ይህንን ጉዳይ ሲናገር፥ *ሙሴም፦ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ፥ እግዚአብሔርም በእነርሱ ላይ መንፈሱን ቢያወርድ አንተ ስለእኔ ትቀናለህን? አለው።* ዘኍ. 11፥29። የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ መልካም ነው። ጳውሎስም በ1ቆሮ. 14፥31 በአምልኮ ጉባኤ ውስጥ ሆነ እንጂ ይህንን የሚመስል ነገር ተናግሮአል። ትንቢት ከማነጽ ተግባሩ አንጻር ሁሉ ነቢያት እንዲሆኑ ያስመኛል። ነገር ግን ጳውሎስ በዚያው መጽሐፍ፤ 1ቆሮ. 12፥29 *ሁሉስ ነቢያት ናቸውን?* አለ። አይደሉም። ሊሆኑም አይችሉም። ይልቁንም በአዲስ ኪዳን የምናገኘው ነቢያቱን እንደ ሹመት ሳይሆን ትንቢቱን እንደ ስጦታ ነው።

ሰዎቹ ስጦታዎቹ ሲሆኑም የተሰጡ አገልጋዮች ናቸው እንጂ የገዢ ሹመቶች አይደሉም። መግዛትና የቅዱሳን በቅዱሳን ላይ መሰልጠን ከቶም የአዲስ ኪዳን አገልግሎት አሳብ

አይደለም። ሐዋርያነት ሹመት ከሆነ ሹመቱ ለመጀመሪያዎቹ ለአሥራ ሁለቱ የጌታ ሐዋርያት ብቻ የተሰጠ እንጂ ለሌላ አይደለም። በዚህ ዘመን ሐዋርያት ከኖሩ እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው የቀቡ ወይም አንድ ቡድን 'የቀባቸው' ሳይሆኑ ቤተ ክርስቲያን የላከቻቸውና ወንጌል ወዳልደረሰበት ጠፍ ክልል የሄዱ ናቸው። ወንጌል ሳይሰብኩ ከየቤተ ክርስቲያን የተለቀሙ ሰዎች ሰባስቦ 'ቤተ ክርስቲያን' እየከፈቱ Apostle Prophet ብሎ ሹመት የለም። ዛሬ ይህም አነሰና የላቁ ሆኖ ለመታየት 'ሱፐር ነቢያት እና ሱፐር ሐዋርያት' መባል ተጀምሯል። የሥልጣኗ ጉዳይ እጃቸው እስኪቀጥን የሚዘረጉላት ሆናለች። የብዙዎች አካሄድ ከሙከራው ሲታይ የጽድቅ አመራርን ከመፈለግ የተነሥሳ ሳይሆን ከሥልጣኗ ጋር ገጠኝትና ገንዘብ ስላለበት ነው።

ወደ ዶሚኒየን ቲዮሎጂ እንመለስ። የግዛት ስነ መለኮት ዋና ትምህርት በአጭሩ፥ አዳምና ሔዋን በኃጢአት በወደቁ ጊዜ እግዚአብሔር በነአዳም በኩል ሊገዛት የነበረውን ግዛቱን ምድርን በሰይጣን ተነጠቀ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ይህን ግዛት ከሰይጣን እጅ ፈልቅቀው የሚመልሱለትን የተወሰኑ የቃል ኪዳን ልጆችን እየተጠባበቀ ይገኛል። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ለሚያስነሣቸው ነቢያትና ሐዋርያት ራሳቸውን የሰጡ የዚህችን ዓለም ግዛቶች ወይም መንግሥቶች (kingdoms) የሚቆጣጠሩ 'አሸናፊ' ሰዎች ናቸው። እነዚህ ግዛቶች መልክዓ ምድራዊ ብቻ ሳይሆኑ ማኅበራዊ ተቋማትም ናቸው፤ ለምሳሌ፥ የፖለቲካ ግዛት፥ የሳይንስ ግዛት፥ የኪነጥበባት ግዛት፥ የትምህርቶች ግዛት፥ ወዘተ፥ ይባላሉ። እነዚህ ሰዎች ይህን በመቆጣጠር አገርን፥ ብሎም ዓለምን ይለውጣሉ፤ ምድርን ምድረ ገነት ያደርጋሉ፤ ይህም የግዛት ወይም የመንግስት ዘመን (Kingdom Age) ይሆናል። ክርስቶስ በእነርሱ አድርጎ ስለሚገዛ የቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ መነጠቅ የሚሉት ነገር አይኖርም። ይህ የሺህ ዓመቱ መንግሥት ቀብድ እንጂ ሌላ አይደለም። ልክ የይሆዋ ምስክሮች ነን የሚሉት እንደሚያስተምሩት ምድር እያማረባት፥ ከዛሬ ይልቅ ነገ እየተዋበች በአዝግመት ወደ በጉ ሙሽሪትነት ትለወጣለች። የክርስቶስ ምጽአት ሁለት ደረጃዎች የመጀመሪያው በሐዋርያቱና ነቢያቱ የሚደረግ አገዛዝ (dominion) ሲሆን፥ ሁለተኛው ክርስቶስ አንድ ቀን ሺህ ዓመቱ ሲያልቅ ወይም በመካከል ላይ መጥቶ ይህንን መንግሥት ወይም ግዛት ከነዚህ ሐዋርያትና ነቢያት እጅ ሲረከብ ነው። ዶሚኒየን ቲዮሎጂ በአጭሩ ይህ ነው።

የግዛት ስነ መለኮት ከመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ ዘመን አስተምህሮ ጋር ግንባር ለግንባር የሚጋጭ ስሕተት ነው። የኢትዮጵኖችን ስነ መለኮት ስናጤነው፥ የሐዋርያቱንና ነቢያቱን ጋጋታ፥ 'ትውልድ አስነሣ ብሎኛል' እያሉ የሚፍገመገሙትን ሰዎች ኣጅንዳ፥ ስለ ሥልጣን፥ ስለ ገንዘብ የሚዘረጋጉትን ሰዎች፥ ያለፈላትና እሰማይ ጉያ ድረስ የተምዘገዘገች ኢትዮጵያን በምናባችን የሚያሳዩንን ሕልመኞች ተረት ስንሰማ የዶሚኒየን ቲዮሎጂ ቁልት ነው የሚሸትተን። ቁሌቱን ብቻ ሳይሆን የዶሚኒየን ቲዮሎጂን ራሱን ድስቱ ውስጥ ፍጥጥ ብሎ እናየዋለን።

በመጨረሻው ዘመን የሚሆኑ የፍጻሜ ዘመናት ምልክቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተጽፈዋል። ጠቅለል አድርገን ስናያቸው፥ እውቀት ይበዛል፤ ዳን. 12፥4፤ የዓመጽ ሰው ይገለጣል፤ 2ተሰ. 2፥3፤ እንደ ኖኅ ዘመን፥ እንደ ሎጥ ዘመን ያለ ይሆናል፤ ማቴ. 24፥37፤ ሉቃ. 17፥28-30፤ መብላት፥ መጠጣት፥ ማግባት፥ መጋባት፥ ሰዶማዊ ዝሙት፤ የስሕተት አሠራርና የኢጋንጉት ትምህርት ይበዛል፤ 1ጢሞ. 4፥1፤ የተፈጥሮ አደጋዎች፤ የምድር መናወጥ፤ ማቴ. 24፥

7፤ ሉቃ. 21፥25-26፤ ሐሰተኛ ነቢያትና ክርስቶሶች፤ ማቴ. 24፥4-5፥11፤ ሐሰተኛ ሰላም፤ ጦርና የጦር ወሬ፤ ማቴ. 24፥6-7፤ 1ተሰ. 5፥3፤ ራብና ቸነፈር፤ ማቴ. 24፥7፤ ዓመጻ ይበዛል፤ ፍቅር ይቀዘቅዛል፤ ማቴ. 24፥12፤ ክርስቲያኖች ይሰደዳሉ፤ ማቴ. 24፥9-10፤ ክህደት ይበዛል፤ 2ጢሞ. 4፥3-4፤ ወንጌል ይሰበካል፤ ማቴ. 24፥14። ኢትዮጵኖች ለነገዋ ኢትዮጵያ የሚያዩት ሁሉ የዚህ ተቃራኒ ሲሆን የግዛት ስነ መለኮት ደግሞ ይህንን የመጨረሻ ዘመን አስተምህሮ ፈጽሞ ይከልሰዋል።

ኢትዮጵኛ ዝማሬዎች

ኢትዮጵኝነት በሕዝባዊ ትንቢትና በስብከት ብቻ ሳይሆን በመዝሙሮቻቸው ውስጥ ገጥጦ እየታየ ነው። እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነውን ጤናማ የአገርና የሕዝብ መውደድና ጤማና የዜግነት ኃላፊነት የቃሉ ሰባኪዎች ሁሉ መስበክ፤ የቃሉ አስተማሪዎችም ሁሉ ማስተማር አለባቸው። የጸሎት ሽክምን የተሸከሙም የጸሎት ምህላቸው መቋረጥ የለበትም። ዘማሪዎችም ይህን ቢያሳስቡና ቢዘምሩ ድንቅ ነው።

ካድማስ ማዶ ያለች፥ ምድር የማስባት
እትብቴ ስወለድ የተቀበረባት
በቁጣው በትር ተመትታ ያነከሰች፤
ከአሳቢ መች ተለየች?
ከጭንቀቴስ መች ተለየች?
ከጸሎቴስ መች ተለየች?
አስባት እናት አገሬን፤ ምሕረትህ ከሁሉም በላይ
ሰላምታህ ይምጣ ከሰማይ። (2)

የደረጀ ከበደ መዝሙር ነው። ከአሳቢ፥ ከጭንቀቴ፥ ከጸሎቴ መች ተለየች? ናፍቆት፥ አሳብ፥ ጸሎት፥ ጭንቀት፥ ልመና። ይህ 'ከኔ አሳብ አልተለየችም፤ አንተም አስባት' ልመና ነው።

በምድረ ኢትዮጵያ ባገራችን
ባራቱም ማዕዘን
ይውረድልን ሰላም ሰላም ሰላም
ጌታ ይብቃ በለን፤ እባክህ ተለመነን።
3፥ አ ሰላም ሰላም ሰላምስ ከወዴት ይገኛል?
ጌታ ሆይ ሁሉም አንተን ያያል፤
የኛንማ ልክ አየነው
ሰላም ከአንተ ነው። (2)

ከወንድዬ ዓሊ መዝሙሮች። ይህ የራስን ልክ ማየት ነው፤ የጌታን ቻይነት ማየት ነው። ይህ ጸሎት ነው፤ ልመናና ምልጃም ነው።

ስለ አገርና ስለ ሕዝብ የሚጸልዩና የሚለምኑ መዝሙሮች ያሉንን ያህል ግን ኢትዮጵኝነት የፈጠራቸውና ያወፈራቸው መዝሙሮችም እየቦነኑ ይገኛሉ።[15] አንዳንድ ዘማሪዎች ቃሉን በመዘመር ፈንታ፥ ወይም የምልጃና ጸሎት ምህላ በማቅረብ ፈንታ የኢትዮጵኞችን ምኞት እየተከተሉ የሰው ትንቢትና ራእይ እየዘመሩልን ይገኛሉ። ተነሺና አብሪ በሚል አንድ መዝሙር ውስጥ የአፍሪቃና የአውሮጳ፥ የዓለም ሕዝብ ሁሉ የኢትዮጵያን ክብሯን እንዳዩት ተዘምሮ (መቼ እንዳዩት ባይታወቅም በኃላፊ ጊዜ ነው የተዘመረውና ታይቷል ማለት ነው)፥

የናቁሽ ሁሉ የተጠየፉሽ፤ ጊዜው ሲመጣ ይሽው ሰገዱልሽ የሚል ስንኝ ተቀንቅኖአል። ሰዎች መጥተው ለኢትዮጵያ መስገዳቸው ነው እኮ እየተደነቀ የተዘመረው! ለአገር የሚሰግዱ ሰዎች መልካም እንዳደረጉ ተደርጎ ነው እኮ የተዘመረው! ሰዎች ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለአገር ሲሰግዱ ተደንቆ መዝዘመሩ ይገርማል!

ይህ ለኢትዮጵያ መስገድ የጣዖት አምልኮ ነው! ኢትዮጵኝነት የአገር አምልኮት ሆኗል የምለው እንዲህ ያለውን አዝማሚያም ነው። በመግቢያዬ ላይ፥ ይህ ጉዳይ ከአገር መውደድ ስሜት ወደ ብሔራዊ ኩራት፥ ከብሔራዊ ኩራት ወደ አገራዊ ስካር፥ ከአገራዊ ስካር ወደ አገር ጣዖትነትና ወደ አምልኮ ደርሷል ያልኩት ይህንን ነው። ስግደት የሚገባው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነውና እንዲያው ለኢትዮጵያ ተሰግዶ ቢሆን ኖሮ እንኳ ይህ እኮ በራሱ በዘማሪውም መወገዝ የነበረበት ነገር ነው። ግን ክርስቲያን ነኝ በሚል ዘማሪ ነው የተዘመረው። ይህ ምኞት ይሁን ቅዠት አይታወቅ እንጂ እውነት ግን አይደለም። ጠቅላላ ስነ መለኮቱ ደግሞ የተፋለሰና የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን የሚያስት መዝሙር ነው።

አገርንና ሕዝብን መውደድ አንድ ነገር ሆኖ ያንን ማምለክ ግን ሌላ ነገር ነው። ይህ አምልኮተ ጣዖት ነው። ሌላም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስነ መለኮት እስኪንኮታኮት ድረስ በምድራዊ አገር ፍቅር መስከር ኢትዮጵኝነት ሊሆን ይችላል፤ ምናልባት አርበኝነት ተደርጎ ሊታሰብም ይችላል፤ አርበኝነትና ኢትዮጵኝነት ክርስትና ግን አይደሉም። ይህ ከላይ ያየነው መዝሙር ውሸትም ስሕተትም ነው። መጥተው የሰገዱላት ስለሌሉ ውሸት ነው። ምናልባት ከኖሩ፥ ለአገር መስገድ ስለሌለባቸው ለአንድ ክርስቲያን ይህንን መዘመር ደግሞ ስሕተት ነው። ስሕተት ደግሞ ዝም ካሉት ዘምሞ ያዘምማል።

የመዝሙሮቻችን አዛባ ተዝቆ ባያልቅም እንዲህ ያለው አዝማሚያ ከኢትዮጵኝነት ጋር መቆራኘቱን አንርሳ። የየጁ ደብተራ ቅኔው ሲያልቅበት ቀረርቶ ሞላበት እንዲሉ ቅኔው እያለቀባቸው መጣ መሰለኝ ዘፈን በመዝሙር ላይ መደረት እንደ ግንባር ሥጋ ገጥቶ መታየት ከጀመረ ሰነበተ። *'ኢትዮጵያ ሆይ ሰሚ ትንቢት ልናገር፤ ከንግዲህ ኣይሆንም ጭንገፋና ውርደት'* ብሎ ዘምሮ ነበር አንድ ዘማሪ መተንበይ ሲከጅለው።

በቅርብ የወጣ አንድ 'መዝሙር' ቀረርቶ ነው። *'አገሬ ኢትዮጵያ (እምዬ ኢትዮጵያ) ዘንድሮ ለለፈልሽ፤ የፍቅር ሉዳኝ ኢየሱስ መጣልሽ . . .* ይላል። ዜማና ቅላጼው የጥሬ ቀረርቶ ነው። ይህን የሸለላና ቀረርቶ ዜማ ወደ ጎን ትተን ግን አለፈልሽ ዘንድሮ መባሉን እናጢን። ሌላ ትንሽ

[15] በአጠቃላይ ስለ መዝሙሮቻችን እየተንጋደዱ መምጣትና በዚህም ውስጥ ስለ ኢትዮጵኛ መዝሙሮችየሳተ አካሄድ ጉዳይ *ይድረስ ለዘማሪዎች* ክፍል አንድ እና ክፍል ሁለት በሚል በኡዲዮ ወይም በጽሑፍ ያዘጋጀሁትን ያድምጡ ወይም ይመልከቱ።

ቆየት ያለና ኢትዮጵያ እንዳለፈላት የሚለፍፍ መዝሙር፥ *'ኢትዮጵያ ለለፈላት፤ ኢትዮጵያ ለለፈላት፤ ሠራዊት መጣላት'* ይላል። እንዲህ ያሉ ጥቂት ያልሆኑ መዝሙሮች አሉን። ኢትዮጵያ እነዚህ መዝሙሮች የወጡ ዓመት ወይም ዘንድሮ አላለፈላትም፤ ኢየሱስም ዘንድሮም አልመጣም። ዘንድሮ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱንና ኢትዮጵያ እንዳለፈላት እያስመሰለ ያለው ግን ሰዎች ክርስትና አስነስተው ወደ መድረክ ያወጡትና በሙዚቃ አጅበው ወደ እስቱዲዮ ያስገቡት ኢትዮጵኝነት ነው።

ማንም አገር ወይም አንድ ሕዝብ አለፈለት የሚባልበት መስፈርት በጣም አወዛጋቢ ነው። ዓለም የወደቀችው ፊተኛው አዳም የወደቀ ጊዜ ነው። ዓለም አለፈላት ከተባለ ያለፈላት ሁለተኛው አዳም፥ ክርስቶስ በመስቀል በሞተና አዲሱ ኪዳን በተመሠረተ ጊዜ ነው። ኢትዮጵያ ወይም ፖላንድ ወይም ሜክሲኮ አለፈላት ማለት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት የራቀ አነጋገር ነው። እንደ አገር፥ የነዳዊትና የነኢያሱ አገር እስራኤልም አለፈልሽ ተብላ አትታወቅም። 'አለፈላት' 'አለፈለት' የሚሉት ቃላት ራሳቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የማይገኙ ናቸው። ቃላቱ ብቻ ሳይሆኑ አሳቡም አይገኝም።

በዘመናችን አነጋገር እነዚህ አገሮች አለፈላቸው፥ ቢያድጉና ቢመነደጉ ታደሉ ማለት አይቻልም አልልም። ከላይ የተመለከትናቸው የመጀመሪያዎቹ ስድስት በንዋይ የበለጸጉ አገሮች ያለፈላቸው አገሮች ናቸው ቢባል ትክክል ነው። አንዲት አገር ከድኅነት አረንቋ ወጥታ፥ ከተበዳሪነትና ተመጽዋችነት ወጥታ ራሷ ለጋሽ ብትሆን አለፈላት ልትባል ትችላለች። ነገር ግን ይህ፥ 'አለፈለት፤ አለፈላት' የሚሉት ነገር ቋንቋውም አሳቡም ዓለማዊ ብቻ ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። እየተነጋገርን ያለነው ደግሞ በክርስቲያንኛ ነው። በዓለምኛ እገሌ ወይም እገሊት አለፈላቸው የሚባሉት ቡትቷቸውን ጥለው ጥዱ ለብሰው ሲዘንጡ፥ ከደሳሳ ጎጆ ወጥተው እተንጣለለ ቤት ሲገቡ፥ ወይም በእግር መኳተን ቀርቶ በካሚዎን ሲዘቡኑ ነው። ለክርስቲያን የአመለካከት መዛባት ካልፈጠረው በቀር ለምድራዊ ተድላና አላፊ ነገር ነፍስ ውጥት እስክትል ድረስ መንሰፍሰፍ ወደ ሰማያዊው መንጠላጠል ሳይሆን ወደ ምድር መንከባለል ነው።

አሁን በገሃድ እንደምናየው ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት መኖር ብቻ ሳይሆን ገንኖ ብዙዎችን ሊያንገዳግድም ችሏል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵኝነትን በጥቅስ ስላሸበረቅነው ወይም ውኃ ረጭተን ክርስትና ስላስነሣነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይሆንም። ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ብታድግና፥ ለምሳሌ በ2015 ስሌት መሠረት ካለባት 19 ቢሊየን ዶላር ዕዳ ሙልጭ ብላ ወጥታ ራሷን ብትገነባና፥ 'አለፈላት' ብትሰኝ መልካም ነው። በ2030 የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነፍስ ወከፍ ገቢ 40ሺህ የአሜሪካ ዶላር ቢሆን፥ ይህ፥ 'እሰይ፥ እልል' የሚያስብል ነው። የሚያስዘፍንም ቢሆን አያስደንቅም። ታዲያ ያም ካስፈለገ ብሔራዊ መዝሙር ሊደረስለት ይገባው ከሆነ እንጂ፥ ደግሞም ከሆነ በኋላ ይዘፈንለት እንደሁ እንጂ፥ ገና ሳይሆን የኛ ትንቢታዊ ዘፈን መሆን የለበትም። የአምልኮ ቃልና መዝሙር አልቆብን የአገር ዘፈን መዝፈን፥ የባቢሎን ሰዎች የጽዮንን ዝማሬ ዘምሩልን ያሉት ተገላቢጦሽ ማለት ነው። እዚያ ካሉዲዎቹ ባቢሎናውያን ናቸው የጽዮንን ዝማሬ የጠየቁት። እዚህ ግን ዘማሪዎቹ ናቸው የባቢሎንን ዘፈን እየዘፈኑብን ያሉት።

2. ኢትዮጵኛ ትንቢቶች

"እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ምን ተናገረዎት?"

ከላይ በተመሳሳይ ንዑስ ርእስ ሥር እንዳልኩት ቀጥሎ የምንመለከተው የሳከርድ ኢንተርናሽናል አገልግሎት የኢትዮጵያን መጎብኘት አስመልክቶ ያቀረበውን የቪድዮ ዋና አሳብ ነው። በጠቅላላው ወደ 30 ያህል ሰዎች የተጠየቁት ሁለት ጥያቄዎች ሲሆኑ የመጀመሪያው እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ምን ተናገረዎት? ሁለተኛው እናስ ምን ይደረግ? የሚሉ ናቸው።

የሰዎቹ ትንቢትና ራእይ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሳይሆን የግለ ሰቦች መረዳት ነውና ስሕተት ነው ወይም እውነት ነው ማለቱ ተጨባጭነት በሌለው ኅሊናዊ (subjective) ጉዳይ ክርክር ብቻ ነው የሚሆነው። በተጻፈው ቃል ላይ የተጻፈውን ቃል ይዞ መነጋገር ይቻላል። እዚህ ግን የሰዎቹ ቃልና ምስክርነት ብቻ እንጂ ሌላ ነገር የለም።

እንደተባለው በአንጻራዊ አጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ የተነገሩት በጥቂት ዓመታት ውስጥ መፈጸማቸው ይታያል። ቀደም ሲል ከዘዳ. 13 በመጥቀስ እንዳልኩት ተፈጻሚነታቸው ታሳቢ እንጂ ዋና ተደርጎ መታየት የለበትም፤ ምክንያቱም ሐሰተኛ ትንቢቶችም ቃል በቃል ሊፈጸሙ ይችላሉ። ዋና ተደርጎ መታየት ያለበት ያ የተነገረው ነገር አስቀድሞ በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ታዝሏል? የሚለው ነው።

በቪድዮው ዝግጅት ውስጥ ወደ እውነተኛው ትንቢት፥ ማለትም ወደ ቃሉ፥ ወደ እውነተኛው መፍትሔ፥ ማለትም፥ ወደ ወንጌል እና ወደ ታላቁ ተልእኮ፥ ወደ ወንጌል ስርጭት እንመለስ ያሉ አገልጋዮችን በአድናቆት ተመልክቻለሁ። ጽሑፌ በኢትዮጵኝነት ላይ ያነጣጠረ እንደመሆኑ መጠን እነዚህን በጣም ጥቂት ሰዎች እዚህ ውስጥ አላካተትኳቸውም። ትኩረቴ በቪድዮው ውስጥ ባየኋቸው ኢትዮጵያን ፈጽሞ ልዩ፥ ቅጠሏንና አፈሯን መድኃኒት፥ ሕዝቧን የዓለም ቋጠሮ ፈቺና የዓለም ሕዝብ የመጎብኛ መሣሪያ በሚያደርገው አሳብ ላይ ይሆናል። ከቃሉ በመጥቀስም ኢትዮጵኝነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊያደርጉ የሞከሩ አሉ፤ ይህንንም ከቃሉ አንጻር እናየዋለን።

እዚህ የማወሳው ጉዳይ በጠቅላላው የቪድዮው ሥራና በተጠየቁት አገልጋዮች ምላሽ ላይ ቢሆንም ትኩረቴን በተመለከተ ሁለት ነጥቦችን ከወዲህ ላስረዳ እሻለሁ።

1. ትኩረቴ ሰዎቹ ሳይሆኑ ጉዳዩ ነው። ትኩረቴ የተላለፈው ትምህርት እንጂ ሰዎቹ አይደሉም። ከሰዎቹ ውስጥ አብረን ያገለገልንና አብረን የቆረስን አሉበት። ይህ አብሮ ማገልገልና መቁረስ ታዲያ ስሕተትን መጠቆምንና መከላከልን አይከለክልም።

2. ትኩረቴ ኢትዮጵያ ተኮር የሆነው ትንቢያ ላይ ነው። ከሰዎቹ ብዙዎቹ በዚህ የቪድዮ ቃለ መጠይቅ ውስጥ መልካም የሆኑ ቃሎችን ወይም ምኞቶችንና ምክሮችን ለግሰዋል። የኔ ትኩረት ኢትዮጵኛ በሆኑት አስተሳሰቦችና አስተያየቶች ላይ ነው። በቪድዮው ዝግጅት ውስጥ የተላለፉት ትንቢያዎች በቃሉ ሲፈተሹ ከተጻፈው ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይመሳሰሉም፤ ደግሞም፥ በአጠቃላይ ኢትዮጵኝነት ራሱ የተሳሳተ ትምህርት ነው በማለት ነው የምሞግተው።

የሰዎቹን ግፊት አላውቅም። የራዕያቸውን ምንጭ አላውቅም። ያንን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻውን ነው። የሚታየውንና የሚደመጠውን ግን ቀድሞውኑ በተጻፈልንና ሌላውን ሁሉ ከምንፈትሽበት መፈተሻ ከቃሉ ጋር አነጻጽረን ከቃሉ ጋር ይስማማል? ወይስ ይጣላል? ማለት እንችላለን።

ትንቢያዎቹ ከተጻፈልን ቃል ጋር ስለማይጣጣሙ የተጻፈው ቃል ምንጭ እና የትንቢያዎቹ ምንጭ አንድ እንዳልሆነ እርግጠኛ መሆን እንችላለን። ምንም ትንቢትም ሆነ ትምህርት ከተጻፈው ቃል ጋር የሚጋጭ ከሆነ፥ ወይም ከቃሉ ጋር ከመስማማት ይልቅ ለስሜት የሚመች ከሆነ ቃሉ ትክክል ተንባዩና አስተማሪው ስሕተት ናቸው። ለዕንባቆም ወይም ለሉቃስ ያንን የጻፉትን እንዲጽፉ ያደረገው መንፈስ ያንን የሚጻረርና ከዚያ ጋር የሚጋጭ ነገር በዘመናችን ይናገራል ማለት አይቻልም። እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ በዚህ ዘመን ተናገረኝ ያሉት ሰዎች ትምህርቶችና አጫጭር ምላሾቹ እነሆ።



ቴዎፍሎስ መኮንን፤ "እግዚአብሔር ለግለሰብ፥ ለግሩፕ፥ እንዲሁም ለምድር እንደሚናገር ሁሉ እግዚአብሔር ስለ አገራችን ስለ ኢትዮጵያም በቃሉና በመንፈሱ የተናገራቸው ብዙ ነገሮች እንዳሉ ሚኒስትሪው ያምናል። ከዚህም አንጻር ከነዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች አንደበት ስለ ምድራችን የተናገረውን የተለያዩ መልእክቶች በማቅረብ ሕዝቡን ለማንቃትና ለማስታጠቅ ሚኒስትሪው ይህንን መልእክት አዘጋጅቷል፤ ከዚህም አንጻር በዓለም ዙሪያ ላሉት ኢትዮጵያውያን በሙሉ የሚያስተላልፈው መልእክት ቢኖር፥ ለዚህ የእግዚአብሔር ድምጽ የበኩላቸውን ምላሽ እንዲሰጡ ነው። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።"

ይህ የጠቅላላውን የቪድዮውን አሳብ ወይም ግብ በተመለከተ የአገልግሎቱ ቦርድ ሰብሳቢ የተናገሩት ነው። የአገልግሎቱ ዓላማ 'የትምህርቱን ዓለም በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው' የሚል ጃንጥላ አሳብ ሲኖረው የዚህ ቪድዮ ዝግጅት እግዚአብሔር ስለምድራችን የተናገረውን በማቅረብ ሕዝቡን ማንቃትና ማስታጠቅ ነው። የትምህርቱን ዓለም መጠቅለል ሰፊውን ክርስቲያን ማንቃትና ማስታጠቅ ይመስላል። ከድረ ገጹም ከፌስቡክ ገጹም እንደሚታየው (የገጹ መልክ በየጊዜው ሊለዋወጥ ቢችልም) የአገልግሎቱ የአሁን መልኩ፥ 'የክብር ዘመን ለኢትዮጵያ' ነው። መሪ ቃሉ የከፍታ ዘመን ለኢትዮጵያ ከተባለው የቄስ በሊና መጽሐፍና ራእይ የተወሰደ ይመስላል። ይህንን ቪድዮ ያዘጋጁት ወገኖች ግብ ከላይ የተባለው መሆኑ ብቻ እንጂ የግፊቱ ምንነት አልተብራራም። ያንደረደሯቸው ጥቂት ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። በግልጽ አላስቀመጡትም።

ይህንን ቪድዮ ያዘጋጀው አገልግሎት ከምሑራንና ከትምህርቱ ዓለም ጋር ግንኙነትና ቁርኝት እንዳለው አገልግሎት ሆኖ ተነግሮአል። ይሁን እንጂ አንዲት አገር በፖለቲካ፥ በኢኮኖሚ፥ በሥልጣኔ፥ በማኅበራዊ ረገድ የምታሳየው ዕድገት አዝማሚያና መለኪያ መታየት ያለባቸውን አቅጣጫዎች ከምሑራዊ መስክ ማየትና ማሳየት ጭራሽ ግምት ውስጥ አልገቡም። ኢትዮጵያን በተመለከተም በየመስኩ ሙያዊ እውቀት ካላቸው ሰዎች ጋር የተደረገ ቅኝት የለም። ይህ አሳዛኝ አካሄድ ሲሆን የሚያመለክተው ክርስቲያናዊው አካዳሚያዊ ዓለምም ከቃሉ ሳይሆን ከሰዎች ስሜት ጋር መንሳዱንና መውደቁን ነው። አገልግሎቱ እንደ ክርስቲያናዊ አካዳሚያዊ አገልግሎት ከታየ ማለት ነው። ምናልባት የቪድዮው ዝግጅት መንፈሳዊውን አገራዊ

እንድርድረት ብቻ ለማሳየት የታቀደ ሳይሆን አይቀርም። ይህም ከሆነ በግልጽ መነገር ነበረበት።

ግቡ እንደተባለው ሰፊውን ክርስቲያን ሕዝብ ማንቃትና ማስታጠቅ ከሆነ የትምህርቱን ዓለም በክርስቶስ ሊጠቀልል እንደተነሣ አካል ጉዳዩን ወይም የቀረበውን ርእስ ከተለያዩ አቅጣጫዎች በማየትና በመመዘን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋርም በማስተያየት የቀረበ አለመሆኑ ይስተዋላል። ከትምህርትና ከንባብ ዓለም፥ ቃሉንም ከመመርመርና ከማጥናት ርቆ ትንቢያ እያሸተተ ለሚኖር ክርስቲያን ሕዝብ እንዲህ ያለ ድግስ ማቅረብን እንደ ትሩፋት ሊያዩት ይችሉ ይሆናል። ግን ይህ ብዙኃኑን ክርስቲያን እያነቃ ሳይሆን እያስተኛ፥ እንደ ቤርያ ሰዎች ቃሉን እንዲመረምሩ እያደረገ ሳይሆን ያልተፈተሸ መንገድን ዓይን ጨፍነው እንዲሄዱ ያደረገ ዝግጅት ነው።



የቪድዮው መንደርደሪያ እንደሆነው እንደ የቄስ በሊና ሣርካ የ2000 ዓመተ ምሕረት ትንቢያ አገራቱ በአራት ቀጣና ተከፍላ ሰሜኑ ኤርትራን ጨምሮ ወሎ፥ ጎንደር፥ ትግራይ በኢንዱስትሪ በልጽጎ፥ ባሌ፥ አርሲ፥ ሸዋ፥ ጎጃም በአግሮ ኢንዱስትሪ ጠግቦ እህል ከኛ ተርፎ ወደ ውጪ ሲላክ፥ ሐረርጌ፥ ሲዳሞ፥ ጋሞ ጎፋ፥ ከፋ፥ ኢሉባቦር፥ ወለጋ በአትክልትና ፍራፍሬ፥ ቅመማት፥ አበቦች በቀጥታ ወደ ውጪ የሚላኩባቸው አውሮፕላኖችና የአውሮፕላን ማረፊያዎች፥ ማዕድኑ፥ ኤሌክትሪኩ፥ ነዳጁ፥ አገሪቱ በ50 ዓመት በደን የተሸፈኑት ምድር መሆኗ፥ ንብኟ ቱሪስቶች አገሪቱን ወድደው ከመጡ በኋላ አልመለስም ሲሉ፥ ባለ ብዙ መርከብ ስትሆን፥ ከምታስገባው የምታስወጣው ሲበዛ፥ ከ2000 ጀምሮ ያለው 30ው ዓመት በሦስት ተከፍሎ የመጀመሪያው የችግርና ሽግግር፥ 2ኛው የመቶ ዓመት ኋላ ቀርነት የሚቀረፍበት፥ 3ኛው የ500 ዓመት ኋላ ቀርነት (አሰላሉ ግልጽ አይደለም) የሚሸቀነጠርበት ይሆናል። የአገሪቱ ጥቁር ማቅ ከአራቱም ማዕዘናት ሲቀደድ፥ የመከራ ዘመንም ሲያበቃ አይተዋል። በ30 ዓመት ኢትዮጵያ የአሁኗን ጃፓን [ትንቢቱ በሚነገርበት ጊዜ የነበረችውን] እንደምትደርስ ተናግረዋል። ይህ ኩበዙ በጥቂቱ ነው።

የቄስ በሊናን ቃል ከቃለ መጠይቁ መገልበጥ እጅግ በጣም ስለሚበዛ ነው ከማሳጠርም ባነሰ መልኩ ያቀረብኩት። ጠቅላላውን ለመስማት / ለማየት ምንጩን መጎብኘቱ ይረዳል።[16] ለንጽጽር፥ በ2000 የጃፓን GDP ወይም ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ከ4.9 ትሪሊየን ዶላር በላይ ነበር። የነፍስ ወከፍ (per capita) ገቢ ደግሞ ከ38 ሺህ ዶላር በላይ ነው። የሕዝቧ ብዛት በዚሁ ጊዜ 127 ሚሊየን ነበር። በተመሳሳይ ጊዜ በ2000 የኢትዮጵያ GDP 8 ቢሊየን ዶላር፥ የነፍስ ወከፍ (per capita) ገቢ ደግሞ ከ200 ዶላር በታች (194 ዶላር) ነው። የሕዝቧ ብዛት በጊዜው ወደ 70 ሚሊዮን ነው። በ2014 የኢትዮጵያ GDP ወደ 55 ቢሊየን ዶላር ሲጠጋ፥ የነፍስ ወከፍ (per capita) ገቢ ደግሞ በተለያዩ ጥናቶች ከ450 እስከ 550 ዶላር ደርሷል። ይህ የ15 ዓመት መልካም ዕድገት ነው፤ አገሪቱ 8 ቢሊየን ወደ 55 ቢሊየን፥ ነፍስ ወከፍ ደግሞ ከ194 ወደ 550 አድጓል። በተመሳሳይ ጊዜ ጃፓን ከ4.9 ትሪሊየን ወደ 37 ትሪሊየን ሲያድግ የነፍስ ወከፍ አማካይ ገቢ ብዙ ለውጥ አላሳየም። ይህ የተረጋጋ ካፒታላዊ ኢኮኖሚና የገንዘብ የመግዛትና ግሽበትን መቋቋም አቅም አንድ ምልክትም ነው።

[16] የአንዳንድ ተናጋሪዎችን ቃል ሙሉ በሙሉ ሳይሆን የተደጋገሙትን አሳቦችን ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው የመሰሉኝን ስዘልል ነጠብጣብ ምልክት (. . .) አድርጌባቸዋለሁ። ለዚህ ዝግጅት ጠቅላላው ንግግር የተጻፈ ስለሆነ ጠይቆ ማግኘት ይቻላል።

የአንድን አገር ኢኮኖሚ ጣራ ማስረገጥ ለእግዚአብሔር ከምንም ያነሰ ጉዳይ ነው። የምጣኔ ሃብት ሊቅነት የለኝም፤ ሆኖም ለአገር ኢኮኖሚ እሳቤ ውስጥ መግባት ያለባቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ጥቂቶቹ፥ የመላከና የማስገባት ገበያ፥ የአገሪቱ ገንዘብ የመግዛት አቅም (purchasing power of money)፥ የገንዘብ የመግዛት ዋጋ (ግሽበት)፥ ሥራና ሥራ አጥነት፥ የሕዝብ ብዛት፥ ወዘተ፥ ናቸው። ሕዝብን ብንወስድ፥ ባለፉት 15 ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ በ30 ሚሊዮን ያህል አድጎአል። በየዓመቱ 2 ሚሊየን ማለት ነው። በ2030 የኢትዮጵያ ሕዝብ 130 ሚሊየን እንደሚደርስ አንድ ጥናት ያሳያል።[17] ይህ በአሁኑ ዕድገት ብቻ ከተሄደ ማለት ነው። ፖለቲካዊ መደላደሉ፥ የአገር ሰላም፥ አገራዊ ጉርብትናና ግንኙነት፥ ማኅበራዊ ተራክቦ፥ ወዘተ፥ ስሌቱ ውስጥ የሚካተቱ ነገሮች ናቸው።

የኢትዮጵያ ጃፓንን መምሰል በብልጽግናና በኢኮኖሚ ብቻ መሆኑ በጀ እንጂ ይህ መመሳሰል ሃይማኖታዊ መልኩንም የሚይዝ ቢሆን ትልቅ ጥፋት ነው። ከጃፓን ሕዝብ ክርስቲያኑ ከ2% ያነሰ ነውና ክርስትና ከኢትዮጵያ ሊጠፋ ነው። ሌላው ተንባይ የኢትዮጵያ 90% በቅርብ ክርስቲያን እንደሚሆኑ ስለተነበዩ እርስ በርስ ቢገጫጭም ይህኛው ያስተካክለው።

እንደ ክርስቲያንና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አማኞች የመጨረሻውን ዘመን መልክም በውኃ ማጠብና አለቅልቀን መድፋት የለብንም። የኢኮኖሚ ዕድገት ብዙ ገንዘብ ማተም የሚመስላቸውና እግዚአብሔር ገንዘብ እንዲያትምላቸው የሚመኙ ሰዎች አሉ። ይህ ስሕተት ነው። ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኞች በረከት እና መባረክ የሚሉት ነገር የኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ ላይ ያተኮረና ያነጣጠረ ነው። ከዚያ የተለቀ ቢሆን መልካም ነበር። ካልሆነ ግን ከላይ የተባሉትና ሌሎቹም ሁሉ እሳቤዎች ወደ ዳር መገፋት የሌለባቸው ናቸው። ቢያንስ የቪድዮው አዘጋጆች ይህንንም ከጥናታቸው ውስጥ ቢያስገቡት መልካም ይሆን ነበር።



ቄስ ዓለሙ ሺጣ፤ "አሁን እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ የሕዳሴ ዘመን አምጥቶአል፤ ቤተ ክርስቲያን ታድጋለች ወንጌል ይፈጥናል፤ ወንጌልን ወደሌሎች የማድረስ ጊዜ እንደሆነ፥ ለኢትዮጵያ ጊዜ እንደሆነ . . . እግዚአብሔር ተናግሮአል፤ . . . የሰላም ዘመን፥ አብሮ ተቀባብሎ የመኖር ዘመን እንደሚሆን እግዚአብሔር ተናግሮታል፤ የተናገረውን ደግሞ ይፈጽማል። ትልቅ በረከት የምለው መንፈሳዊ በረከት ብቻ ሳይሆን . . . ምድራዊ በረከትም፥ የማቲሪያል በረከትም፥ የፀሐይ፥ የዝናብ፥ የኢኮኖሚ፥ የትውልድ በረከትም፥ የፖለቲካ በረከትም ሁሉ ለምድራችን እንደሚሆን አምናለሁ።"

ምድራዊና ቁሳዊ፥ የሕዳሴ፥ የስነ ምሕዳርና የፖለቲካ በረከት ብቻ ሳይሆን የመቀባበልና የሰላም ዘመን ከፊታችን መኖሩ መልካም ምኞት ነው። ተቀባብሎ መኖር ጥሩ ባህል ነው። ግን ጥንት ሰላም ሳይኖር ሰውን የሚያዘናጋ ሰላም የሚሰብኩ ነቢያት እንደነበሩ ወደፊትም እንደሚነሡ ቃሉ ያስተምራል። ሰላም የለም፤ አይኖርምም ብዬ ሽብር መፍጠሬ አይደለም። አንጻራዊ ሰላም አለ። ወደ ፍጻሜ ዘመን እየተራመድን ሳለን ወደ ፊት ከክርስቶስ መምጣት በፊት የሚኖር የሰላም ዘመን መኖሩን አስረግጦ ማወጅ እግዚአብሔር ከተናገረ ከተጻፈው ቃሉ ጋር የሚጋጭ አያደርገውም? የተነገረውን ከተጻፈው ለይቶ ማወቅና የተነገረውን

[17] http://www.ethiodemographyandhealth.org/PopulationPolicyandProjectionAynalemAdugna.pdf

በተጻፈው መፈተሽ ከዘመናችን ክርስቲያኖች፥ በተለይም ከእጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን አእምሮ በላጲስ ተፍቆ የጠፋ ይመስላል። መሪዎችም ሰዎችን ወደተጻፈውና በእርግጥ ወደሚፈጸመው ቃል ማመልከትና መምራት እንጂ ወደተነገሩ ትንበያዎች መንዳት የለባቸውም።



መጋቢ ዳዊት ሞላልኝ፤ "ኢትዮጵያ የታሰበች አገር ነች፤ እግዚአብሔር ያሰባት አገር ነች፤ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ብዙ የተስፋ ቃሎች አሉት፤ ብዙ ብሏል፤ በጣም ታላላቅ ሰዎች ተናግረዋል፤ ብዙ አባቶች ተናግረዋል፤ . . . በጣም ትልቅ በምድራችን ላይ ሊነነባ የሚገባው ነገር ምንድርነው? የእግዚአብሔር ሰዎች፥ እግዚአብሔር የጠራቸው ሰዎች ተቀባይነት ማግኘት አለባቸው፤ መከበር መቻል አለባቸው፤ እግዚአብሔር ከተናገረኝ ነገር ውስጥ የመጀመሪያው ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የሚነበኙ ነገሮች አሉ፤ የቱሪስት መስህብ የሆኑ የሰሜን ተራሮች፥ አክሱም፥ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፥ ባሌ ያለው ዋሻ አለ፤ ሌሎችም የተለያዩ ወፎች፥ አራዊት፥ . . . አሉ፤ እነዚህን ለማየት የሚመጡ ብዙ ፈረንጆች አሉ።

እግዚአብሔር የተናገረኝ ደግሞ ታላላቅ ሰዎች በኢትዮጵያ ምድር ስለሚነሡ . . . እግዚአብሔር የሚያስነሳቸውን ሰዎች ቅባት ፍለጋ፥ ይኼን ጸጋ ፍለጋ ብዙዎች ይመጣሉ፤ ነጮች ጥቁሮች ይመጣሉ፤ የሚመጡትም በትራንስፖርት ነው፤ በውጪ አገር ገንዘብ ነው ሚመጡት፤ በጣም ብዙ ናቸው፤ አሁን ሚገነቡት ሆቴሎች በምንም እይታ አይደለም፤ በጣም ብዙ ሆቴሎች፥ ሱፐርማርኬቶች፥ ሬስቶራንቶች የሚያስፈልጉን እነዚህን ሰዎች ለማስተናገድ ይመስለኛል። በጣም ከፍተኛ ዝማጅት እግዚአብሔር ጨርሷል፤ እነዚህ ሰዎች ልክ ሲነሡ ምድራችን መባረክ ትጀምራለች ማለት ነው። . . . እግዚአብሔር ይህንን ተናግሮኛል፤ ደግሞ ያደርገዋል።"

አንዳንዶች ተንባዮች መንፈሳዊውን በረከት በጨረፍታ ነካ ሲያደርጉት አንዳንዶቹ ጨርሶም አያነሱትም። አገራዊ በረከት የቱሪስት መስኅብነትና የውጪ ምንዛሪ ማግኘት ከሆነ ይህ ትንበያ ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ለቱሪዝም ኮሚሽን ታትሞ ቢሰጥ ውጤታማ ሳይሆን ይቀራል? የእኒህ መጋቢ ጠቅላላ አሳብ በቅርብ በአገራችን የሚነሡትን ባለ ቅባት ሰዎች የማስተዋወቅና ተቀባይነታቸውን የማሳመን ጉዳይ ይመስላል። ይህኛው የዶሚኒየን ቲዮሎጂ ቁልጭ ያለ ትምህርት ነው። ቅባት ፍለጋ፥ ጸጋ ፍለጋ ከቦታ ቦታ እንደ ዘላን መሄድን ማበረታታት እግዚአብሔርን በበረት ውስጥ እንዳለ ማስመሰል ነው። እግዚአብሔርን ከቦታ (ከኢትዮጵያ) እና ከጊዜ (ከቀጣዮቹ ጥቂት ዓመታት) ጋር ማሰር ነው።

የኩራቱ ጃኖ ደግሞ የመሳለሚያዋ፥ ቅባቱ የሚንዶለዶልባት የመቀቢያዋ አገር ኢትዮጵያ መሆኗ ነው። እግዚአብሔር በቦታ የሚመለከበት ዘመን ከብሉይ ኪዳን ጋር እኮ አብቅቶአል። 'በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም' መስገድ የሚያበቃ መሆኑን ጌታ አስተምሮአል፤ ዮሐ. 4፥21። ዝቋላና ቁልቢ ሲያስኬድ ለኖረ ባህል፥ 'ሕዝብ ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ!' ሲባል እውነት ሊመስል ይችላል። ግን አይደለም። እግዚአብሔር የሚመለከው በመንፈስና በእውነት ነው፤ መኖሪያውና ክብሩን የሚቀበለውም የሰው ልብ ነው። እግዚአብሔር ከደብረ ሊባኖስና ከቁስቋም ጋር እንዳልተቆራኘ ሁሉ ከኢትዮጵያ ወይም ከአዘርባይጃን ጋር አይቆራኝም።

አገሪቱ ብቻ አይደለችም። ተፈላጊው ነገር ራሱም የሚገርም ነው። ቅባት ፍለጋ ኢትዮጵያ! በዚህ ዘመን ለጨረታ ሳይወጣ እንደተሸጠና እንደተነገደበት 'ቅባት' እንደሚባለው ቃል ያለ ሌላ ቃል ያለ አይመስለኝም። በነገራችን ላይ ይህ ቅባት የሚባለው ቃል የዘመናችን 'ቃል-እምነት' አስተማሪዎች እንደሚጠቀሙበት ቅባት ተሰኝቶ የተጻፈው ሁለት ቦታ ብቻ (1ዮሐ. 2፥20 እና 27) እንደሆነ እናውቃለን? አንዳንዶቹ ቅባት የሚሉት ነገር፥ ለምሳሌ፥ 'ከቅባቱ

የተነሣ ቀንበር ይሰበራል' ሲባል ብዙ ጊዜ የሰማነው፥ ቃሉ በተጠቀሰበት (ኢሳ. 10፥27) የሌለና ያልተጻፈ፥ ከሩቅ ተንትቶ የመጣና ያላለውን እንዲል የተደረገ ቃል ነው። ኢትዮጵኞች ስለ ኢትዮጵያ ሲጠቅሱ እንደሚያደርጉት ሁሉ ስለ ቅባት ሲናገሩም ቃሉ ያላለውን እንዲል ማስገደዳቸው እውነት ነው። ይህ ዓይነቱ የአፈታት አካሄድ የሐሰተኛ አስተማሪዎች አንድ መታወቂያ ነው።



መጋቢ አቢ አምሻው፤ ". . . በግሌ እግዚአብሔር ስለ ምድራችን ተናገረኝ ከምላቸው ነገሮች አንዱ በ1998 በኢትዮጵያ የጴንጤቆስጤ 40ኛ ዓመት በተከበረ ጊዜ እግዚአብሔር አንድ መንፈሳዊ ሽግግርና አዲስ መንፈሳዊ ዘመን ለምድራችን ለኢትዮጵያ እንደደረሰና እንደመጣ በግልጽ ተናግሮኝ ነበር፤ መጽሐፍ ቅዱስ የ40 ዓመት ሽግግር አንድን ሂደት እንደሚያመጣ ያሳያል፤ 40 ዓመት አንድን ሂደት የአንድን ትውልድ ሽግግር የሚያሳይ ነገር ነው፤ በምድራችንም ከዚህ የጴንጤቆስጤ ጉዞ በኋላ አዲስ ነገር እንደመጣ የእግዚአብሔር ቃል፥ የእግዚአብሔር መንፈስ አሳስቦናል። . . . ኢትዮጵያ ስለሚጠብቃት ጉብኝት ስናስብ ብዙ ቅዱሳን የሚያስቡት ዛሬ ካለብን ተጨባጭ ችግሮች አንጻር ብቻ ነው የሚያስቡት፤ የእግዚአብሔር ጉብኝት ምድራችን ካለችበት የኢኮኖሚ፥ ማኅበራዊ፥ ፖለቲካዊ, መንፈሳዊ ቀውስ የሚያወጣት ጉብኝት አድርገን ብቻ ነው የምናስበው፤ በርግጥ የእግዚአብሔር ጉብኝት እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያከናውናል፤ ነገር ግን መኅበኝታ ከዚህ የሰፋ መሆኑን ከእግዚአብሔር ቃል እናስተውላለን፤ . . . በተለይ መዝ. 68፥31 . . . ይህ የኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ማንሣት በሚሆንበት ጊዜ ውጤትና ኢፌከቱ ግን ቀጣዩ ቁጥር ላይ የኢትዮጵያ እጁን ወደ እግዚአብሔር ውጤቱ ነገሥታትን ለእግዚአብሔር የሚያስዘምርና የሚያስገዛ ሁኔታ አለው፤ . . . የኢትዮጵያ መኅበኘት ለምድር ነገሥታት ወይም በአጠቃላይ ለምድር ወደ እግዚአብሔር መመለስ ምክንያት የሚሆን ትልቅ ንቅናቄ፥ ትልቅ መነቃቃት፥ ትልቅ ሪቫይቨል፥ ትልቅ ተሃድሶ እንደሚሆን ያመላክተናል። . . . በሌላ በታም ስለ ኢትዮጵያ መኅብኘት ዓለም አቀፋዊ ኢምፐሊኬሽን በመዝ. 72፥8-9 በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ ይላል፤ [ሌሎችም ይገዛሉ ይልና] . . . የዚህ መገዛት፥ የጠላቶች መመታት ምንጩ ግን የኢትዮጵያ በፊቱ መስገድ ነው፤ ከኢትዮጵያ መገዛት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይናገራል። . . . አሁን ከጴንጤቆስጤ 40 ዓመት በኋላ እግዚአብሔር አዲስ ጉብኝትን ይዞ መጥቷል፤ . . . ለዓለም፥ ለምድር የሚሆን ለእግዚአብሔር ታላቅ ክብር የሚያመጣ መንፈሳዊ መነቃቃት እንደሚሆን ነው የማምነው።"

እንደ እኒህ መጋቢ አነጋገር እግዚአብሔር በየ40ው ዓመት አዳዲስ የጉብኝት ፈሊጥ እየቀያየረ ይመጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 40 ዓመታት የፈጁ ነገሮች ኖረው ያውቃሉ። 40 ዓመታት እየጠበቀ ግን እግዚአብሔር አዳዲስ ክስተቶችን ሲያመጣ አልታየም። የኢትዮጵያ ጉብኝት መነሻ ደግሞ አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት 1958 ሆኖ አሁን ሁለተኛው 40 የተገባበት ነው። ቀጣዩ በ2038 ይሆናል። እንዲህ ከሄድን 40ን ብቻ ሳይሆን 3ንም፥ 7ንም፥ 12ንም፥ 24ንም፥ 50ንም፥ 70ንም፥ እንደ ዶቃ እየቀጣጠልን የቀናትና ዓመታት ሂሳብ ልንጽፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ሳይሆን አጎዛዊ ጥንቆላ ነው።

ሌላው እኒህ መጋቢ ያነሡት ስሕተት የኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ማንሣት (ማንሣት የሚለው ሳይተነተን) ዓለምን አስከትሎ ወደ እግዚአብሔር የሚያመጣ ጉዳይ መሆኑ ነው። ነገሥታት እንዲዘምሩ፥ የእግዚአብሔር ጠላቶች አፈር እንዲልሱና በፊቱ የተገዙ እንዲሆኑ መጀመሪያ ኢትዮጵያ እጆቿን መዘርጋት አለባት። የዓለም መኅብኘትና ለግዛታዊው መልኳ መቀየር አንድና ብቸኛ ቅድመ ሁኔታ የኢትዮጵያ እጆቿን መዘርጋት ነው። ኢትዮጵያ እጆቿን ካልዘረጋች እነዚህ ነገሮች አይፈጸሙም። ይህ እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤልን ወይም እንደ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያንን ሳይሆን ኢትዮጵያን ያማከለ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ነው።

መዝ. 68፥32 እኮ ይቀኛሉ፤ ይዘምራሉ ብሎ ስለ ወደ ፊት ወይም ስላለንበት ዘመን ወይም የኢትዮጵያን እጅች መዘርጋት 'ኢፌክት' እየተናገረ አይደለም። ይቀኛሉ የሚል ትንቢት ሳይሆን፥ 'ተቀኙ፤ ዘምሩ' ነው የሚለው። የትንቢት ሳይሆን መዝሙሩ የተዘመረበት ወይም የተጻፈበት ዘመን 'የአሁን' ግስ ነው። በመጋቢው ይህ ጥቅስ የመጨረሻው ዘመን ጉዳይ በኢትዮጵያ ዙሪያ እንዲሽከረከር ማጠፊያና መዘውር ተደርጎ የዓለምን ወደ እግዚአብሔር መምጣት በእርሷ እርምጃ ላይ እንዲደገፍ ሆኗል።

መዝ. 68፥31 ኢትዮጵያ ካልተነበኘች እግዚአብሔር የሚያደርገው እንደማይኖር ተደርጎ በኢትዮጵኞች ያላለውን እንዲል ያስገደዱትና ያስጨነቁት አንድ ጥቅስ ነው። የኢትዮጵያ መነበኘት ለምድር ወደ እግዚአብሔር መመለስ ብቸኛው ምክንያት ሆኖና አገሪቱም የዓለማችን የልብ ትርታ ሆና ቀርባለች።

ክርስቲያን ኢትዮጵኞች ቤተ ክርስቲያንን በኢትዮጵያ ለውጠው ኢትዮጵያን የክርስቶስ ሙሽራ አድርገው ሲያቀርቡ ደንታም ጎፍረት አይሰማቸውም። የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች እንደ ሌሎቹ ክርስቲያኖች ሁሉ የክርስቶስ አካል የሆነችው የኩላዊዋ ቤተ ክርስቲያን አካል ብልቶች ናቸው እንጂ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፥ ቤተ ክርስቲያንም ኢትዮጵያ አይደሉም። ይህ አይጥፋብን። መልከዓ ምድራዊ ክልልን ወይም አንድን ብሔር የፍጻሜ ዘመናት የክርስቶስ ሥራ መሪ ተዋናይ አድርጎ ማቅረብ መጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይም አዲስ ኪዳን የማያሳየው ትምህርት ነው።



ቄስ ዶ/ር ቶሎሳ ጉዲና፤ "እግዚአብሔር ስለምድራችን ብዙ ተናግሯል፥ በነቢያት ባለፉት አባቶቻም ብዙ ተናግሯል፤ በዘመናችንም እየተናገረ ነው፤ ለኔ በጣም እጅግ አርጎ የነካኝና እግዚአብሔር ይኼ ቢሆን ይኼ ይሆናል የሚል ከ2000 ዓመተ ምሕረት በነጮች አቆጣጠር ማለት ነው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንስሐ ቢገባ፥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ንስሐ ብትገባ፥ ቤተ መንግሥት፥ ቤተ ከህነት፥ ቤተ ክርስቲያን ንስሐ ቢገቡ በኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት የነበረው መርገም፥ ሰቆቃ፥ ድኅነትና ልመና እንደሚነሣ፥ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ምድሪቷን፥ ኢኮሎጂዋን፥ ኢኮኖሚዋን፥ ፖለቲካዋን፥ ሁሉን ነገር አንድም ሳይቀር፥ አየሯን አፈሯን እንደሚፈውስ፥ ያን በማድረግ እግዚአብሔር በምድሪቷ ላይ ከሁሉ የሚያደርግ ሞገስን እንደሚሰጥ፥ በቤተ መንግሥት ላይ ሞገስ ይመለሳል፤ በቤተ ከህነት ላይ ሞገስ ይመለሳል፤ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሞገስ ይሆናል፤ በዩኒቨርሲቲዎች፥ በትምህርት ተቋማት ላይ ራእይና ሞገስ ይሆናል። ሁሉ ነገር ከሞገስ ነው፤ ሞገስ ከሌለ ምንም ዋጋ የለውም፤ እና እግዚአብሔር ያን አደርጋለሁ አለ።

ከዚያ በኋላ የምድሪቷ ፍሬ በዓለም አካባቢ የተከበረና የሚፈለግ እንደሚሆን፥ ወጣቶች ታላላቅ ቢዝነስ ፒፕል፥ ራእይ ያላቸው እንደሚሆኑ፥ በምድራችን ውስጥ ብዙ ማዕድን እንዳለ፥ እግዚአብሔር እስካሁን ድረስ ያን የጠበቀው እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች እስከሚነሱ ድረስ እንደሆነ፥ እነሱ ይነሣሉ፤ ወጣቶች የሆኑ በሚሊየን የሚቆጠር ገንዘብ እንደሚነግዱ፥ ብዙ ካረንሲ፤ በምድራችን ላይ በረከት እንደሚሆኑ፥ በዘመናት ያጣነው፥ ስማችን የቆሸሸው፥ በሌሎች ዘንድ የቀለለው፥ ፓስፖርታችን የቀለለው፥ ይኼ ሁሉ እግዚአብሔር ክብርን እንደሚሰጠን፤ እና ሕዝቡ ንስሐ ከገባ፥ ሕዝቡ ወደዚያ ከተመለሰ የሚል ነው ጌታ የተናገረኝ። ከዚህ አንጻር ነው ብሔራዊ የንስሐና የዕርቅ ጊዜ ያዘጋጀነው በ2003። . . . ያ ትልቅ ሥራ ሠራ፤ ግን የምንፈልገውን ያህል አልሠራም፤ ምክንያቱም የሚፈለጉቱ ንስሐ አልገቡም፤ ተራ ሕዝቡ ጮኸ በእግዚአብሔር ፊት፤ ተራ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት ፊቱን ደፋ፤ ሕይወቱን ሰጠ፤ ሕዝቡ የተባረከ ምዕመን ነው፤ . . . በአመራር ነው ኢትዮጵያ የተጎዳችው እንደ ማንኛውም 3ኛ ዓለም፤ እግዚአብሔር ደግሞ ያን የሚያስተካክለው ውስጣቸው የተስተካከለ ሰዎች ሲነሡ ነው፤ . . ስለዚህ፥ ጌታ የሱስን የሚያውቁ ብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ እግዚአብሔርን በመፍራት ቢመላለሱ፥ ቤተ ክርስቲያን ብትመላለስ ይቺ ምድር ለኛ ትንበረከካለች ባንድ ጊዜ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ያን ለማድረግ ነው ቤተ ክርስቲያንን በምድር ላይ የተወው፤ ይኼ ነው ጌታ የተናገረኝ።"

ከመጨረሻው ሐረግ ልነሣ፤ 'ቤተ ክርስቲያን ብትመላለስ ይቺ ምድር ለኛ ትንበረከካለች ባንድ ጊዜ።' እነማን ናቸው 'እኛ' የተባሉትና ምድሪቱ የምትንበረከከላቸው? ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የተተወችው እውነት ምድርን ለማንበርከክ ነው ወይስ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ለመስበክ? ምድርን ማንበርከክ የተጻፈላትና የታዘዘችው ትምህርት ነው? አንድ ቀን ጉልበት ሁሉ ለአብ ክብር ለክርስቶስ እንደሚንበረከክ እናውቃለን። ለኛ ማለት ግን ተናጋሪውን እና ተናጋሪው የሚወክሏቸውን ሰዎች ከክርስቶስ ጋር አብሮ መንበርከኩን የሚጋሩ የሚያደርግ ነው።

የእኒህ ቁስ ትንበያ ቢሆንታዊ (conditional) ነው። ቢሆንታውም ሕዝቡ ንስሐ ቢገባ ሌላው ነገር ሁሉ ይሆናል የሚል ነው። ከንስሐው በኋላ የሚሆኑትን ነገሮች ስቆጥር ሥጋዊውና ምድራዊው በረከት መንፈሳዊውን በረከት በፎርፌ አሸንፎታል። በመጀመሪያ መንፈሳዊው የቱጋ እንዳለ ፈልጋችሁ ለማግኘት ሞክሩ። ቢሆንታው የሕዝቡ ንስሐ ቢሆንም፥ ጥሪውን ተቀብሎ ሕዝቡ ንስሐ እንደገባ ቢነገርም፥ መሪዎች ንስሐ ስላልገቡ በረከቱ ገና እንደተያዘ ነው። 'የሚፈለጉቱ ንስሐ አልገቡም' ተብሎአል። ከቀድሞም የንስሐው ዒላማዎች መሪዎች ነበሩ ማለት ነው። የሚመስለው ሕዝቡ ሳይሆን መሪዎች ንስሐ ቢገቡ የበረከቱ አሸንዳ እንደሚለቀቅ ነውና ዒላማን ስቶ ሕዝቡን ማንገላታት ባላስፈለገም ነበር። መግባት የተፈለገው ወደ ቤተ መንግሥት ነው። ሕዝቡ፥ 'ተራ ሕዝብ' ተብሎ ንስሐውም አቅም ያነሰው ሲደረግ፥ አልሆነም እንጂ፥ የመሪዎች ንስሐ ግን ጣሪያ ዘለል ክብር ተሰጥቶታል።

የመሪዎች ንስሐ መልካም ነው፤ ለራሳቸው፥ ለነፍሳቸው። መልካም መሪዎች ሲመሩ ለሕዝቡ መልካም ይሆናልና፥ የተጋቦት ክልላቸው አድማስ ሰፊ የመሆኑን ያህል ልዩነት የመፍጠር አቅማቸውም ያን ያህል ይተልቃልና፥ ይህም መልካም ነው። ነገር ግን መሪ ንስሐ ስለገባ ሕዝብ ንስሐ ይገባል፥ ይለወጣል፤ አገር ትቀደሳለች ማለት ትክክል አይደለም። መሪ በሕዝብ ውስጥ እንጂ ሕዝብ በመሪ ውስጥ አይኖርም። መሪ የሚወጣበት የሕዝቡ ንስሐ በተከበረ መልካም ነበር።

እምነትን ከቤተ መንግሥት መጀመር ደግሞ ብሔራዊ ሃይማኖትን ነው የሚፈጥረው። ክርስትና ከአናት ሲጀምር ምን እንደሚመስል በቆስጠንጢኖስ ዘመንም በአገራችን የክርስትና ታሪክም የታየ ነው። ይህ ብሔራዊ ሃይማኖትን የመፍጠር አካሄድ አሓዳዊ ማኅበረ ሰብን መፍጠር ይችል ይሆናል፤ ሃይማኖትንም ሊፈጥር ይችላል። መንፈሳዊ ለውጥን ግን አይደለም። ብሔራዊ ሃይማኖት ፍጻሜው እምነት ሳይሆን ፖለቲካ ነው። ብሔራዊ ሃይማኖት ፖለቲካ እንጂ እምነት አለመሆኑን ከዘመናችን ሃይማኖታዊ መንግሥታት ወይም ክርስትና ራሱ መንግሥታዊ ሃይማኖት ሆኖባቸው ከሚያውቁባቸው አገሮችና ዘመናት መልክ መረዳት ይቻላል። ይህ የዶሚኒየን ቲዮሎጂ አንድ ገጽታ ነው።

'በቤተ ከህነት ላይ ሞገስ ይመለሳል፤ በቤተ ክርስቲያን ላይ ሞገስ ይሆናል' ተብሎአል። ቤተ ከህነት ግልጽ ባይደረግም ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖትን ይመስላል። መሠረታዊና የተሰመረበት የአስተምህሮ ችግር እንደሌለ ሁሉ በደፈናው ሞገስ ይሆናል ተብሎአል። ይህ አሳብ በሌላ ተናጋሪም ተጠቅሶአል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትና ውስጣዊ ንጽሕና ወደ ጎን ተጥሎ ውጪያዊ ሞገስ በመሪዎች ንስሐ ከተገኘ ይህ የሕይወት ሳይሆን የሹመት ሞገስ ነው።



መጋቢ ተመስገን ብርሃኑ፤ ". . . እኔም ወደ ጌታ መጥቼ የእግዚአብሔር መንፈስ በኔ ላይ አርፎ መልእክቶችን በውስጤ ማስተላለፍ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የምረዳው እና ጌታ የተናገራቸው እጅግ ብዙ ናቸው፤ እኒያን ሁሉ አሁን በአጭር ጊዜ መናገር አልችልም። ነገር ግን 77 ዓመተ ምሕረት ላይ በሕይወቴ ሆኖ ከሚያቀው እና ከተለማመድኩት በተለየ ሁኔታ እግዚአብሔር ወደኔ መጥቶ ሁኔታ ስመለከት እርሱን ብገልጽ ይሻለኛል። እና በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር የተናገረኝ ነገር፣ ትልቁ ኢትዮጵያ ሆኖ በማያውቅ ታላቅ መንፈሳዊ ባርኮት እባርካታለሁ፤ ከዚያም በኋላ በታላቅ ምድራዊ በረከት እባርካታለሁ፤ ከዚያ በፊት ግን በምድሪቱ ላይ የገዘፉትን ለሥራዬ ዕንቅፋት የሆኑትን ከምድሪቱ ላይ አነሣለሁ፤ ከሚመጣው ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተነሣ እጅግ ብዙ የወንጌል ሠራዊት ከምድሪቱ አስነሣለሁ፤ በልዩ ልዩ ዓለማት በድንቅና በተአምራት እጠቀምባቸዋለሁ፤ እጅግ ብዙ ሰዎች በምድሪቱ ከማደርገው ከፍተኛ ለውጥና በረከት የተነሣ ወደ ምድሪቸው መጥተው ለማየት ወረፋ ይዘው ይጠባበቃሉ፤ የምድሪቸውም አፈር ለመድኃኒት እስኪፈልጉት ድረስ አደርጋለሁ። አስቀድሞ ግን ታላቅ ጨለማ፣ ዓይን ቢወጉ የማያሳይ ድቅድቅ ጨለማ ይሆናል፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ትውልድን አዘጋጃለሁ፤ ዕንቅፋትንም አስወግዳለሁ። . . . ጌታ ከመምጣቱ በፊት የሚዴታ እንደሚሆን ሙሉ እምነቴም ልቤም በዚህ የተሞላ ነው።"

እኒህ መጋቢ ይህን ትንቢያ ከጌታ መምጣት በፊት እንደሚፈጸም አስረግጠው ገልጠዋል። ያውም የግዴታ ተብሎ ነው የተነገረው። ይህ ካልተፈጸመ ጌታ አይመጣም ማለት ነው። ለጌታ ዳግም መምጣት ከተጻፈው ቃል ሌላ ቅድመ ሁኔታ መፍጠር የኛ ተግባር ከሆነ ጌታ ጨርሶም ላይመጣ ነው። ምክንያቱም እገሌም እገሊትም ይህ ካልሆነ፣ ይህ ካልተፈጸመ ጌታ አይመጣም እያሉ ሊያዘገዩት የፈለጉትን ያህል ሊያራዝሙት ይችላሉ። ደግነቱ ጌታ የሚመጣው ወይም የሚዘገየው በተንባዮች ሙቀት ከፍታና ዝቅታ አለመሆኑ ነው። ጌታ እስካሁን ያልመጣው የሚመጣበት ጊዜ ስላልደረሰ ነው እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ መደረግ ያለበት አንድ አጀንዳ ስለቀረ አይደለም። የተጻፈልን ነገር ቢኖር የዘገየው ሰዎች ይድኑ ዘንድ ወዶ በመታገሱ ነው። ይህ ማለት አሁንም የምሥራቹ ቃል ለምድር ሁሉ ይነገር ዘንድ ነው።

ጌታ የሚመጣበትን ቀኒቱን አስልተው የተናገሩ ሰዎች ኖረው ያውቃሉ። ሁሉም የተሳሳቱ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ነበሩ። ለጌታ መምጣት ጌታ ከተናገረው ነገር በቀር የግዴታም የውዴታም ብለን በቃሉ ላይ ቃል መጨመር እርግማንን መጥራት ነው።

ወረፋ ይዞ መጠባበቁ ከምን የተነሣ እንደሆነ ባይታወቅም በምድሪቱ የሚደረገውን ለማየት ወረፋ መያዝ አገሪቱን እጅግ ብርቅዬ ያደርጋታል። የኢትዮጵያ ምድር አፈር ለመድኃኒት እስኪፈለግ ማለት ይኼ ገዳምና ጠበል ሲሄዱ ሰዎች 'እምነት' እያሉ የሚያመጡት አፈርና ጭቃ መሰለ። አንዳንዶች ይቀቡታል፤ አንዳንዶች ይበሉታል። አፈሩን ነው የሚበሉት፤ መድኃኒት ነው ብለው ነው የሚበሉት። ስለ አፈር መቀባት ስንነጋገር አንድ ሰው፥ 'እንዴ!? ንዕማን እንኳ ሁለት የበቅሎ ጭነት አፈር ከእስራኤል አልወሰደም?' አለኝ። ንዕማን ያደረገው ነገር ተጻፈ ማለት እኮ እኛም ያ ከጣዖት አምላኪ አገርና ሕዝብ መካከል የመጣ ሰው ያደረገውን እናደርጋለን ማለት አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ (በተለይም የብሉይ ኪዳን) ሰዎች ያደረጓቸውን ነገሮች ሁሉ ማድረግ አለብን ማለት አይደለም። ከኖረብን ከቃዮን ጀምረን ታሪክ ልንደግም ነው። የተደረጉ ነገሮች ሁሉ የሚደረጉ ናቸው ማለት አይደለም። የስሕተት ትምህርቶች ሲጀመሩ ብዙ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካዊ ጽሑፎች ምሳሌ በመውሰድ

የሚጀመሩት እዚያ የተደረጉት ነገሮች ዛሬና እዚህም መደረግ አለባቸው ከሚሰኝ ስሕተት ነው።



መጋቢ መስፍን መሉጌታ፤ "በኢትዮጵያ ውስጥ እንግዳና የልተለመደ ሪቫይቫል እንደሚነሣ ተናግሮኛል። የዚህ የእግዚአብሔር ሪቫይቫል ወይም የእግዚአብሔር እጅ መነሣቷ ትልቅ የሚያደርገው የጽድቅን ተጽዕኖ ማምጣት ነው። መቼም ኢትዮጵያ ሁሉ ይድናል ብዬ አላምንም፤ ግን ያ የሚመጣው ሪቫይቫል፥ የሚመጣው የእግዚአብሔር ክብር በምድራችን ላይ የጽድቅ ትጽዕኖ ያመጣል። እና የተባለላት፥ አንደኛ ኢትዮጵያ በሽተኛነቷ በሦስት ነገር ነው፤ እስፒሪቻቿ በሽተኞች ነን፤ መንፈሳዊ ነገራችን፤ ኢኮኖሚክሊ ደግሞ ያን ያህል በሽተኞች ነን፤ ሌላው ደግሞ ሥጋዊም ቢሆን በጣም ቡብዙ የተጎዳ አገር የኛ ነው፤ እነዚህ ሦስቱ። የእግዚአብሔር መንፈስ ሲመጣ የመጀመሪያው የሚፈውሰው እኔን እንደገባኝ ወይም መንፈስ ቅዱስ እንደተናገረኝ መንፈሳዊን ነገር፥ እርግማንን ይሰብራል። ከእያት ከቅድመ አያቶቻችን፥ በነገሥታቶችም ምክንያት በዚህች ምድር የብዙ ቅዳሳን የብዙ ሕዝብ ደም ፈሷል፤ የዚህ የደም ጩኸት ወደ እግዚአብሔር ቀርቧልና ይኼ እርግማን በትውልድ ላይ መጥቷል፤ ይኼን እርግማን እንደሚሰብር እግዚአብሔር በዚህ ጀነሬሽን፥ በዚህ ትውልድ መካከል እግዚአብሔር ይሄን ተናግሮኛል፤ ይሰበራል ብሎኛል። . . . ኢኮኖሚካሊም እርግጠኛ ሆኜ ምናገረው፥ እሩቅ አይደለም፤ እግዚአብሔር በቅርብ ታሪክ እንደሚለወጥ እየደጋገመ እየተናገረ ነው። . . . ኢኮኖሚያችን ይፈወሳል፤ እሩቅ አይደለም። እስፒሪቻሊ ይፈወሳል፤ ሥጋዊ ማንነታችን እግዚአብሔር በቅርብ እንደሚለውጥ ደጋግሞ ተናግሮኛል። ፕሊዝ፥ እንዴት እንደምገልጽላችሁ አላቅም፤ አንድ ያልተለመደ ነገር፥ ያልተጠበቀ ነገር እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ ያደርጋል። ይኼን እግዚአብሔር ተናግሮኛል። እግዚአብሔር ይህንን ነገር ማድረግ ጀምሯል፤ አይቻለሁ በዓይኔ።"

'እንግዳና ያልተለመደ ሪቫይቫል' ማለት ከዚህ በፊት ያልሆነ ወይም ሆኖ የማያውቅ ማለት ይመስላል። ምናልባት ከዓይነቱ ይልቅ መጠኑን ወይም ሁለቱንም ለማመልከት ይሆናል። ኢትዮጵያ ሦስት በሽታዎች ይዟታል፤ መንፈሳዊ በሽታ፥ ኢኮኖሚያዊ በሽታ፥ ሥጋዊ በሽታ። ሦስቱም በሽታዎች በዚህ ትውልድ ውስጥ የሚጠፉ ናቸው። ይህ የመጣው ባለፉት ትውልዶችና መሪዎች ምክንያት በእርግማን ሲሆን አሁን እርግማኑ ተሰብሮአል። የትውልድ እርግማን ወይም generational curse የሚሉት የተቃወሰ ትምህርት በቃል-እምነት አስተማሪዎች ዘንድ የተስፋፋ የስሕተት ትምህርት አለ። ይህ ትምህርት ክርስቲያን ክርስቲያን ከሆነም በኋላ የቀደመ ትውልድ እርግማን ባለ ዕዳ እንደሆነ የሚያስተምርና በፍርሃት እየተሳቀቀ እንዲኖር የሚያስገድድ ትምህርት ነው።

አንድ ትውልድ የሚዘራውን እንክርዳድ ቀጣዩ ትውልድ ማጨዱ እርግጥ ነው። የዚህ ትምህርት ቀውስ ግን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆነን እና ኩነኔ የሌለበትን ክርስቲያንም የዚህ ትብታብ እስረኛ ማድረጉ ነው። እርግማኑ ለመሰበር ከክርስቶስ መስቀል ጀምሮ እስከ ዛሬው ዘመን ጊዜ የመውሰዱ አስፈላጊነትና የወሰደበት ምክንያት ግልጽ ባይሆንም ይህ ዘመን የተመረጠበት ትምህርትም የዚያኑ ያህል እንግዳ ነው። በኔ ዘመን በኔ ትውልድ ይህ ይፈጸማል፤ ተጀምሮአል

የሥጋዊ በሽታ ፈውስ ጅምላ ሆኖ መቅረቡና ይህ ፈውስ የሥጋዊ ማንነት መለወጥ መሆኑ አሻሚ ቋንቋ ነው። በሽታ ሁሉ ጠፍቶ ሐኪም ቤቶች ቤተ ክርስቲያን ሆስፒታሎች መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሲሆኑ ሌላው ካዩት ጋር ይህ ይስማማል።

ከአዳም ውድቀት ጀምሮ ኩነኔና ሞት በምድር ላይ አለ። ወደ ኋለኛው አዳም ወደ ክርስቶስ ውስጥ መግባታችንም አዲስ ፍጥረት አደረገን እንጂ አዲስ ሥጋ አላደረገንም። ስለዚህ በዚህ ሥጋ ውስጥ ሆነን እንኖራለን፤ እንቃትታለን፤ እናቃስታለን፤ እንሞታለን። እግዚአብሔር ይፈውሳል? እውነት ነው፤ ይፈውሳል። በሽታን ከኢትዮጵያ ክልሎች ሁሉ ጠራርጎ ያጠፋል? ውሸት ነው! አልተጻፈም!



ወንጌላዊ ሉቃስ ወ/ፃድቅ፤ "እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ላይ ሊያመጣ ያለው ጉብኝት በእግዚአብሔር መንፈስ ብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደተናገሩት እኔም በእግዚአብሔር መንፈስ እንደምረዳው፥ በሁለት ዋና አቅጣጫዎች የእግዚአብሔር ጉብኝት ወደ ምድራችን ይመጣል። አንደኛው፥ ከፍተኛ የወንጌልን ሥራ ከመሥራት አቅጣጫ የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ የሚያደርግ ከፍተኛ ክብርና ኃይል እግዚአብሔር በአብያተ ክርስቲያናት ላይ የማምጣት፥ ይህን ሥራ መሥራት የሚችሉ አገልጋዮችን በማስነሣት ሕዝቡን ማንቃት አንደኛው አቅጣጫ ነው። ሁለተኛው፥ አገሪቷን ከማሰልጠን፥ ከማበልጸግ አቅጣጫ በነዚህ ሁለት አቅጣጫዎች እግዚአብሔር ምድሪቷን ይሰበኛል ብለን እንጠብቃለን። . . . አሁን በኢትዮጵያ ላለው ጉብኝት መጀመር ምክንያት የማደርገው ወይም ምልክት አድርጌ በዋናነት የምወስደው እግዚአብሔር እንደ እርሱ [እንደ ሙሴ] ያስነሣቸው ሰዎች አሉ። እዚህም እዚያም ያስነሳቸው ሰዎች አሉ፤ ጅምር ሥራዎችን እንመለከታለን፤ እግዚአብሔር ከነዚህ ሰዎች ጋር ሆኖ ስለሆነ ምድሪቱን የሚጎበኘው የነዚህ ሰዎች መነሣት ዋናው ምልክት ነው። ከዚህም ባሻገር አገሪቱን ከማሰልጠን አቅጣጫ የተለያዩ ዘሮችን የሚዘሩ ሰዎች ተነስተዋል፤ ዘሮች እየተዘሩ ነው፤ ነገ ፍሬ መሆን የሚችሉ ነገሮች ናቸው። ዋናዎቹ ምልክቶች ምላቸው እነዚህ ናቸው።"

አገሪቱ መሰልጠኗ መልካም ነው፤ ግን ይህ ከሰማያት እንደወረደ ድንቅ ነገር የሚታይ አይደለም። እኛ ብቻ አይደለንም፤ ዓለም በሞላዋ እየሠለጠነችና መንደር እየሆነች ስለሆነ ይህ ብቻውን ሊያስደንቅና ጉድ ሊሰኝ የተገባው አይደለም። ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ ስልጣኔ አስመዝግባ ታውቃለች፤ ተመልሳ ጨለማ ውስጥ ገብታም ታውቃለች። አሁን ከኋላ ተርታ ብንሆንም እንደ ብዙዎቹ የዓለም አገሮች እመር ብንል አዲስ መሆን የለበትም።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናነኛቸው አማኞችና አገልጋዮች ክርስቶስ በዕድሜያቸው ዘመን ውስጥ ተመልሶ እንደሚመጣ በመረዳት ወንጌልን የኖሩና የተናገሩ ነበሩ እንጂ እስራኤል የተባለች መኖሪያ አገራቸው ዙብና ሮምን እና አቴናን ስትመስል ማየትን የሚቋምጡ አልነበሩም። ለክርስቲያን ዘመናዊነትን እንደ መጨረሻ መድረሻ ማየት ውድቀት ነው። መድረሻችንና ግባችን ክርስቶስን መምሰል እንጂ ዘመናዊነት አይደለም። ሥልጣኔን ማጥላላቴ አይደለም። ሥልጣኔ መልካም ነው። ዘመናዊነት ግን ለሰው ልጆች የቸገር መቅረፊያ እንጂ መፍትሔ አይደለም እያልኩ ነኝ። አንድ ቀን ዘመናዊነቱ ከዘመናዊቱ ዓለም ጋር በእሳት እንደሚጠፉ ቃሉ በግልጽ ያስረዳል።

ምዕራባዊው ዓለም አሁን ድኅረ ዘመናዊ ዘመን ላይ ደርሶአል። ዙብኖ ዘመናዊነትንም አልፎአል ማለት ነው። የምዕራቡ ዓለም ድኅረ ዘመናዊ ብቻ ሳይሆን ሌላ መታወቂያና መጠሪያው፥ 'ድኅረ ክርስቲያን' የሚልም ነው። ለምዕራቡ ዓለም ሥልጣኔ መሠረት የጣሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና ክርስቲያናዊ እሴቶች አሁን ተገፍተው ከመንገዱ ወጥተዋል። ጋጠ ወጥነትና ማን አለብኝነት፥ ግብረ ወጥነትና ዝቅጠት፥ መንፈሳዊ እሴቶችን ማጣጣልና እግዚአብሔርን መጥላት የት ነው ያለው ቢባል በዘመናዊው፥ በድኅረ-ዘመናዊውና በድኅረ ክርስቲያኑ ባሕል ውስጥ ነው። ዘመናዊነት መልካም ቢሆንም መፍትሔ ባለመሆኑ ኢትዮጵያ ከዘበኝነትና

ከበለጠገች የከበረች አድርገን መመልከት የዋኅነት ነው። መንፈሳዊ ዝቅጠት እና ዘመናዊነት እያጠባ የሚያሳድጋቸው ባሕሎች በአገራችን እየታዩና እየተስተናገዱ አይደለም ማለት እንችላለን? አንችልም።

ኃጢአት ዕድሜው ከሰው ፍጥረት ጋር እኩል ነውና ኃጢአት ሁሉ የዘመናዊነት መዘዝ ነው ማለት አይደለም። ዘመናዊነት ግን ኃጢአትን ቅልል አድርጎና ሸላልሞ እያቀረበልን መሆኑን አንሳት። ድኅረ ዘመናዊው ባህል ኃጢአትን መናቅን እንደ ጅልነት፥ መቃወም ደግሞ እንደ ድፍረ ትና ጥቃት አድርጎ እያየና እያሳየ መሆኑን ላለማየት የማይፈልግ ካልሆነ በቀር ማንም ያየዋል። ግብረ ሰዶማዊነት ሕጋዊነትን ከተቀዳጀ በኋላ በአሜሪካ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት የሚቆሙ ሰዎች ግልጽና ስውር ስደትን መቀበል ጀምረዋል።

በቅርብ በአገራችን አንዲት ልጃገረድ እንሰሳነት በተጠናወታቸው ወጣቶች በቡድን ስትደፈር ቤተ ክርስቲያን ምን አለች? በግብረ ሰዶም ላይ ከአሁኑ የጸና አቋም እያሳየች ናት? መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጥላሉና የሚያጣጥሉ ባሕሎችን ለመቃወም መንፈሳዊ ድፍረት አላት? ሐሰተኛ ነቢያትና የሰባኪ ካባ የለበሱ ጠንቋዮች በመድረክ ሲቦርቁና እንደ አሸን ሲፈሉ ሃይ የማለት ድፍረት አላት? ኢትዮጵኝነት ራሱ የሐሰት ትምህርት መሆኑን አስተውላ ይሆን?

እኒህ ወንጌላዊ እግዚአብሔር ከዚህ በኋላ የሚያደርጋቸው ነገሮች የቀደሙትን የጥቂቱን ቀን ነገሮች እንደ ዘካርያስ ዘመን (ዘካ. 4፤10) እንድንረሳና እንድንንቅ የሚያስገድዱን ነገሮች ይመስላሉ። ኢትዮጵኞች በቅርቡ የሚሆኑትን ነገሮች ሲነግሩን ጆሮ ሰጥተን ብንሰማቸው ገባሬ መስተንክር ወድንቅ ወተአምር የሆኑ ሰዎች በቅርብ ቀናት የሚነሡ ስለሆነ ያሉን አገልጋዮች ድንክ መስለው እንዲታዩን እያደረጉን ናቸው። 'እንደ ሙሴ ያስነሣቸው ሰዎች አሉ' ከተባለ እውነትም የዓለም ሕዝብ ወደኛ አገር ለመምጣት ወረፋ ቢይዝ አያስገርምም።



መጋቢ ፃድቁ አብዶ፤ "በብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ስለዚህች አገር ተናግሮአል፤ በቃሉ ውስጥ ተናግሮአል፤ . . . ከዚያ ቀጥሎ እግዚአብሔር ለዚህች ምድር የተናገራቸው ነገሮች አሉ፤ እኔ ጌታን የተቀበልኩት የ16 ዓመት ወጣት በነበርኩበት ጊዜ ነው፤ ከዚያን ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር የተናገራቸው የሆኑ ነገሮች አሉ፤ ያለፍንባቸው ችግሮችም እንደዚሁ። እኛ ኢትዮጵያውያኖች እንግዲህ በብሉይ ኪዳንም ታሪካችን ጥሩ ነበር፤ ልክ እንደ ግብፃውያን፥ እንደ ግሪካውያን፥ ጥንታዊ ሲቪላይዜሽን እንደቀመሱት ሕዝቦች ጥንት ጎናና የነበሩ አገሮች አሉ፥ አሁን ደግሞ ትንሽ ሆነዋል፤ እኛም ጥንት ትልቅ ነበርን አሁን ብዙ ነገር ተፈራርቆበናል፤ ግን እግዚአብሔር ያንን መልሶ ሳይሰጠን የክርስቶስ ምጽአት ይመጣል ወይ የሚል ጥያቄ አለብን። . . .[ስለ ቻይና መንበኘት ተነግሮ] . . . እግዚአብሔር ይህቺንም ምድር፥ ለርሷ የተናገራትን መልካም ነገር ወደሚሆንበት ዘመን ሊያመጣት ሚታዩ ነገሮች አዝማሚያዎች ሁሉ አሁን ወደዚያ እየሄዱ ናቸው። አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ጉብኝት ወደዚህች ምድር ተመልሶ በሁለንተናዊ መልኩ፥ ኖት በኢኮኖሚ በፋይና[?] በሌላ መልኩ ሳይሆን በተሟላ መልኩ፥ ሰው ሀብት ኖሮት ነፍሱ ባዶ ቢሆን ዋጋ የለውም፤ ግን እግዚአብሔር በተሟላ መልኩ ያንን ለዚህች ምድር ያረጋል ብዬ አስባለሁ።"

እኒህ መጋቢ፥ 'አስባለሁ' ስላሉ የተናገሩት ከትንበያ ይልቅ አስተያየትና ግምት ይመስላል። ከኢትዮጵኝነት አንጻር ሲታይ ግን ተምኔታዊ ትንበያ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን በብሉይ ኪዳን ጥሩ ታሪክ ነበረን? በእውነቱ አልነበረንም። በትውፊት ብንሄድ፥ ትውፊቱ በ13ኛ ምዕት ዓመት የተፈጠረ ውሸት ነው እንጂ፥ እውነት ኖሮ ቢሆን እንኳ የታቦት ሰራቂዎች ነን እኮ! ይህ አንገት የሚያስደፋ ወንጀል እንጂ ጥሩ ታሪክ የሚባል አይደለም። ደግነቱ የክብረ ነገሥት ታሪክ የፈጠራ መሆኑ ነው።[18] በቃሉ ከሄድን ደግሞ አይሁድን ለብቻችንም ከግብጽ ጋር ወግነንም የወጋን ሰዎች ነን። ወራሪነት ጥሩ ታሪክ አይደለም። ከዚህ ሌላ የባቢሎን ቅኝ ተገዢዎች ነበርን። ከባለ ሚሊዮን ሠራዊት ወራሪነት ወደ ቅኝ ተገዢነት። እነዚህ አኩሪ ታሪኮች አይደሉም። ትልቅ ነበርን? ነበርን። በብሉይ ኪዳን ታሪካችን ጥሩ ነበር? እኔ ካነበብኩት ብሉይ ኪዳን ጥሩ ታሪክ አላየሁም። ይሁን፤ ጥሩ ነው ቢባል እንኳ በዱሮው 'ጥሩ ታሪክ' አሁንም ትሩፋት ይመዝብልንና ኢትዮጵያ ትበልጽግልን ማለት ይቻላል? የለም፤ አይቻልም።

'እንደገና ባለ ታሪክና ባለ ዝና ሳንሆን የቀድሞውን ክብር መልሶ ሳይሰጠን የክርስቶስ ምጽአት ይመጣል ወይ?' ብሎ መጠየቅ ራሱ ነውር ነው! የእግዚአብሔር ክብር ተመልሶ ወደዚህች አገር ይመጣል ማለት የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ እስራኤል የተናገሩትን ትንቢት ወስዶ 'እስራኤል' የሚለውን ስም 'ኢትዮጵያ' ብሎ ለውጦ አዲስ ትንቢት መጻፍ ይመስላል። የክርስቶስን ምጽአት ከኢትዮጵያ ገናናነት ጋር ማቆራኘቱ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና አሳችነት ነው። ኢትዮጵያ ገነነችም አልገነነችም ክርስቶስ ይመጣል።

የክርስቶስ የቀድሞ አመጣጡ ከኢትዮጵያ ጋር ቅንጣትም ግንኙነት እንዳልነበረው ሁሉ ሁለተኛው ምጽአቱም ከኢትዮጵያ ጋር ቅንጣትም ግንኙነት አይኖረውም። የራሳችንን ዋጋ ለማናር ብለን የክርስቶስን ምጽአት ከኢትዮጵያ በረከትና ጉብኝት ጋር ማቆላለፍ ክፉ ስሕተት ነው።



አቶ በቀለ ሻንቆ፤ " . . . እግዚአብሔር በሰጠን የ100 ዓመት ራእይ በኤነክ ራዕይ የዚህችን ምድር ለውጥ እና ጽድቅን የተሞላች፥ ጽድቅን የለበሰች፥ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ፥ በከፍለ ዓለም ደረጃ፥ እግዚአብሔርን የምታስተዋውቅና እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት የምትኖር ኢትዮጵያ እንደምትፈጠርና በመፈጠር ላይ እንዳለች እግዚአብሔር ተናግሮናል። . . . እግዚአብሔር ደግሞ የተናገረውን ይፈጽማል፤ እግዚአብሔር ሊሠራ ተነስቷል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራበት ጊዜ ደግሞ ደርሷልና እግዚአብሔር እጅግ የተከፈተ በር ሰጥቶናልና ይህንን በር ተጠቅመን ለእግዚአብሔር ክብር፥ ለሰው ልጆች ሰላምና ነፃነት፥ ለዚህችም ምድር በረከት የምንሠራበት ጊዜ አሁን ነው፤ ተነሥተን መሥራት ይጠበቅብናል።"

'ጽድቅን የተሞላች፥ ጽድቅን የለበሰች፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል የምትኖር ኢትዮጵያ እንደምትፈጠርና በመፈጠር ላይ እንዳለች' ማለት አዲስ ኪዳን የተጨመረበት ሆኖ እንደ ጥንቷ እስራኤል ወይም ይሁዳ ማለት ይመስላል። በምድር ላይ ጽድቅን የተሞላና ጽድቅን የለበሰ ሕዝብ ወይም አገር ኖሮ አያውቅም። ይህ እስራኤልንም ጨምሮ ነው። ኢትዮጵያ እንደ አገር፥ ሕዝቡም እንደ አንድ ሕዝብ እንደ እግዚአብሔር ቃል ከኖረ እግዚአብሔር በእስራኤል ሊያደርግ አስቦ ያልሆነለት ነገር አሁን በኢትዮጵያ እውን ሊሆንለት ነው ማለት

[18] ስለ ክብረ ነገሥት ከጻፍኩት የአማርኛውን፥ ፈላሻ? ወይም የእንግሊዝኛውን፥ *Falashas: Are They Hebrew?* እና ኢትዮጵያ ኢጀጅን ምን? የሚሉትን መጣጥፎት ይመልከቱ።

ነው። በራእ. 19፥8 እንደ አካል የጽድቅ ልብስ የለበሰች አንዲት አለች፤ እርሷም የበጉ ሚስት የተባለችው ቤተ ክርስቲያን ናት። ጽድቅን የለበሰች አገር ኖራ አታውቅም፤ ወደ ፊትም ከዚህች ከተባለችው የክርስቶስ ሙሽራ በቀር አትኖርም።

ጽድቅን በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ካገኘነው አቋም አንጻር ካየን ይህ በነጠላ፥ በግል፥ በጌታ ሞትና ትንሣኤ አምነን የምናገኘው እንጂ የጋራና የወል አይደለም። አገር ጽድቅን አትለብስም፤ ሰዎች ናቸው ጽድቅን የሚለብሱት፤ ይህ ጽድቅ ደግሞ ክርስቶስን ያመኑ የሚሆኑት ነው። እንዲህ የሆነ ሕዝብ አለ? አዎን አለ፤ ግን ያ ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን ናት። የኢትዮጵኝነት መላ ያጣ ችግር እስራኤልን ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንንም በኢትዮጵያ ለመለወጥ መሞከሩ ነው። ይህ ስሕተት ነው።



መጋቢ ዮሐንስ ግርማ፤ " ጌታ ሲጠራኝ የጠራኝ ጥሪ ራሱ ከዚህች ምድር ጉብኝት ጋር የተያያዘ ነገር ነው። እየሠራሁት ያለሁትም ነገር ጌታ ከዚህች ምድር ጉብኝት ጋር በተያያዘ፥ ከሊርሊ ስሜን የማውቀውን ያህል የማውቀው ጉብኝት ስላለው ለዚያ ነገር ማድረግ የሚገባኝን ተናግሮኝ ነው ሲልከኝም የላከኝ። እና ይሄ ጉብኝት ውሸት ከሆነ የኔም ጥሪና አገልግሎት ውሸት ነው ማለት ነው። ስለዚህ ጌታ ምንድነው ያለህ? ለሚለው ነገር፥ እግዚአብሔር የተናገረኝ ነገር ምንድነው፥ በዚህ በኔ ትውልድ ዘመን፥ የኔ ትውልድ ሳያልፍ፥ እግዚአብሔር ይህቺን ምድር በመንፈሳዊ፥ በቁሳዊ፥ በኢኮኖሚ ሁኔታ፥ በፖለቲካ፥ በሁሉ ረገድ እግዚአብሔር ይህቺን ምድር እንደሚጎበኛት ነው የተናገረኝ። . . . እኔ በጣም ኢትዮጵያዊ በመሆኔ በጣም ደስ የሚለኝ ሰው ነኝ፤ ምክንያቱም በሁሉ ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር ዓላማ ቢኖረውም በዚህ የዘመን መጨረሻ ግን እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ወይም በአበሻ ሕዝብ ላይ በጣም ትልቅ የሆነ የትውልዶች ታሪክ መቋጫ አሳብ እንዳለው በጣም አምናለሁ። እና ደግሞም ከቃሉም፥ ከትንቢትም ድምጽ ዙሪያ ላይ ያለውን ነገር ራሱ አይተን እንድንተረጉም የእግዚአብሔር ቃል መሠረት እንደሚሆንና እንደሚያስተምረን ከብዙ ማስረጃ ጋር የቀረበ የእግዚአብሔር ጉብኝት እንዳለ በጣም እረዳለሁ።"

እኒህ መጋቢ የትንቢቱ መፈጸም እውነት ካልሆነ አገልግሎታቸውና ጥሪያቸውም ውሸት መሆኑን ገልጠዋል። እንደሌሎቹ ኢትዮጵኖች ትንቢያዎች ሁሉ ጉብኝቱ 'መንፈሳዊ፥ ቁሳዊ፥ ኢኮኖሚያዊ፥ ፖለቲካዊ፥ በሁሉ ረገድ' ነውና እነዚህ ነገሮች ካልታዩ አገልግሎታቸው በዜሮ ሊባዛ ይሆን? አገልግሎትና ጥሪን ዋስ አድርጎ መጥራት ያልተለመደ ቢሆንም በቅርብ አንድ ናይጄሪያዊ ተንባይ የተናገረው ነገር ካልተፈጸመ አገልግሎቱን እንደሚተው ተናግሮ ነበር። ነገሩ አልተፈጸምና አገልግሎቱን መተው ነበረበት፤ አልተወም እንጂ።

እንደ እኒህ መጋቢ አሳብ እግዚአብሔር ትልቅ የሆነ የትውልዶች ታሪክ መቋጫ አሳብ በአበሻ ሕዝብ ላይ አለው። ነገር ግን ይህን ትልቅ የትውልድና የታሪክ መጠቅለያ አሳብ በቃሉ ውስጥ እንዲጻፍ አለማድረጉ እግዚአብሔርን ሊያስጠይቅ የሚችል ክስ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ሰዎች የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያውቁበት ዋናውና ግልጹ ምንጭ ቃሉ ነው እንጂ ትንቢያዎች አይደሉም።

በቃሉ ውስጥ የማይገኝ የትውልዶችና የታሪክ መቋጫ በአንድ ሕዝብ ውስጥ ተደብቆ ሳይታወቅ ኖሮ መጨረሻው ሊሆን የአንድ ትውልድ አጋማሽ ዕድሜ ሲቀር መናገሩ እግዚአብሔርን ራሱን ሰዎችን የሚያስትና ከፍጡሩ ጋር ድብብቆሽ የሚጫወት አምላክ አድርጎ ሊያሳየው ይችላል። የአንድ ትውልድ ግማሽ ዕድሜ ያልኩት የመጋቢው ዕድሜ ሠላሳዎቹ

አጋማሽ ውስጥ ቢሆን እንኳ የአሁኑ የኢትዮጵያ አማካይ ዕድሜ (life expectancy) 58 ነውና በ20 ዓመት ውስጥ የሚሆን ነገር ነው የሚነገረን። ስሌቱ ከሌሎቹም ተንባዮች ጋር ተቀራራቢ ነው።

የምናየው የዙሪያችን ነገር የቃሉን ፍጻሜ ያሳየናል እንጂ የእግዚአብሔር ቃል ዙሪያችንን እያየን ወደ ኋላ በመሄድ የምንተረጉመው አይደለም። በኤፌ. 1፥10 *የተጻፈው በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል* ነው ይላል እንጂ እግዚአብሔር በሰማይና በምድር ያለውን አሳቡን የሚቋጨው በግሪክ እና በግሪካውያን እንዳልሆነ ሁሉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያንም አይደለም። የራሱ ይህን ቪድዮ ያዘጋጀው አገልግሎት አሳብም ይህንን ጥቅስ አንግቶአል። መስመሩን ለቀቀ እንጂ።

ኢትዮጵኞች በአንድ ድምጽ የሚነግሩን የመጨረሻው የእግዚአብሔር ጉብኝት ጅማሬውም ፍጻሜውም፥ መሠረቱም ድምድማቱም፥ የጉብኝቱ መሣሪያዎችም፥ አስኳኋኞችና አስተባባሪዎችም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ነው። ይህ ስሕተት ነው! ትልቅ ስሕተት! ጤናማ የሆነ የራስ አክብሮትና የራስ ግንዛቤ መያዝ ትክክል ነው። የራሳችንን መታወቂያ ራሳችን በፈለግነው መልክና ሹመት እንድንጽፍበት ባዶ ወረቀት ግን አልተሰጠንም።

በክርስቶስ ማንነታችን ከገባን ከክርስቶስ ውጪ ባለው ማንነታችን መኩራትና መመካት ይወገድ ነበር። ማንም ዜጋ የአገሩ ዜጋ መሆኑ እንደሚያስደስተው ሁሉ ኢትዮጵያዊ መሆን አስደሳችነት ሊኖረው ይችላል፤ ሊያኮራ ግን አይገባም። አስደሳችነቱ ደግሞ በማይጨበጥ ተስፋ ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም። ከማይጠፋ ዘር የተወለደ ሰው በሚጠፋ ዘር እንዴት ይኮራል? ዜግነት የራሱ ስፍራ ያለው ቢሆንም ሰማያዊ ዜግነትን የተቀዳጀ ሰው በጠፊ ምድራዊ ዜግነት ሊመካና ሊጓደድ እንዴት ይቻለዋል?



መጋቢ ዳንኤል መኮንን፤ "ኢትዮጵያ እጅግ ተስፋ ያላት፥ በእግዚአብሔር የምትታሰብና የምትታይ፥ እግዚአብሔር ታላቅ ዓላማ ለምድሪቷ አለው። ያም ደግሞ የእግዚአብሔር ዓላማ ሁሉን የሚጠቀልል ሆሊስቲክ የሆነ ኢኮኖሚውንም፥ የፖለቲካውንም ዓለም፥ የመንፈሳዊውንም ዓለም የሚጠቀልል ነው። ይህ በእግዚአብሔር ዓይን ታናሽ ነገር ነው። . . . የኢትዮጵያ የወደፊት ሁኔታ በእያንዳንዳችን እጅ ውስጥ ነው ያለው። እግዚአብሔር ይህቺን ምድር እንድንኩተኩታት፥ እንድናጠጣት፥ እንድንንከባከባት፥ እኔ ልቅደም ሳንል አገራችንን አስቀድመን፥ የኔ ጥቅም ሳንል ለአገር ጥቅም ብለን ከወጣን ኢትዮጵያ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደምትፈልገው ደረጃ ላይ ትደርሳለች ብዬ አምናለሁ። ይሁንና በዚህ ላይ ደግሞ ጌታን የሚያውቁ የጌታ ልጆች ከርስቲያኖች አስተዋጽዎቸው እጅግ ከፍተኛ ነው። ያም ደግሞ የሚሆነው በምሳሌነት በኢኮኖሚው፥ በፖለቲካው፥ እንደገናም ደግሞ በመንፈሳዊውም ዓለም፥ ምሳሌ በመሆን መቅደም ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ይህንን እያስተዋልንና እየተረዳን ተስፋ እንዳላት አገሪቱ አውቀን እግዚአብሔርን እያመሰገንን ጠንክረን ልንሯመድና ልንሠራ ይገባናል።"

የእኒህ መጋቢ አስተያየት፥ በዚህ ጊዜ ይህ እንደሚሆን እግዚአብሔር ተናገረኝ የሚል ሳይሆን የግል እምነትን የያዘ ነው። የኔ ጥቅም ሳንል ብንሠራ አገሪቱ እፈለጎችበት ደረጃ ትደርሳለች፤ ኢኮኖሚው፥ ፖለቲካው፥ መንፈሳዊውም። በጥቅሉ ኢትዮጵያ ትቅደም ማለት ጥሩ ምክር

ነው። ከዚህ በፊትም ተብሎ ነበር። 'ትቅደም' ያሉትም በማስቀደም ሲቀድሙ አልታዩም እንጂ።

ይህ ሥራን፥ ታታሪነትንና ተግባራዊነትን ያቀፈ ግሥጋሴ ምክር ከሆነ መልካም ነው። የኢትዮጵያ እጅግ ተስፋ ያላት መሆን ግን ከዚህ ከስስታምነት የራቀ ታታሪ ሠራተኛነት የሚወልደው ይሁን ወይም ከቃሉ መሆኑ ግልጽ አልተደረገም። ከኢኮኖሚያዊ ትንታኔና ከሠራተኝነት ባሕል አንጻር ከሆነ ማለፊያ ነው። የቃለ መጠይቁ ጥያቄ ግን፥ እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ምን ተናገረዎ? የሚል ስለሆነ መልሱም ጥያቄውን የተደገፈ ነው ብንል አገሪቱ እጅግ ተስፋ ያላት መሆኗ እንደ እግዚአብሔር አሳብ ወይም እንደ ቃሉ ነው ሊባል ይቻላል? ይህ ከሆነ ኢትዮጵያን ልዩ፥ ባለ እጅግ ተስፋ፥ ባለ ታላቅ ዓላማ፥ ታሳቢና ባለ ትኩረት ሆና ተስላለች።

'የኢትዮጵያ የወደፊት ሁኔታ በእያንዳንዳችን እጅ ነው ያለው' ሲባል ከኃላፊነት ይልቅ ሥልጣንን የሚያመለክት ይመስላል። እያንዳንዳችን ጠቅላላው ዜጋ ነው ወይስ ክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ ብቻ? በዚህ ስሌት ውስጥ የእግዚአብሄር ድርሻ ምን ይሆን? ለመሆኑስ እግዚአብሔር ድርሻ አለው?

ኢትዮጵኞች ኢትዮጵያን ከሌላው አገርና ከሌላ ሕዝብ ጋር እኩል አሰልፈው እግዚአብሔር ለሁሉም ዓላማ እንዳለው፥ አሳብ እንዳለው ስለማያቀርቡ የአድልዎ አምላክና ፍርድ ገምዳይ አስመስለው ያቀርቡታል። እግዚአብሔር ለሌላው አገርና ሕዝብ ግድ የሌለው መስሎ ለኢትዮጵያ ግን ከመንገዱ ወጥቶ የማበሻ ጨርቅ ታጥቆ ሊያገለግላት የተነሣ አምላክ ያደርጉታል። ይህ ስሕተት ነው።



ወንጌላዊ መድህን ገ/ስላሴ፤ ". . . የእግዚአብሔር መንፈስ ለኔ በግሌ የተናገረኝ ከብዙ በጥቂቱ ማስታውሰው፥ እግዚአብሔር አምላክ ኢትዮጵያን አገራችን ታያላን ከሚባሉት አገሮች መካከል አንዷ እንዲሁም፥ እንዲያውም ዋናዋ እንደሚያደርጋት፥ በዚህ ምድር ላይ ብዙ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደሚገቡ፥ ጌታ በድንቅና በተአምራት በብዙ ከብር በዚህች ምድር ላይ እንደሚሠራ ተናግሮኛል። . . . እንግዲህ ጠቅለል አድርገን ስናየው ስለ ኢትዮጵያ እግዚአብሔር የሚናገረው መልካም ነገር ነው፤ እንዲያውም እኛ ከምናስበው፥ ከምንገምተው፥ ይሆናል ብለን ፈጽሞ ከማናስታውሰው ነገር እጅግ በላይና ያለፈ ነገር ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር እርሱ እግዚአብሔር ነው። . . . እግዚአብሔር አምላካችን በዚህች ምድር ላይ ታላላቅ ነገር እንደሚያደርግ ደጋግሞ ተናግሮአል፤ በውጪ ያሉት ሰዎች ሳይቀር ወደዚህ ምድር መጥተው አፈሯን ለፈውስ ይዘው እስኪሄዱ ድረስ እግዚአብሔር እንደሚያደርግ ተናግሯል። ትልቅ መንፈሳዊ መነቃቃት ዓለምን ሁሉ የሚያነቃንቅ መንፈሳዊ ነገር በዚህች ምድር ላይ እንደሚገለጥ እግዚአብሔር ተናግሯል። . . . እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ መንፈሳዊም፥ ምድራዊም፥ ሁለተናዊ በረከትና በነገር ሁሉ ስለ ኢትዮጵያ ወደላይ መነሣት ነው እግዚአብሔር የተናገረውና ይኼ ደግሞ እንግዲህ በጊዜው ይሆናል።"

እኒህ ወንጌላዊ ከብዙ በጥቂቱ ያስታወሷትን ነው የተናገሩት። እግዚአብሔር በግል ተገልጦ የተናገረው ነገር እንዲህ በቀላሉ የሚረሳ መሆን የጀመረው ቃሉን በጻፉልን ሰዎች ዘመን አለመሆኑ ድንቅ ነው። እነ ኢሳይያስና እነ ጳውሎስ ከተቀበሉት ከፊሉን እየረሱ ከፊሉን እያስታወሱ የሚጽፉ ሰዎች እንኳን ያልሆኑልን።

ኢትዮጵያ ኃያላን ከሚባሉት አገሮች ዋናዋ ትሆናለች ማለት እንደ ዛሬዎቹ እነ አሜሪካ ትሆናለች ማለት ነው። ኃያል ሲባል አሁን ጎልታ የምትታየው እርሷ ስለሆነች ነው አሜሪካን የጠቀስኩት። በብልጽግና እፍታዎቹ እንደሆኑት አገሮች በገንዘብና ምጣኔ ሃብት ብቻ ሳይሆን፥ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በሳይንሱና ቴክኖሎጂው፥ በኢንዱስትሪና ዘላቂ ግንባታዎች (infrastructure)፥ በጦር መሳሪያና በጦር ኃይልም ጭምር ነው ኃያልነት የሚለካው።

ኃያልነትን ወይም የብልጽግና ንጽጽርን ከብዙ አቅጣጫ ማየትና ማነጻጸር ይቻላል። በዕድገት ውስጥ ከሚካተቱት ትልልቅ ነገሮች አንዱ ጤንነትና የጤና ተቋማት መሆናቸው እሙን ነው። ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ለማየት የሆስፒታሎችን ቁጥር እንውሰድ፤ በኢትዮጵያ 120 በአሜሪካ 5880 አሉ። የሕዝቡን ቁጥር ግምት ውስጥ አስገብተን ብናሰላው አንድ ሆስፒታል ኢትዮጵያ ውስጥ ለ830 ሺህ ሰዎች ሲሆን አሜሪካ ለ55 ሺህ ሰዎች ነው። የሆስፒታሎች ዘመናዊነትና የሕክምና ቅልጥፍና ግምት ውስጥ ከገባ ስሌቱ ጨርሶውኑ ይበላሻል። እንዲህ ያሉ ስሌቶችን በየአቅጣጫው አይተን ኢትዮጵያ በ2030 2ሺህ ዘመናዊ ሆስፒታሎች ይኖሯታል ብለን መተለም እንሞክራለን። ይህ እንዲሆን በየዓመቱ 130 ሆስፒታሎች ሊሠሩ መሆን አለበት። ግን እንዲህ አለመተለም ይሻላል፤ ምክንያቱም ሌላው ተንባይ ሆስፒታሎች ሁሉ ይዘጋሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ይሆናሉ፤ በሽታ ይጠፋል ብሏል። ከኃያላን አገሮች ዋናዋ ከሆነች ኃያልነት የጦር ኃይል ብቻ አለመሆኑን ለማውሳት ነው።



"ሁለት ትልልቅ ንግግሮች እግዚአብሔር ተናገረኝ፤ አንደኛው በኃይል የሚያቃጥል ፀሐይ በምድሪቱ ላይ እየነደደ ሰው ሁሉ ከፀሐይዋ ጨረር ለማምለጥ ልብሱን ጋርዶ ነው ሚሄደው፤ . . . አይናገርም ሳዘንተኛ ነው፤ ድንገት ከምሥራቅ ቀስተ ደመና ይመጣል፤ . . . ምድርን በሚነካበት ጊዜ ከኢትዮጵያ ምድር ላይ እርግማን እንደ ጉም ተነቅሎ ወጣ፤ ሦስት ድርብርብ ቀስተ ደመና ነው፤ . . . ከሰማይ ድምጽ፥ 'በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም የጸና ቃል ኪዳን ማለት ነው፤ . . . ኢትዮጵያ ለረጅም ጊዜ እጅግ ትባረካለች፤' የሚል ድምጽ። ልክ ይህን ሲናገር ምድር ሳትታረስ ኃይሏን ስለምትሰጥ ሳይዘራ እህል ይመረት ጀመር፤ . . . ያ ቀስተ ደመና ሰዉን ሁሉ ከምድር ሲሰብ ከአራቱም ማዕዘን ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው የሰው ሕዝብ ብዛት ለመቁጠር ያታክታል፤ ምድሪቱ ግን አትጠቡብም፤ የማስተናገድ ብቃት አለ። አዝመራው እጅግ ከመባረኩ የተነሣ፥ እህል ከመበዛቱ የተነሣ፥ . . . አሀያ ጥራጥሬ እስኪንቅ ድረስ ጠግቦ ምድር ተዝረከርካለች በበረከት። . . . እግዚአብሔር በሰማያዊም በምድራዊም በረከት ሲባርከን አይቻለሁ።

በሌላ መንገድ ደግሞ እንዲናገረኝ ጠየቅሁት፤ አሁንም ሁለተኛውን ንግግር እናገራለሁ፤ ሁለተኛው ንግግር ምንድነው? ሰው ሁሉ በድቅድቅ ጨለማ ተሸፋ በመቁረጥ መሬት ላይ ተኝቷል። . . . በእኩለ ሌሊት ነጋ ይባላል። አሞራዎች ከምዕራብ፥ ከሰሜን ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያን ይዞራሉ፤ መጥተው ስፍራ ስፍራቸውን በሚይዙበት ጊዜ ሰው ሁሉ በትንሣኤ እንደሚነሣ ከእንቅልፉ ይነቃል፤ ተነሥቶ አየሩን ሲጠጣው ሕይወት የሚሰጥ አየር ነው፤ ምግብ መሆን ሚችል ነው፤ በጣም ጣዕም ያለው አየር ነው፤ ጤንነትን የሚሰጥ አየር ነው፤ ማመን እስከሚያቅተው ሰው ሁሉ፥ 'እውነት እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ወይ? ይኼ ንጋት የነጋው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ወይ? በእውነት እኛ ኢትዮጵያውያን ነን ወይ እንደዚህ ዓይነት አየር ምንጠጣው?' ብሎ ማመን እስከሚያቅተው ድረስ በእግዚአብሔር ደስታ ውስጥ ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ጤና የሚሰጥ አየር ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኗል በሚል ነጩም ጥቁሩም ከኢትዮጵያ ውጪ ወደ ኢትዮጵያ ሲጎርፍ አየሁ። ይሄ የቀረልን ዘመን የሚሆንልን እግዚአብሔር የተናገረው ነው። . . . ዕድሜና ጤና እንዲሰጠን ለራሱም ለሕዝቤም እጸልያለሁ።"

ምድር ሳትታረስ ኃይሏን እየሰጠች እህል ከተመረተ ግብርና አዲዮስ! ዔድን ገነት ተመልሳ መጣች፤ የት? ኢትዮጵያ! በኢትዮጵያ የድርቁና ረሃቡ ነገር ከመጥበሻው ወደ ምድጃው እየሆነ

ነው። ዋናዎቹ ምክንያቶች የገበሬው በዝናብ መደገፍ እና የገበሬው የምርት መሣሪያዎቻችን ዛሬም የጥንታዊው የድንጋይ ዘመን መሣሪያዎች መሆን ናቸው። በዚህ ላይ አስተዳደራዊ ችግር ሊታከልበትም ይችላል። ስለዚህ በዚህ ዓመት በበልግ ዝናም ካልጣለ በቀጣዩ ዓመት ራብ አለ ማለት ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ በዓለም የዕድገት ሊቃውንት 'chronically food insecure' ተብላ ተጠርታለች። የምግብ ዋስትና እጅግ እጅግ አሳሳቢ የሆነባት ወይም የምግብ ዋስትና ጨርሶ የሌለባት ማለት ነው። ይህንን እየጻፍኩ (Nov. 2015) በጎን ዜና ሳነብብ በአሁኑ ጊዜና እስከ ቀጣዩ ዓመት እንደሚገመተው ከ9 እስከ 15 ሚሊየን ሕዝብ ተረጂ ሊሆን በአሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ይገኛል።

አህያ ጥሬ ንቆ ምድር በእህል ስትዝረከረክ የሚያዩልንን ባለ ራእዮች አያሳጣን እንበል? የተንባዮች ተስፋ እራት ከሆነ እየጠገብን ነን። አየራችንም 'ሕይወት የሚሰጥ አየር፥ ምግብ መሆን ሚችል ነው' ከተባለ ምግብ ጥንቡን ይጣል እንጂ! እንዲህ ከሆነ የምድር አሕዛብ አየራችንን ለመጎንጨትና ሕይወታቸውን ለማራዘም አገራችንን ቢሰፍሩባት ምን ይደንቃል?! አየር ከተበላ አዞን ሳይሸነቆርና ምድር ሳትበክት ገና እንደተፈጠረ የነበረው አክሲጅን ነበር እንጂ መገመጥ የነበረበት። ግን ታዲያ እነ አዳም እንኳ መቼ ነው አየር እየቆረሱ የበሉት?

ተንባዮቻችን የመጨረሻው ዘመን መቅረቡን የሚስማሙ ይመስላል። ብዙዎቹ ይህንን በቀጥታም በተዘዋዋሪም ገልጸዋል። ሆኖም በመጨረሻው ዘመን ራብና ቸነፈር ይሆናል ብሎ ጌታ የተናገረው (ማቴ. 24፥7፤ ማር. 13፥8፤ ሉቃ. 21፥11) ስሕተት ሳይመስላቸው አይቀርም። ቃሉ መስተካከል ይኖርበት ይሆን? እንደ ብዙዎቹ ወይ ቃሉ ወይም ጠቅላላው የፍጻሜ ዘመናት ስነ መለኮታችን መስተካከልና የዶሚኒየን ስነ መለኮትን እግር በግር መከተል አለበት። የለም፤ ቃሉ መስተካከልም መለወጥም አይችልም። ሰዎች ይህንን የማይስተካከል ቃል በጥሞና ማንበብ ቢችሉ ምንኛ እነርሱም ሰሚዎቻቸውም ከስሕተት ሊጠበቁ በቻሉ ነበር።



መጋቢ ፋሲል ኃ/ማርያም፤ "እግዚአብሔር አምላክ በተለይ፥ ከአስራ ስድስት ከአስራ ሰባት ዓመት በፊት፥ በ84 ዓመተ ምሕረት፥ እግዚአብሔር ታላቅን፥ ዓለምን ሁሉ የሚያስደንቅ፥ የመንፈስ ቅዱስ ጉብኝት በኢትዮጵያ ላይ እንደሚሆን ተናግሮኛል እግዚአብሔር። ነገር ግን፥ 'ለምን ይህን ያህል ጊዜ ዘገየ?' እያልኩ በእግዚአብሔር ፊት የማለቅስበትም፥ የምጠይቅበትም ጊዜ አለ፤ ብዙ ጊዜ ለምን ብዬ በምለው ነገር ላይ፥ እንዲያው እስፔሲፊክ የሆነ ከእግዚአብሔር ያገኘሁት ነገር አልነበረም፤ ነገር ግን ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት በ94 በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር እጅግ ልቤ ቢቃ በዚህ ጉዳይ ላይ በማዘንና ተስፋ በመቁረጥ፥ 'ስለምን ጌታ ሆይ የጉበኝትህ ጊዜ ዘገየ?' እያልኩኝ በምጠይቅበት ጊዜ፥ በአንድ የጸጥታ፥ የእግዚአብሔር ፊት ጊዜ ላይ፥ አራት ሰዎች በኢትዮጵያ ላይ ቢታላቅ የመንፈስ ቅዱስ በረከት እንደሚነሡ እግዚአብሔር በፊት ለፊት፥ ፍጹም በሆነ ግልጽ በሚገባኝ መንገድ ተናግሮኛል እግዚአብሔር። እነኚህ አራት ሰዎች ከኢትዮጵያ ገጠር ይሁን ከአዲስ አበባ ይሁን ከኢትዮጵያ ውጪ ከተበተኑ ኢትዮጵያውያን ይሁን አላውቅም። ነገር ግን አንድ ነገር አውቃለሁ፤ እነኚህን ሰዎች እግዚአብሔር በቅርብ ጊዜ ውስጥ ያስነሣቸዋል።"

አንዳንዶቹ ተንባዮች የሚናገሯቸው ነገሮች በጣም ግልጽ ከመሆናቸው የተነሣ ሊያስጠይቃቸው የሚችል ሲሆን፥ የአንዳንዶቹ ደግሞ ጉምና ጭጋግ ባለበት ጨለማ ከሩቅ ሊያዩት እንደሚሞክሩት ነገር ያለ ነው። ጉም ነው፤ ጭጋግ ነው፤ ጨለማ ነው፤ ሩቅ ነው። ይህኛው እንደዚያ ያለ ትንበያ ነው። መጋቢው ቀድሞ ስላዩት ነገር ሲናገሩ፥ 'እስፔሲፊክ የሆነ ከእግዚአብሔር ያገኘሁት ነገር አልነበረም፤' ብለው በቀጣዩ ይህንን እንዳገኙ ተናግረዋል።

እስፔሲፊክ ማለት በጣም ግልጽ የሆነ፥ ጥቅልልና ጅምላ ያልሆነ ማለት ነው። ከየት እንደሚነሱ የማይታወቁ አራት ኢትዮጵያውያን በቅርብ ይነሣሉ፤ ከዚያ በነዚህ ሰዎች ዓለም የሚደነቅበት ታላቅ ጉብኝት፥ የመንፈስ ቅዱስ በረከት ይሆናል። የመንፈስ ቅዱስ በረከት ምንድር ነው? ጉብኝትስ? ቅርብ መቼ ነው? ምኑ ነው 'እስፔሲፊክ?'

ከእኒህ መጋቢ ቃል ከሌሎቹ ኢትዮጵኞች ጋር የሚስማማው አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ ያም ዓለምን ሁሉ የሚያስደንቀው ጉብኝት ጅማሬ ኢትዮጵያ ናት። ይህንን እየጻፍኩ ሳለሁ አንድ መጽሐፍ እየገረፍኩ ነበር። ርእሱ፥ ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው የሚል አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ በተባሉ ሰው የተጻፈ ነው። 'እውነት፥ ለዚህ ላሉት ነገር ውኃ የሚያነሣ ማስረጃ አላቸው ይሆን?' ብዬ በመግረፍ ፈንታ አነበብኩት። ብዙ ተረትና ጥንቆላ መሳይ ትምህርቶች የታጨቁበት ሆኖ ማርቆስ ብቻ ሳይሆን ቶማስንና ፊልጶስንም ኢትዮጵያውያን ያደርጓቸዋል።[19] ምንጭ ሲጠቅሱ፥ 'በ[illegible] - [illegible] በተጻፈው ላይ ዋልድባ ሄደህ ተረዳ' ይላል። ለዚህ ከተረትም የወረደ ነገርስ ዋልድባ መሄድ ነውር ነው። ግን ድንቅ ነው! ክርስትና ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት ሳይገባ በፊትም በዋልድባ ተጽፎ የተቀመጠ የጌታ ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት ኢትዮጵያውያን የመሆናቸው ታሪክ አለንና! ኢትዮጵኝነት በሚሊኒየም የተጀመረ ጉዳይ አይደለም።



መጋቢ ዶ/ር ቤዛለም ፍስሃ፥ " . . . በረከት እንዲያደርጋት እጸልያለሁ፤ በዚህ ሂደት ውስጥ የተረዳሁት፥ በውስጤ የተቀመጠው የገባኝ ነገር ምንድርነው፤ እግዚአብሔር ይህቺን ምድር የሚነበኝበት፥ የሚባርከበት፥ ከዚህ ጉስቁልና፥ ሕዝቦቿ ካሉበት ውርደትና ስቃይ፥ ድኅነት፥ የመልካም አስተዳደር እጦት፥ ማኅበራዊ ቀውስ አውጥቷት፥ ባርኳት፥ በልጽጋ፥ ታላቅ ሆና፥ ከዚያም አልፋ ደግሞ ለሌሎች አገሮች፥ በምሥራቅ አፍሪቃም፥ በሰሜን አፍሪቃም፥ እመካከለኛው ምሥራቅ፥ ለሌሎች አህጉራት እንኳ ሳይቀር በተለያየ ረገድ፥ ወንጌልን በማስፋፋት፥ ለጽድቅ ለፍትሕ በመቆም፥ በድህነት ያሉትን ሰዎች ካሉበት ድህነት በማውጣት፥ በዓመጽ በከፋት ለሚሮጥ ሕዝብ በመማለድ፥ እግዚአብሔር ቡብዙ አቅጣጫ ለበረከት እንደሚያደርጋት አምናለሁ፤ ጊዜውም እንደቀረበ፥ ወቅቱ እንደደረሰ እረዳለሁ። ልክ ነቢዩ ሳሙኤል፥ ነቢዩ ኤልሳዕ፥ በቀርሜሎስ ተራራ ሲጸልይ ሲያምጥ እንደነበረ በጓላ እጅ የምታህል ደመና ግን በርክታ ዝናብ ውስጡ የያዘ ደመና እንዳየ፥ ያ ደመና እየታየ ነው፤ ጊዜው እንደደረሰ፥ ጉብኝታችን እንደደረሰ፥ በደጅም እንደሆነ ይሰማኛል። እና በዚህ ሚሊኒየም ኢትዮጵያ ካለችበት ድህነት፥ ጉስቁልና፥ ጨለማ፥ ረሃብ፥ [?]እጦት፥ ማኅበራዊ ቀውስ ተላቅቃ ወደ በለጸገ፥ ሁሉ ሰው በደስታ ወደሚኖርባት፥ ከዚያም አልፋ ለሌሎች አገሮች በረከት ወደምትሆንባት ደረጃ እንደምታልፍ፥ ይህንን እግዚአብሔር በልቤ ውስጥ አስቀምጧል።"

እኒህ መጋቢ፥ 'እጸልያለሁ' ብለው ጸሎታቸውን ቢገልጡም የጠቀሷቸው ነገሮች ሁሉ እንደሚሆኑ 'አምናለሁ፤ እረዳለሁ፤ ወቅቱ ደርሷል፤ በደጅ እንደሆነ ይሰማኛል . . .' በማለታቸው ያዩአት ኢትዮጵያ ሌሎቹም እንዳዩአት ያለችው ናት። በዚህ ሚሊኒየም በልጽጋ፥ ታላቅ ሆና፥ ድኅነትና ማኅበራዊ ቀውሶች፥ ረሃብና እጦት ጠፍተው፥ ሰው ሁሉ በደስታ የሚኖርባት አገር ስትሆን አይተውላታል።

ነቢዩ ሳሙኤልና ነቢዩ ኤልሳዕ በቀርሜሎስ ላይ ደመና አላዩም፤ ይህ በስሕተት ስለ ኤልያስ ስለተነገረው የተጠቀሰ ቃል ቢሆንም ከኢትዮጵኝነትን ጉም መዝገን ጋር በጣም የሚመሳሰል

[19] ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው፤ ገጽ 42-43።

ነው። የተጠቀሱት ሰዎች በቦታው (በቀርሜሎስ) እንዳልነበሩ፥ ደመናውም በቦታው እንዳልነበረ ያለ ነገር ነው በኢትዮጵኞች አማካይነት እየሆነ ያለው። ከሌለ ደመና ዝናብ እየጠበቅን ነን። ድኃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ በነጣ እንደሚባለው ነው። በሕልማችን ቅቤ እየጠጣን ንጣታችን ይጥፋ እንጂ! ችግሩ ግን ቅቤው የሕልም የመሆኑን ያህል መውዛታችንም የሕልም ብቻ መሆኑ ነው።



መጋቢ ወንድሙ ሞላ፤ "እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ብዙ ነገር ተናግሯል . . . እኔም እንዲህ ያለ ነገር ነው በልቤ ውስጥ ያለው፤ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ፥ የእግዚአብሔር ሰው ቁስ በሊና በተናገሩት ቋንቋ ብጠቀም፥ የከፍታ ዘመን የሚል መጽሐፍ ጽፈዋልና . . . እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ስለለምድራችን፥ የመጨረሻው፥ የዓለም የመጨረሻ ያለው፥ በዓለም አለን የሚሉት ሃብት ተንጠፍጥፎ፥ እግዚአብሔር አንደኛ ብልጽግናንም በተመለከተ ለኢትዮጵያ ያለው ነገር አለ፤ ሌላው ግን እኔ ሚታየኝ ወንጌልን በተመለከተ፥ ለኔ ትልቁ ብልጽግና ወንጌል ነው፤ ወንጌልን በተመለከተ፥ የኛ አገልግሎት ኢትዮጵያ ላይ ብቻ የሚቀር ሳይሆን ዓለም በሙሉ ኢትዮጵያን እንደምትጠበቅ፥ ለዓለም ሁሉ መፍትሔ ከኢትዮጵያ አገልጋዮች እንደሆነ፥ እግዚአብሔር በልቤ አስቀምጧል። . . . ውስጤ ያለው መረዳት፥ አሜሪካንን፥ የስለጠኑ አገሮችን፥ እንረዳለን የሚል እምነት ውስጤ አለ። . . . በጣም ደስ የሚለኝ፥ አንዳንድ ጊዜ፥ 'እግዚአብሔር ኢትዮጵያዊ ነው ወይ?' እላለሁ። እንደኛ ስለ ኢትዮጵያ ከ42 ጊዜ በላይ ከ43 ጊዜ በላይ ኢትዮጵያ የሚል መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እናነኛለን። . . .

እግዚአብሔር አንድ ጊዜ አንድ ነገር ተናገረኝ፤ ምንድነው የተናገረኝ፥ እነዚህ ከዓለም ያሉ ኮሪያ፥ ቻይና፥ ጀርመን፥ አሜሪካ፥ ካናዳ፥ የሁሉም፥ እስፔሻሊ መንፈሳዊ ነገር ሚሰሩት ትኩረታቸው ለኢትዮጵያ ነው። ለምንድነው ጌታ ሆይ አልኩ። "ፑልፒት የሚገኘው ሰባኪው አጠገብ አይደል?" አለኝ እግዚአብሔር። "አዎ።" "ፑልፒት ወዳለበት የማይመለከት ተሰባኪ አለ?" አለኝ። "የለም።" "እንግዲያው፥ የሁሉም አገር ትኩረት፥ በሚሽነሪም በሁሉም ነገር ትኩረት ወደዚህ ትኩረት የሚያደርገው የኔ ፑልፒት ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።" አለኝ። በጣም እግዚአብሔርን ባረከሁት። የእግዚአብሔር ትኩረት ወደዚህ ነው። . . . ዓለምን የሚደርሰው፥ ዓለምን የሚናገረው እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ላይ ቆሞ ነው። . . . ስለዚህ ኢትዮጵያ ለዓለም መንፈሳዊ ነገር፥ ለዓለም የእግዚአብሔር የሆነ ነገር እንደምታደርስ እኔ እግዚአብሔር ተናግሮኛል። ከዚህ የተነሣ ይህንን እንኳ ሳላይ ዕድሜዬ ወይም ሕይወቴ እንደማያልፍ እርግጠኛ ነኝ። . . . 90% የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስቲያን ይሆናል። 10% ደግሞ ይመለከታሉ። . . . ከ90% ምክንያት ወደፊት የኢትዮጵያ ፓርላማ በፓስተሮች ጸሎት ነው የሚከፈተው። ይኼ እውነት ነው። ሚዲያዎች በሙሉ በወንጌል ስር ይገባሉ። ኢቫን የኢትዮጵያ መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን በጅት የሚመድብበት ዘመን አለ፤ ወንጀሎች ይቀንሳሉ፤ በሽታዎች ይጠፋሉ፤ ከሊኒኮች በብዛት ይጠፋሉ፤ አብዛኛው ክሊኒክ ቸርች ይሆናል፤ አብዛኛው ሆስፒታል መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ይሆናል። . . . በቃ ምድሪቱ ትፈወሳለች።"

የእኒህ መጋቢ ትንበያ በጣም ግልጽና ዝርዝር፥ በአጎዝም የተደገፈ ነው። 90% ክርስቲያን፥ 10% ተመልካች። የፓርላማ ተመራጮች ክርስቲያኖች፥ ወንጀል ይቀንሳል፤ ወንጀል ጨርሶ ያልጠፋውም 10%ው ተመልካቾች ስላሉ መሆን አለበት። ሚዲያዎች ክርስቲያን፤ መንግሥት ክርስቲያን፤ በሽታ የለም፤ ሐኪምና ሐኪም ቤት አይኖርም። ኢትዮጵያ የዓለም መፍትሔ፥ አሜሪካን ሳይቀር የምትረዳ፥ የኢትዮጵያ አገልጋዮች የዓለም ችግር ቁልፎች ሁሉ መክፈቻዎች፥ የእግዚአብሔር ምስባክ (ፑልፒት) ኢትዮጵያ ውስጥ፥ እግዚአብሔር የሚናገረው ከኢትዮጵያ፥ ትኩረቱ ኢትዮጵያ፥ ዓለምን የሚደርሰው ኢትዮጵያ ላይ ቆሞ ይሆናል። ኢትዮጵያ፥ ኢትዮጵያ፥ ኢትዮጵያ።

እግዚአብሔር እንኳ አበሻ እንደሆነ ሲታሰብ አይደንቅም?! እንዲህ ያለ የወረደ ነገር በአንድ ክርስቲያን መታሰቡ ራሱ ቢያሳፍርም ይድነቅ እንጂ! ከላይ የተባሉት ነገሮች ከሆኑ

እግዚአብሔር አበሻ ባይሆን ነው የሚያስደንቀው እንጂ አበሻ ቢሆን ምን ይደንቃል?! በሬ ካልሆንኩ እንዳለው እንቁራሪት ኢትዮጵኝነት ተጠቅጥቆብን ልንፈነዳ ትንሽ ነው የቀረን። እግዚአብሔር ከዚህ ይጠብቀን እንጂ የፈነዳን ቀን ግማታችን ዓለምን ይሞላል። ቀደም ሲል እነ አዳምን እና ከርስቶስንም አበሾች አድርገው የጻፉ ስላልታጡ እኒህ መጋቢም እግዚአብሔርን ኢትዮጵያዊ አድርገው ቢያስቡ ምንም ማሰቡ ራሱ አሳፋሪ ቢሆንም ይህ የተለመደ አካሄድ ነውና አይገርምም።

ይህ የሚሆንበት ጊዜም ተነግሮአል። 'ይህንን ሳላይ ዕድሜዬ ወይም ሕይወቴ እንደማያልፍ እርግጠኛ ነኝ።' ብለዋል። ከመጋቢው ዕድሜ፥ ከኢትዮጵያ አማካይ ዕድሜ (life expectancy) ወይም ከሌሎቹ ትንበያዎች በመነሣት ከላይ የተባሉት ነገሮች በቀጣዮቹ ጥቂት ዓመታት ብንጠብቅ በፍጹም ስሕተት አይሆንም።



መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን፤ "ይኼ እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ ያለው የሚባለው ነገር ዝም ብሎ ከኪሳችን አውጥተን የምንናገረው ነገር አይደለም። ዝም ብሎ ትናንት የመጣ ራዕይ፥ ትንቢት ሕልም ነገር ብቻ አይደለም፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈ ነው። መቼም ለኛ እንዴት ኢትዮጵያ እንዲያው ከሌላው አገር ሁሉ ከስንት ስንት የተሻሉ አገሮች ተለይተን እኛ እንዴት የእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብለው ሰዎች ሊገርማቸው ይችላል፤ ግን፥ ይህ ደግሞ ልንክደው የማንችለው እውን ነው፤ በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ፥ ይህች ኢትዮጵያ፥ የኛ ኢትዮጵያ፥ የፖለቲካ ክልሏ አሁን የምናውቀውም እንኳ ባይሆን፥ ከዚህ ሰፋ የሚልም እንኳ ቢሆን፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሳለች። በደንብ እንደተጠቀስን እናውቃለን፤ ስለ እኛ የሚናገሩ ብዙ ጥቅሶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉ እናውቃለን። ከነዚህ ጥቅሶች አስደናቂዎቹ እግዚአብሔር በዚህች ምድር ወደፊት ሊያደርገው ስላለው ነገር የሚናገሩ ነገሮች ናቸው። ለምሳሌ የዳዊት መዝሙር 68፥31 ይታወቃል። ኢትዮጵያ እጆቿን ፈጥና ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለው ይታወቃል።

አንዳንድ ሰዎች፥ 'ይኼ እውነት ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ነው ወይ የሚናገረው? እንደዚህ ስትሉ እናንተ ከዐውዱ አውጥታችሁት ነው ይህንን ጥቅስ ይላሉ። በጭራሽ! ከዐውዱ አላወጣነውም። ዐውዱ እንደዚያ ነው የሚለው። *ሦስት ምሳሌዎችን እዚህ መጥቀስ እችላለሁ።* ቁጥር 18 ላይ፥ *ወደ ላይ ዓረግህ፥ ምርኮን ማረክህ፥ ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ፥* ይላል። ይኼ በአዲስ ኪዳን በኤፌሶን ሐዋርያው ጳውሎስ ጠቅሶታል፤ . . . ስለዚህ ይኼ ነገር ፕሮፌቲክ ነው ማለት ነው። ወደፊት ስለሚሆን ነገር ነው ሚናገረው ማለት ነው። ሌላም ቁጥር አለ፤ ቁጥር 25 ላይ፥ *አለቆች ቀደሙ፥ መዘምራንም ተከተሉ፤ ከበሮን በሚመቱ በቈነጃጅት መካከል።* ይላል። አንዳንዶቹ ሰዎች የሚሉት ምንድነው? ይኼ ለዳሮ ጊዜ የተነገረ ነው፤ ተፈጽሞአል፤ ስለ ምድረ በዳው ጉዞ ነው የሚናገረው፤ የእስራኤል ሕዝብ 40ውን ዓመት በምድረ በዳ እንዴት እንደተጓዙ ነው ሚናገረው ነው የሚሉት። እውነት ነው፤ ስለዚያ ጉዞ ይናገራል፤ ምንም የማንክደው ነገር ነው፤ ግልጽ ነው፤ ግን ከዚያ ያለፈ ነገር ደግሞ ይናገራል፤ ያን ጉዞ ሲጓዙ እንዴት ይጓዙ እንደነበረ አስላላፋቸው፥ የትኛው ነገድ ፊት እንደሚሆን፥ የትኛው ነገድ ቀጥሎ እንደሚሆን፥ የትኛው ነገድ መጨረሻ ላይ እንደሚሆን፥ የትኛው ነገድ በስተግራ በስተቀኝ እንደሚሆን፥ ተድፏል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ። ይኼ ግን የሚለው አለቆች ቀደሙ መዘምራን ተከተሉ ነው የሚለው፤ ይህ አዲስ አሰላለፍ ነው። የምድረ በዳው አሰላለፍ አይደለም። መዘምራን ተከተሉ አለቆች ቀደሙ የሚል የለም፤ ስለዚህ ይኼ ፕሮፌቲክ ነው። ሌላ ቁጥር አለ፤ ቁጥር 29 አለ፤ *በኢየሩሳሌም ስላለው መቅደስህ ነገሥታት እጅ መንሻን ለአንተ ያመጣሉ።* ይላል። በኢየሩሳሌም መቅደስ የኖረው 1ሺህ ዓመተ ዓለም ገደማ ነው፤ ከክርስቶሽ በፊት 1ሺህ ዓመት በፊት በዳዊት ዘመን ነው፤ 9መቶ 1ሺህ ገደማ። የምድረ በዳው ጉዞ ደግሞ የነበረው 1ሺህ 5መቶ ዓመት ገደማ ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው። ኢየሩሳሌም ያኔ የለችም፤ በኢየሩሳሌም መቅደስም የለም ያኔ፤ ስለዚህ ይኼ የዳዊት መዝሙር 68፥31 ፕሮፌቲክ ነው። ወደፊት ስለሚሆን ነገር ነው የሚናገረው። አንድ አሉ ነው።

ሶፎንያስ አለ፤ ሶፎ. 3፥10 ላይ ያለው ስለ ኢትዮጵያ ሰዎች ነው የሚናገረው፤ በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ያሉት ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል ይላል፤ በጣም ግልጽ ነው አርሱ። ኢሳ. 18 አለ፤ ስለ ኢትዮጵያ ነው ሚናገረው፤ ምን ልላችሁ ነው እነዚህን ጥቅሶች የማነሳው፥ ይኼ እግዚአብሔር ጉብኝት አለው ለኢትዮጵያ፥ ጉብኝት አለ ብለን ምንናገረው እንዲያው ምኞታችንን አይደለም፤ እንደሱ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ፤ እንዲያው የምንመኘውን ነገር ምኞታችንን የምንሰብክ የሚመስላቸው ሰዎች አሉ፤ አይደለም። ምኞታችንን አይደለም የምንናገረው። ለኛም ግራ የሚገባ ነገር ነው፤ 'እንዴት? ከዚህ ሁሉ ሕዝብ በዓለም ዙሪያ ካለ፥ ከኛ ከተሻለ፥ በመንፈሳዊም በሥጋዊም፥ እንዲያው እግዚአብሔርን በመፈለግም እንኳን፥ በጸሎትም፥ በእግዚአብሔር ቃልም፥ ከኛ የተሻሉ ስንት ሰዎች እያሉ እንዴት ስለኛ እንደዚህ ይናገራል እግዚአብሔር? የማይመስል ነገር ነው' የሚለው ነገር ሁላችንንም ያስቸግረናል። ግን እሱ ስለሚያስቸግረን ብለን ደግሞ እውነቱን ዲናይ ማድረግ አንችልም።"

እኒህ መጋቢ ከሌሎቹ ኢትዮጵኞች ይልቅ በቃሉ ላይ ያተኮረ ነገር ነው የተናገሩት። ይህ በቃሉ ላይ ማተኮር አስተያየታቸውን ከብዙዎቹ ኢትዮጵኞች በጣም የተሻለ ያደርገዋል፤ ምክንያቱም በተጻፈው ቃል ዙሪያ መነጋገር እንችላለን። ይህንን አቀራረብ እንደ ዓይነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኢትዮጵኝነት፥ ተመልክቼዋለሁ።

እኛ ከሌሎች አገሮችና ከኛ ይልቅ የተሻሉ ከሚባሉት ሕዝቦች ተለይተን መታየታችን ትልቅ ጉዳይ ሆኖ ነው የቀረበው። ከኛ ከተሻሉት ተለይተን መታየታችንም ከተጠቀሱት ጥቂት ጥቅሶች በመነሣት ነው። ከጥቅሶቹ የተሻገረውና የኢትዮጵያውን መነቃቃት (revival) ወደር የሌለውና የመጨረሻ የሚያደርገው ግን ሕዝባውያን ትንበያዎች ናቸው እንጂ ጥቅሶቹ አይደሉም። በዚህ ክፍል የተነገሩት ኢትዮጵያን የተመለከቱና ከሌሎች ሕዝቦችና አገሮች ልዩ መሆኗ የተረጋገጠባቸው ሦስት ጥቅሶች ናቸው፤ መዝ. 68፥31፤ ሶፎ. 3፥10፤ እና ኢሳ. 18፥1። ጥቅሶቹንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትኩረቱን ኋላ አነሣዋለሁ።

መዝ. 68፥31 ትንቢታዊ ስለመሆኑ ድጋፎች ቆመውለታል። መዝሙሩን የጻፈው ዳዊት ነውና በተጻፈበት ዘመን ትንቢታዊ መሆኑን ግሱም ያስረዳል። መታለፍ የሌለበት ነጥብ ዐውዱና በጥቅሱ ውስጥ አሻሚ ቃላት ከኖሩ የቃሎቹ ትርጉሞች ናቸው። ዐውዱ የቃሉ የቅርብና ሰፊ ከባቢ ሲሆን አሻሚ ቃላት የሚባለው ራሱ በዚህ ጥቅስ የሚገኘውን መዘርጋትን እና የመሰሉ ድርብርብ ትርጉም ሊኖራቸው የሚችሉ ቃላት መኖር ነው። መዘርጋት ለአምልኮ ሊሆን ይችላል፤ ለመልካም ወይም ለክፉ ሥራም፥ ጠላትን ለመምታትም ተጠቅሶአል። ይህ ድርብርብ ትርጉም ምሳሌ ነው።

እንደ መጋቢ በቀለ በዚህ ጥቅስ የተጻፈው እጅ መዘርጋት አምልኮን፥ ይህ አምልኮም ከኢትዮጵያ የሚመነጭ ዓለም አቀፍ መነቃቃትን የሚያመጣ ነው። የመጋቢው ዋና አሳብ ከዚህ በፊት በተጻፈውና እንደገና ታርሞና ተሻሽሎ በተከለሰው መጽሐፋቸውም (ሪቫይቫል ኢትዮጵያና የመለከት በዓል) እንደተመለከተው በኢትዮጵያ አናት ላይ በፍጥነት ሊወድቅ የተንጠለጠለ የመነቃቃት ፍንዳታ ሊከናወን እንደቀረበና ይህ መነቃቃት ከኢትዮጵያ በመነሣት ዓለምን የሚያዳርስ ምናልባት በዓለምና በቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ነው። እዚህ የሚታየውም ይህ ነው።

እንዲህ ያለው የመጨረሻውና ከኢትዮጵያ መንጭቶ የዓለምን ፊት የሚሞላው መነቃቃት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትንቢት ይዘት ያለው ቢሆን ኖሮ በየመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጁና ሴሚነሪው የኮርስ ስም ተሰጥቶት በተስተማረ ነበር። በየአገሩና በየአብያተ ክርስቲያናቱም፥ ስለ መጨረሻው የፍጻሜ ዘመናት ትኩረት ሰጥተው በሚያስተምሩ ሊቃውንት ትምህርቱ በናኘ

ነበር። ይህ የኢትዮጵያው የመነቃቃት ፍንዳታ በኢትዮጵያውያን ተንባዮች ብቻ መነገሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ያደርገዋል። ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵኛ ያደርገዋል።



ቁስ በሪሁን መኮንን፤ "እኔም በውስጤ ያለው እይታ ምንድርነው? ወደፊት በሚመጡት ዓመታቶች በሥላሴ የሚያምኑ አብያተ ክርስቲያናት፥ አርቶዶክስ፥ ካቶሊክ አንግሊካን፥ ሜቶዲስት፥ ፕሮቴስታንቱም፥ ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ፤ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በልዩነታቸው ኅብረት አድርገው ሲያመልኩና እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ማየት ነው። እግዚአብሔር በሚቀጥሉት ዓመታቶች ይኼ ግንዛቤ ያላቸው ጳጳሳት፥ ቄሶች፥ የፕሮቴስታንት መሪዎች፥ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በሚቀጥለው ዘመን ላይ ተፈጥረው እናያለን። እግዚአብሔር ይህንን ያደርጋል። ሰዎች የወደዱትን ዓይነት አምልኮ፥ ቅዳሴ ቢፈልግ፥ በዝማሬ ዓይነት ደግሞ ቢፈልጉ በዚያ ዓይነት የሚያመልኩበት ዘመን ይመጣል፤ እሱ ደግሞ ለወንጌል ስርጭት በጣም አስፈላጊ ነው። ልዩነት ውበት ነው እንጂ ችግር አይደለም። ስለዚህ ይህንን ሆኖ የምናይበት ዘመን ቅርብ ነው።

ሁለተኛው በሚቀጥሉት ዓመታቶች ግን የሚሆነው ነገር፥ በሁሉም አቅጣጫ፥ በሰማያዊውም፥ በመሬታዊውም አቅጣጫ ለውጥ የሚያመጡ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚፈጠሩ ነው፤ እነዚህ አደጉ ምንላቸው አገሮች፥ ትላልቆቹ አገሮች መሠረታቸው ወንጌል ነው፤ በዚያ ብርሃን ነው ወደዚያ ከፍታ የወጡት፤ ስለዚህ ምስጢሩ አንድ ነው፤ ሰማያዊውና መሬታዊውን ትምህርት ማስተማራቸው ነው እንጂ የተለየ ወንጌል አይደለም እነርሱ ጋር ያለው፤ እኛም አገር በአብያተ ክርስቲያኑ በእርግጠኝነት ሰማያዊውንም መሬታዊውንም ትምህርቶች ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ትምህርቶች በምድራችን ላይ ማስተማር እንዲጀመር የእግዚአብሔር መንፈስ እየለቀቃቸው ያሉ ትምህርቶችና መረዳቶች አሉ። ስለዚህ በቅርብ ወደዚያ ዓይነት ሁኔታ እንገባለን፤ ያ ማለት፥ በኢኮኖሚው፥ በፖለቲካውና፥ በሶሻሉ ላይ ለውጥ የሚያመጡ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ይፈጠራሉ ማለት ነው፤ ፍትሕ የሚያመጡ፥ ረሃብን የሚሰብሩ፥ ሶሻሉ ደግሞ ሰላማዊ የሆነ፥ ለሕዝቦች በረከት የሆነ፥ ወደ ኋላ የማይጎትት፥ የተራቆተ ያልሆነ የሶሻል አወቃቀሮችን የሚፈጥሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ይመጣሉ፤ የፖለቲካው ሥርዓት የተረጋጋ ይሆናል፤ ሶሻል እስትራክቸሩ ውብ ይሆናል፤ ልመናን እናባርረዋለን፤ ገለል እናደርገዋለን፤ እግዚአብሔር ይህንን በቅርብ በሕዝባቸንና በምድራችን በአገራችን ላይ ይህንን ያደርጋል።"

በልዩነት ኅብረት ማድረግ? Unity in Diversity የሚሉት መሰለኝ። ልዩነታቸውን ጠብቀው ኅብረት የሚያደርጉ አርቶዶክሶችና ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች ማለት ልክ እንደ WCC (የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ) ያለ ማለት ነው። አንድ የሚያደርጋቸው የሥላሴ አስተምህሮአቸው ብቻ ነው። ለቤተ ክህነት ሞገስ እንደተባለው ያለ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና ስነ መለኮት ቢታቸውን ለማንና ለምን እንደሚለቅቁ ሳይታወቅ ግን ለቅቀው ኅብረት ለሚሉት ነገር እጅ ይሰጣሉ። ቢፈለግ ቅዳሴ ወይም ዝማሬ ተመርጦ ይመለካል። ግቡ ይህ ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና የትምህርት ንጽሕና አይደለም።

ለመላእክትና ማርያም፥ ለጻድቃንና ሰማዕታት ዙፋን ዘርግተው ለክርስቶስ በርጩማ እንኳ ከማይሰጡ ሃይማኖቶች ጋር በልዩነት ኅብረት ማድረግ የነገዋ ኢትዮጵያ ዕድል ፈንታ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስነ መለኮት በመስኮት ተወረወረ ማለት ነው። ያለዚያ ኅብረቱ የለበጣ ነው፤ የውሸትና የሸንገላ ነው። ኢየሱስ ብቸኛው መንገድ ነው ብሎ መግባባት ካልተቻለ፥ መጽሐፉ ሳይሆን፥ ትምህርቱም ሳይሆን ቅዳሴና ዝማሬው ከበረታ ሳይነካኩ ውሎ መግባት ይቻላል።

ዛሬ ትምህርት በዝማሬ መለወጡ አይደል ቤተ ክርስቲያንን እየሸረሸረ ያለው። ትምህርቱ እየቀረ፥ ዝማሬውም እየቀረረ መጣ። ቅዳሴና ዝማሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖልበቱ መልካም ሳለ ትምህርቱን እየዋጠ ትምህርቱም ሳይነካ ዝማሬውም ጭፈራ እየሆነ ነው። ጭፈራ ብቻ ሳይሆን ሽብር የሚመስልባቸው ቦታዎች ብዙ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ስፍራውን ከለቀቀ በኋላ በፈንታው፥ 'በሰማያዊውም፥ በመሬታዊውም አቅጣጫ ለውጥ የሚያመጡ ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚፈጠሩ' የተባለው ቦታውን ይይዛል። ለውጥ የሚፈጥሩ አዳዲስ ትምህርቶች አሁን የሉም፤ በቅርቡ ይፈጠራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያላስተማረው አዲስ ትምህርት ነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከዚህ በኋላ የሚፈጠረው? መሬታዊው ትምህርት የቀለም ትምህርት ዘርፍ ይሆን? መንፈስ ቅዱስ እየለቀቃቸው ያሉት ትምህርቶችና መረዳቶች እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ልጆች መሬታዊውን አገዛዝ እንዲወርሱ የሚያደርጉ ናቸው። ሰማያዊው ግዴታና የጌታ ትእዛዝ በመሬታዊው ተተካሳ!

ሶሻል እስትራክቸሩ ውብ፥ ፖለቲካው የተረጋጋ፥ ፍትሕ የሰፈነ፥ ረሃብ የተሰበረ፥ ድኅነትና ልመና ገለል ያሉ ይሆናሉ፤ እኒህ ሁሉ የሚሆኑት በቅርብ ነው። ይህ እና ሌሎቹም የጠቀሷቸው ነገሮች በዚህ ፍጥነት በኢትዮጵያ ሲፈጸሙ የሺህ ዓመቱን መንግሥት ሊመስል የቀረው ትንሽ ነው። ይህ የክርስቶስን ምጽአት የሚያስናፍቅ አይመስልም። ችግሩ ግን ይህ ሁሉ የሚሆነው በኢትዮጵያ ብቻ ስለሚሆን የሺህ ዓመቱ መንግሥት ሊሆን አይችልም። ግን ይህ ዶሚኒየን ቲዮሎጂ ነው።



መጋቢ ሚካኤል ወንድሙ፤ "እግዚአብሔር ከኛ በፊት በነበሩ በተለያዩ የእግዚአብሔር ሰዎች የተለያየ በኢትዮጵያ ላይ ሊሠራና ሊያደርግ ስላሰበው ነገር እግዚአብሔር ሲናገር ኖሯል፤ ከዚያም በኋላ ደግሞ በዚህ ዘመን እግዚአብሔር በተለያዩ ሰዎች አማካይነት በአገራችን ላይ ሊያደርግ ያሰበውን ነገር አሳቡን እየገለጠ ነው ያለው፤ በአጠቃላይ እግዚአብሔር በዚህ አገር ላይ ሊያደርግ ያሰበውን ነገር ጠቅለል አርገን ስናየው የመጀመሪያው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጸሙ ትንቢቶች ወይም በእግዚአብሔር ሕዝብ የሚፈጸሙ መልእክቶች አሉ፤ እነዚህ በእግዚአብሔር ሕዝብ ወይም በቤተ ክርስቲያን በኩል የሚፈጸሙ ትንቢቶች የመጀመሪያው ዋናና መሠረታዊ ትንቢት ብዬ እኔ የምቀበለው ትውልድ የመነሣቱ ጉዳይ ነው፤ ወይም ሰዎች የመነሣታቸው ጉዳይ ነው፤ እንግዲህ የእግዚአብሔር ተስፋ መፈጸም የሚጀምረው ቤተ ክርስቲያን ትውልድ ከመነሣት ሲጀመር ነው፤ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለአገር የሚጠቅም፥ የመሪነቱን ስፍራ የሚይዝ፥ ኢኮኖሚውን ለመቀየር የሚንቀሳቀስ፥ እንደገና በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የተለያየ የሃይማኖት እስትሮንግሆልዶችን የሚሰብር፥ በተለያየ አቅጣጫ የሚንቀሳቀስ ትውልድ እንደሚነሣ እግዚአብሔር ተናግሯል፤ ስለዚህ የመጀመሪያውና ዋናው ትንቢት ብዬ የማስበው ትውልድ የመነሣቱ ጉዳይ ነው። እንግዲህ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ላይ አመራሩን የሚቆጣጠር፥ የኢኮኖሚውን ስፍራ የሚቆጣጠር፥ የትምህርቱን ዓለም የሚቆጣጠር፥ እንደገና ደግሞ የንግዱን ዓለም የሚቆጣጠር፥ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱትን ዓለሞች የሚቆጣጠር ትውልድ ይነሣል በሚል ነገር እግዚአብሔር ደጋግሞ ተናግሯልና ይህን ነገር እየጠበቅን ነው፤ ስለዚህ እኔ በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ይፈጸማል ብዬ የማስበውና እግዚአብሔር የተናገረው ትንቢት እነዚህን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን እንቅስቃሴዎች የሚቆጣጠር ትውልድን የመነሣቱ ጉዳይ ነው፤ ጊዜው ደግሞ አሁን ነው፤ አሁን የተለያየ ለዓለም፥ ለምድር፥ ለአገራችን፥ ለትውልዳችን፥ ለሕዝቦችን የሚጠቅም ሥራ የሚሠራ በእግዚአብሔር የተቀባና፥ በእግዚአብሔር የቢቃ፥ እግዚአብሔር ውስጡን በኃይል የሞላው ትውልድ ይነሣል ብዬ አምናለሁ።"

የትውልድ መነሣት እና መቆጣጠር የእኒህ መጋቢ ዋና ቃላት ናቸው። በዚህች አጭር ንግግር እነዚህ ሁለት ቃላት አስራ ሦስቴ ተደጋግመዋል። መቆጣጠር ከላይ የተመለከትነው የመግዛት ወይም የዶሚኒየን ስነ መለኮት ዓይነተኛ ቋንቋ ነው። የዶሚኒየን ስነ መለኮት ነገሮች ሁሉ ከላይ ወደ ታች በተዋረድ እንዲለወጡ የሚጥርና ከፍተኛ የሥልጣን ጥም ሰዎቹን ከው አድርጎ እያደረቀው ያለ ትምህርት ነው።

የክርስቲያኖች በየመንግሥታዊው መዋቅር ውስጥ መሆን ጨውነትንና ሙብራትነትን ማናኘት ነውና መልካም ነው። ያልተስተዋሉት ሁለት ነገሮች ግን ይህ ስሌት በሰዎች ትንበያ እንጂ በቃሉ ትንቢት ውስጥ አለመገኘቱና ሰው በፍጥረቱ የሸኾነት ባህርይን አጥብቆ የሚፈላለግ፥ ካገኘ በኋላ ደግሞ የሚባልግ መሆኑ ናቸው።

ይህንን ቪድዮ ያዘጋጀው ሳክርድ ኢንተርናሽናል ዋና ግብ የትምህርቱን ዓለም መቆጣጠር መሆኑ በመግቢያው ላይ በአገልግሎቱ መሪዎቹ ተገልጧል። ይህ እዚህም የተጠቀሰው እየተጠበቀ ያለው የሚነሣው ትውልድ ተቆጣጣሪ ትውልድ ሲሆን ቁጥጥሩ አመራሩን፥ ኢኮኖሚውን፥ ትምህርቱን፥ ንግዱን የሚጨብጥ ነው። ስለ መንፈሳዊ ነገር የተነገረው ነገር ቢኖር የሃይማኖት እስትሮንግሆልዶችን የሚሰብር መሆኑ ነው።

ከላይ ያየናቸው ቁስ በልዩነት አንድነት የሚስማማ ሃይማኖት እንደሚኖር ሲተነብዩ እኒህ ደግሞ የሃይማኖት መዋቅሮች እንደሚሰባበሩ ተንብየዋል። ተገድዶ ሳይሆን መርጦ የመቀበል ወይም ጭራሹኑ ያለመቀበሉ ዕድል ክፍት መሆኑ መልካም ነው እንጂ የአንዱን ትንቢት ከሌላው ጋር ለማስታረቅ ልንዳክር ወይም ከአራምባ ቆቦ እየዘለልን ልንኖር እንገደዳለን።



መጋቢ ሐንፍሬ አሊጋዝ፤ ". . . በሄድኩበት የአፍሪካ አገሮች ሁሉ የምሰማው አንድ ነገር አለ፤ መሪዎች የሚሉት ምንድነው? 'እግዚአብሔር በረከት ከእናንተ እንደሚወጣ፥ እግዚአብሔርን ማወቅ ከናንተ እንደሚወጣ፥ እግዚአብሔርም ብዙ እንደተናገራችሁ፥ በቃሉም እንደተናገረ፥ ወንጌልም በናንተ አማካኝነት ወደ አፍሪካ እንደገባ፥ እንደገናም ደግሞ የአፍሪቃ ቀንድ እንደሆናችሁ እና የአንድ ነገር ኃይሉ ያለው በቀንዱ ውስጥ ነው፤ እናንተ የወንጌል ኃይል ናችሁ፤ ስለዚህ እናንተ ብትነሡ አፍሪካ ሁሉ ትባረካለች በመንፈሳዊ በረከት፤ እናንተን እየጠበቅናችሁ ነው፤' የሚል ንግግር ከብዙ መሪዎችና ከብዙ የአፍሪካ አገሮች መሪዎች ሰምቻለሁ። እና ያም ደግሞ እውነት ነው፤ አፍሪካ ራሷ የምትጠበቀው እኛን ነው፤ አገራችን የእግዚአብሔር ብዙ የተስፋ ቃል ያላት ምድር ናት፤ ብዙ ጊዜ ከ50 በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰች አገር ናት፤ ትልልቆቹ እንኳ ሚባሉት አገሮች እንደ አሜሪካ እንደሌሎቹ አገሮች እንኳን ያልተጠቀሱትን ያህል ምንም ያልተገኙትን ያህል በኢትዮጵያ ግን እግዚአብሔር ዓላማ እንዳለው ቀደም ብሎ በቃሉ ተናግሮ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናገኘዋለን። ስለዚህ ዓላማ ያላት ምድር ናት። ስለዚህም ደግሞ እግዚአብሔር መቼስ የሚሠራበት ዘመን አለው፤ እና ብዙም የድህነትም፥ የተለያየ ችግርም ብታልፍ አሁን ግን በፈታችን ያለው ዘመን በጣም እጅግ የተባረከና እጅግም ደግሞ ብልጽግና የተሞላበት ምድር እንደሚሆን፥ ብዙዎች ሰዎች እግዚአብሔርን በማወቅም እንደሚሞሉ እና ብዙ እንደሚያውቁ ነው እግዚአብሔር በልባችን ውስጥ የሚናገረው። እና ስለዚህ እንኳን ለምድራችን ለአገራችን ቀርቶ ለሌላው ዓለም ሁሉ የምትተርፍበት፥ በሁሉም ነገር ምትባረክበት ዘመን በጣም በጣም እጅግ ቅርብ ነው ብዬ ነው የማምነው።"

እጅግ መባረክ፥ እጅግ ብልጽግና በእጅግ በጣም ቅርብ ጊዜ!

ውድቀታችን አፍሪቃንም የያዘ ሆኗል ማለት ነው? ኢትዮጵያ አፍሪቃንም አዝላ ነው በተዳፋት እየሮጠች ያለችው ማለት ነው? የአፍሪካ መሪዎችና በተለይ፥ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንዲህ ከላይ እንደተጠቀሰው ካሰቡና ካመኑ ምንኛ ያሳዝናል! የጌታን የመጀመሪያ የወንጌል ትእዛዝ ችላ ብለው የኢትዮጵያ ሰዎች እንደሚነሡ እየጠበቁ ከሆነ እንዴት ያለ መወዘፍና ኪሳራ ውስጥ ናቸው!

ኢትዮጵያ የወንጌል ኃይል! የአፍሪቃ መሪዎች ኢትዮጵያን እንደ ቀንድ በማየታቸው ምንኛ ተታልለዋል! ወንጌል በኢትዮጵያ እንደተጀመረ ማሰባቸውስ እንዴት ያለ ስሕተት ነው፤ እነ ግብጽ፥ እነ ልብያ፥ እነ ቀሬና እንዴት ጠፉባቸው? እነ አትናቴዎስ፥ እነ ቆጵርያኖስ፥ እነ ጠርጡልያኖስ፥ ሌሎቹም የአፍሪቃ ልጆች ከኢትዮጵያ የተገኙ እኮ አይደሉም። ኢትዮጵያን እንደ መጀመሪያዋ ቀንድ ብቻ ሳይሆን እንደ መጨረሻው ዘመን ቀንድ መመልከትም ስሕተት ነው።

እነ አሜሪካ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲጠቀሱ መጠበቁ ወይም ያለመጠቀሳቸው ኪሳራ መሆኑ በምን መንገድ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ዘመን ዛሬ ያሉት 196 አገሮች ገና ሳይኖሩ እንዲታወቁና ስማቸው እንዲጻፍ መጠበቅ የለበትም። ያኔ የነበሩና ዛሬ መታሰቢያቸውም የሌለ አገሮች መኖራቸውም መረሳት የለበትም። ኢትዮጵያ ግን ከ50 ጊዜ በላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሷ እንዴት ነው? ከ50 ጊዜ በላይ? እንዲህ የታሰበው ምናልባት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የ21ኛው መቶ ኢትዮጵኛ ተንባዮች የተናገሩትም እንደ ጥቅስ ተደርጎ ተጨምሮበት ካልሆነ በቀር ወይም የተነገረው ስለ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ካልሆነ በቀር የምናነበበው መጽሐፍ ቅዱስ ተመሳሳይ ከሆነ ይህ አባባል ከአንድ መጋቢ የሚጠበቅ አይደለም።



መጋቢ ኢዮብ ማሞ፤ "እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ላይ ስላለው ዓላማ አስመልክቶ ነገሩን በሦስት መልኩ ነው ማየው፤ አንደኛ፥ እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪነቱ በአንድ በማንኛውም አገር ወይም በማንኛውም ጎብረተ ሰብ ወይም ኔሽን ላይ የራሱ የሆነ ዓላማ አለው፤ ዓላማም ስላለው ነው ያንን አገር እንደ አንድ ጎብረተ ሰብ እንደ አንድ አገር እግዚአብሔር የሚወልደው፤ ስለዚህ እንደ አንድ አገር ኢትዮጵያ፥ ማንኛውም አገር ተስፋ ቃል እንዳለውና በዚያች አገር ላይ ዓላማ እንደመኖሩ መጠን በኢትዮጵያ ላይም የተለየ ዓላማ እንዳለው አጥብቄ አምናለሁኝ።

በሁለተኛ ደረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስንመለከት እግዚአብሔር የተለያዩ አገሮችን አስመልክቶ በስም እየጠራ የበረከትን ቃል ተስፋ ቃል ሲናገር እንመለከታለን፤ ከነዚያ ጥቂት አገሮች መካከል ኢትዮጵያ መሆኗን ሁላችንም እናውቃለን፤ ስለዚህ እግዚአብሔር በቃል ላይ አጽንቶ ተስፋ የገባላት ስም ያኖሣለት አገር እንደሆነችና እግዚአብሔር ትልቅ ዓላማ እንዳለው ኢትዮጵያ ላይ በጣም አምናለሁ፤ ለምሳሌ ብንወስድ፥ መዝ. 68 መውሰድ እንችላለን፤ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር የምትዘረጋ አገር እንደሆነችና ያ ነገር በመፈጸም ላይ እንዳለ፥ እንደሚፈጸምም አምናለሁ። ሶፎንያስ ምዕራፍ 3 ላይ ስንመለከት የምልጃ መንፈስ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንዳለ፥ እንደሚታወቀው በጸሎት ሕዝባችን የተባረከ የሚጸልይ ሕዝብ እንደሆነ እናውቃለን ሁላችንም። ወደ አሞጽም ስንሄድ ምዕራፍ 9 ላይ የእስራኤል ልጆችን እናንተ እኮ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች ናችሁ ለኔ ብሎ ኢትዮጵያን እንደ ምዴል፥ እንደ ምሳሌ ሲያያትና ኢትዮጵያ ላይ ያለው አመለካከት ጥሩ እንደሆነ እግዚአብሔር ጥሩ አሳብ እንዳለው፥ ፍጻሜና ተስፋ ያለው አሳብ እንዳለው በኢትዮጵያ ላይ እንመለከታለን። እንግዲህ ከነዚህ በአንዱ አገር ላይ እግዚአብሔር ተስፋ እንዳለው ሁሉ፥ ዓላማ እንዳለው ሁሉ ለኢትዮጵያም አላት፤ በቃሉ ላይ ደግሞ በስሟ የተጠቀሰች አገር እንደመሆኗ መጠን የተስፋ ቃል አላት።

በተጨማሪ በዘመናችን በጆሯችን የሰማነው፥ በትንቢታዊ ሰዎች፥ በነቢያቶች በእግዚአብሔር መንፈስ ተነድተው በኢትዮጵያ ላይ እግዚአብሔር ዓላማ እንዳለው በልዩ ልዩ ቦታ ሲነገር እንሰማለን፤ በአገራችን ይነገራል፤ በአገራችን ነቢያቶች ተነግሯል፤ በየስፍራው፥ በየገጠሩ፥ በየከተማው እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ያለውን ዓላማ በሰፊው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አማካይነት በትንቢት መልክም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በሚል መልክም፥ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል እንኳ ሲሰበክ እግዚአብሔር በኢትዮጵያ ላይ ስላለው ዓላማ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ሲነዳ እንሰማለን። ስለዚህ እነዚህ ሦስት ማረጋገጫዎች አሉን ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ተስፋ ያላት አገር እንደሆነች እናምናለን፤ እንጠብቃለን። . . . የተስፋ ቃላችንን ለመጨበጥ ከሁሉ በላይ ብዬ የማምነው እንደ ኢትዮጵያዊ እራሴን ማክበርና ወኔን ማክበር እንደሚጠበቅብኝ አምናለሁኝ የተስፋን ቃል ወደ ፍጻሜ የሚያመጣ አንድነት ይሄ እንደሆነ አምናለሁ።"

ከእኒህ መጋቢ አስተያየት የተስፋው ቃል መጨበጫ ዋና ቁልፍ እንደ ኢትዮጵያዊ ራስንና ወገንን ማክበር ነው። አክብሮት መልካም ስነ ምግባር ነው፤ ግን ይህ የራስና የወገን አክብሮት ምግባር የተስፋና የትንቢት ፍጻሜ ቁልፍ መሆኑ በምን ሂሳብ ነው?

በቃሉ ውስጥ በስሟ የተጠቀሰች አገር መሆኗ ብቻውን ታሳቢ ሊያደርጋት ይገባዋል? በስም የተጠቀሱ ስንት አገሮች በቃሉ ውስጥ አሉ? በስም የተጠቀሱ ስንት ሰዎች በቃሉ ውስጥ አሉ? በአንጻሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስም ያልተጠቀሱ ስንት ወንጌልን ሮጠው ያሮጡ አገሮችና ሕዝቦች አሉ? ስማቸው ማን መሆኑን የማናውቅ ስንቶች ናቸው ወንጌልን ይዘው እየሮጡ የወደቁ? ቁም ነገሩ በስም መጠቀስና በስም መጠራት ወይም አለመጠራት ከሆነ ስተን እናስታለን። ኩሽ የሚለው ቃል በቃሉ ውስጥ መጻፍና ኮሪያ የሚለው አለመጻፍ በክርስቶስ መንግሥት የሚፈጥረው ለውጥ የለም። ማንም ክርስቶስን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ከሞት በኋላ፥ 'ይኸው አገሬ፥ ዜግነቴ በመጽሐፍ ተጽፎአል' ብሎ መከራከር አይችልም።

እግዚአብሔር ሉአላዊ አምላክ ነውና፥ ምድርና በላይዋ ያለው ፍጥረትም ሁሉ የራሱ ነውና፥ እንደ ፈጣሪና እንደ ጌታ ለሚሠራው ነገር ዓላማ ባይኖረው እንጂ ቢኖረው አያስደንቅም። ዓላማ አለው፤ አሳብ አለው። ግን የኢትዮጵያን ዓላማውን ልዩ አድርገን ማየት እኛን የተለየን አድርገን ማየት ነው። እኛን ከሌላው ሁሉ የዓለም ሕዝብ ልዩ የሚያደርገን ምንም ነገር የለንም። ከዓለም 7.3 ቢሊየን ሕዝብ የኛ 100 ሚሊየን ማለት ከ73ሺህ ሕዝብ አንድ ማለት ነው። የቁጥር ጉዳይ ያነሣሁት ልዩ ያለመሆን ለማሳየት ነው።

እኒህ መጋቢ ግን ልዩ መሆናችንን ቃሉም እንደሚናገር አሞ. 9፥7ን በመጥቀስ፥ "የእስራኤል ልጆችን እናንተ እኮ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች ናችሁ ለኔ" በማለት ኢትዮጵያን እንደ ሞዴል፥ እንደ ምሳሌ ሲያያትና ኢትዮጵያ ላይ ያለው አመለካከት ጥሩ እንደሆነ . . ." በማለት ተናግረዋል። ጥቅሱን መጋቢው እንዳሉት ማየትና በተጻፈበት አጻጻፉ፥ "የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?" ማለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

በርካታ ኢትዮጵኞች ዐውዱን እንደሌለ በመቁጠር ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ከእስራኤል ይልቅ የተወደደች፥ የቀረበች፥ በእቅፉ ውስጥ ያለች መሆኗን መናገሩ እንደሆነ አድርገው ያስተምራሉ። ግን ዐውዱን ገፍተን ከመንገድ ካላወጣነው ኢትዮጵያውያን የእቅፉ ልጆች መሆናቸውን ሳይሆን እጅግ የራቁ መሆናቸውን ጠቅሶ እስራኤልም ከእርሱ መራቋን መናገሩ ነው። ይህ ጥቅስ በበርካታ ኢትዮጵኞች ዘንድ ብርቅዬ የእንቁልልጭ መጫወቻ ነው። ግን የኢትዮጵያ አጠቃቀስ በእቅፉ መሆኗን ሳይሆን እጅግ መራቋን የሚናገር ነው። ይህንን ጥቅስ

እንደገና እመለስበታለሁ። ኢትዮጵኞች ኢትዮጵያን ሸላልመውና የገና ዛፍ ይመስል አንቆጥቁጠው ከሚያቀርቡበት ጥቅሶች አንዱ ይህ ነው።



መጋቢ ፋሲል ጌታቸው፤ ". . . ወደ መንፈስ ቅዱስ አሳብና እግዚአብሔር ለኔ በግሌ ወደተናገረኝ ነገር ስመጣ ምንም እንኳን በተደጋጋሚ ተስፋ ያላቸውን ድምፆች ከመድረክም ከሌሎችም ወገኖች ከራሴም ብሰማ፥ እንደዚሁም ደግሞ ሕልምና ራዕይ የሚባሉ ነገሮች አሉና እነሱ በብዙ በተደጋጋሚ ወደ ሕይወቴ ሲመጡ አያለሁ፤ ከነዚህም ውስጥ ተስፋ የሚኖራት፥ ጨለማውን ዘመን አልፋ ብርሃን ላይ የምትወጣ፥ በዚህች ምድር ያለች ቤተ ክርስቲያን ለሌላው ለአፍሪካ ምድር እንደዚሁም ደግሞ ለዓለም ሚሽነሪዎችን የምትልክ ወይም ደግሞ የምታሰማራ አገር እንደምትሆን ይሄ ተስፋ በራዕይም በሕልምም በመንፈስ ቅዱስም ድምጽ የተነሣ በውስጤ ሞልቷል አሁንም እያየን ነው ያለነው። . . . ለአፍሪካ ፈውስ፥ ለአፍሪካ ሰላም፥ ለአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት መበርታት፥ መጠንከር እግዚአብሔር የሚጀምረው ከዚህች ምድር ነው ብዬ አምናለሁ።"

ብርሃን ላይ የምትወጣ፥ የአፍሪካ ፈውስና ሰላም፥ የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት መበርታትና መጠንከር የሚጀምረው ከዚህች ምድር ነው። ለምን ከዚህች ምድር? መልሱ ራእይ፥ ሕልም፥ እና የመንፈስ ቅዱስ ድምጽ። አንዳንድ ሰዎች ዛሬም ሕልምን እንደተጻፈው ቃሉ ያህል በአክብሮት የሚያዩ አሉ። ከቃሉ ውጪ የሆነ ማናቸውንም ነገር መስማት ከተጻፈው ቃሉ ይልቅ ወደዚያ ወደሚታየውና ወደሚሰማው ነገር የሚያቀርብና የሚያስጠጋ ነው።

አሁንም እየታየ ያለ ነገር መኖሩ ተባለ እንጂ የሚታየው ነገር ምንነት አልተነገረም። ከራሳቸው ቤተ ክርስቲያን ወደ አፍሪካና ወደ ዓለም የተላኩ ከኖሩ ለአብነት ቢያቀርቡ መልካም ነበር። ከስንት የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ነው ወደ ዓለምና ወደ አፍሪካ የወንጌል መልእክተኞች የተላኩት? መላክ ሲባልም ላኪዋ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋቸውን እያደረገች ማለት ነው እንጂ በኢኮኖሚ ስደት ወጥተው በየአገሩ የተበተኑትን ክርስቲያኖች እንደ ወንጌል መልእክተኞች መቁጠር ስሕተት ነው። ስደተኞችን ከቆጠርን ኢትዮጵያውያን የዓለሙን ፊት ሞልተናል፤ ግን የተላክን ወይም ሐዋርያት ነን? የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን እያደረጉ ናቸው?

ምናልባት ይህ ገና ወደፊት የሚደረግ ነገር ነው ተብሎ ሊታለፍ ይችላል። ቢሆንም እንኳ ኢትዮጵያ ለወንጌል የበኩሏን አስተዋጽዖ እንዳደረገች ቢቆጠርላት እንጂ ከምድሯ የመጀመሩ አሰላል እንዴት ነው? የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ስትጀመርም ከኢትዮጵያ እንዳልጀመረች ሁሉ መበርታትና መጠንከሯም ከኢትዮጵያ እንደሆነ መታሰቡ ራስን ማግነን አይሆንም ወይ? አንዳንዶች የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት እናት ያደርጓታል። ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስና አሁንና ከዚህም በኋላ ለአፍሪካ ወንጌል መዳረስና የቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ ብዙዎች ያደረጉትንና የሚያደርጉትን ልፋት የራስ ማድረግ ስግብግብነት አይሆንም?



መጋቢ ዮናስ ሰይፉ፤ "ጌታን ከተቀበልኩበት ጊዜ አንሥቶ ነው እግዚአብሔር ስለ ምድሪቱ ሲናገረኝ የነበረው። ማለት ጌታን ከተቀበልኩና ከተለወጥኩ በኋላ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አንሥቶ በውስጤ በምድሪቱ ላይ ትልቅ ጉብኝት፥ ትልቅ ተሐድሶ፥ መነቃቃት እንደሚመጣ እግዚአብሔር ይናገረኝ ጀመረ፤ እና ግን ከብዙ ዓመት በኋላ አሁን ነው ይሄ ጉዳይ ዝም ብሎ በውስጤ ሚቃጠል ብቻ አሳብ ሳይሆን፥ ወይ ደግሞ አንዳንድ ነቢያት በአገር ፍቅር ስሜት ተነሥተው የሚናገሩት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በቃሉ ውስጥም የተቀመጠ፥ በግልጽ የተጻፈ ጉዳይ መሆኑን ያወቅኩት አሁን አሁን ነው። በርግጥም እግዚአብሔር ተናግሮኛል፤ ግን በቃሉም ላይ ተናግሯል እግዚአብሔር በተለያዩ ስፍራዎች ላይ ከመጨረሻው ዘመን ጋር፥ ከፍጻሜ ዘመን ጋር በተገናኘ መልኩ ከዚህች ምድር ላይ እግዚአብሔር ሠራዊትን እንደሚያስነሣ፥ ይሄ ሠራዊት ደግሞ እስከ ምድር ጫፍ የሚሄድ ሠራዊት እንደሆነ፥ ወንጌል የሚሰበክ እንደሆነ እግዚአብሔር ተናገረኝ። በዚያም የተነሣ ነው መጽሐፍ የጻፍኩት . . . ።"

እኒህ መጋቢ፥ "አንዳንድ ነቢያት በአገር ፍቅር ስሜት ተነሣስተው የሚናገሩት ጉዳይ . . ." ያሉት አገላለጽ የሚናገረው ነገር አለ። እንዲህ ያሉ 'ነቢያት' አሉ ማለት ነው። የአገር ፍቅር ትንቢት ያናግራል ማለት ነው? ያናግራል። እንዲህ ያሉ ነቢያት ነበሩም? አሉ? ነበሩም፤ አሉም።

እኒህ መጋቢ የተናገሩት ቃል ራሱ በአገር ፍቅር ስሜት ተነሣስተው የተናገሩት አለመሆኑ በምን ይታወቃል? ይህ ያሉት ነገር በቃሉ ውስጥ የሚገኝ ነገር ነው? እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ከፍጻሜ ዘመን ጋር በተገናኘ መልኩ ከኢትዮጵያ ሠራዊትን እንደሚያስነሣ ተናግሯል? እኒህ መጋቢ እንደተናገረ ነው የገለጡት። የዚህ ኢትዮጵያዊ ሠራዊት መነሣት የት ይሆን የተጻፈው? ቢጻፍ ኖሮስ መነገር፥ መነበብ አልነበረበትም? ኢትዮጵኞች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብቡት 'ኢትዮጵያ' በሚባል በልዩ ትእዛዝ በተሠራ መነጽር ይመስላል። ይህ መነጽር 'እስራኤል' ወይም 'ቤተ ክርስቲያን' ወይም ይህን የመሰለ ቃልን ሲያዩ፥ 'ኢትዮጵያ' እያለ የሚለውጥ መነጽር ይመስላል።

እኒህ መጋቢ በጠቀሱት የጻፉት መጽሐፍም ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ በሚነሣው ሪቫይቫል ውስጥ ቀዳሚ፥ ፊት መሪና ዋነኛ ተዋናይ ትሆናለች ይላሉ።[20]



ሐዋርያ ዘላለም ጌታቸው፤ "እግዚአብሔር ስለ ኢትዮጵያ በግሌ ትውልድን እንዳስነሣለት ተናግሮኛል፤ እና ትውልድን እንዳስነሣለት ሲናገረኝ የመጀመሪያው አሳብ የትውልዱን አይምሮ ለክርስቶስ ወደ አባቶች አመለካከትና ለወንጌል ሥርዓት መቀየር ነው። ያ ማለት ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱሳችን በመጨረሻ ዘመን እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሠራ ያሰበውን የመጨረሻ ዘመን ሥራ በኢትዮጵያውያን እንደሚሠራ በነቢያት አፍ አስቀድሞ ስለተናገረ ስለዚህ የነቢያቱን ትንቢት አካል የሚያስይዝ ትውልድ በዚህ ምድር ላይ እንደሚነሣ ነው የተናገረኝ። ሌላው የትውልዱ አነሳስና ሥርዓት የሚሆነው በትንቢተ ኢሳይያስ እንዲሁም በሶፎንያስ፥ በመዝሙረ ዳዊት ላይ አስቀድሞ አባቶች ስለ መጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንደተናገሩት፥ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ይኸውም የክርስቶስ ሙሽራ የምትሆነው የሚያዘጋጀው ወይም የሚማልደው ትውልድ ከኢትዮጵያ እንደሚነሣ ነው። ያንን ለማዘጋጀት ደግሞ እግዚአብሔር አስቀድሞ በዚህ ምድር ባለነው ሰዎች ትንቢታዊ ድምጽ

[20] እምነትና ፍርሃት፤ ገጽ 157።

ለእያንዳንዳችን አምጥቷል፤ ደግሞም ትውልዱ አሁን እየተዘጋጀ ያለ ይመስለኛል፤ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ትውልድ የሚሆነው በኔ እምነት፥ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የተሰፋ ቃል በእምነት አምነው በመውጣት መውረስ ነው፤ ይሄ ማለት ምንድነው? ከቤተ ክርስቲያን ወይም ከሕዝቡ ሚጠበቀው እምነት ነው፤ ከእምነት ጀርባ ሁልጊዜ መገለጥ አለ፤ መጽሐፍ ሲናገር አባቶቻችን የተመሰከረላቸው በእምነት ነው፤ ከእምነታቸው ጀርባ ደግሞ የእግዚአብሔር አስቀድሞ የተነገረው የትንቢት ቃል አካል ሲይዝ እናያለን፤ ስለዚህ የተነገረንን የትንቢት ቃል አምነን ሁላችን በኅብረትና በአንድነት ክርስቶስን በማስቀደም ሁሉም የየራሱን የተነገረውን የትንቢት ቃል አካል ሲያስይዝ ሙሉ የሆነው የእግዚአብሔር እይታ ይገለጣል ብዬ አምናለሁ።

ስለዚህ ስለ ኢትዮጵያ ያለን የተስፋ ቃል፥ ኢትዮጵያ በዓለም ዙሪያ ለሚነሣው ለመጨረሻው ዘመን ሪቫይቫል የመነሻ ስፍራ እንደሆነች ነው፤ ይሄንንም ኢየሩሳሌምን ምሳሌ ማድረግ እንችላለን፤ መጀመሪያ ኢየሩሳሌም ለዓለም ሁሉ ለሚሄደው የትንሣኤ ምስክርነት የመነሻ ቦታ ነበረች፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ለትንሣኤው የመጠቅለያ አካል የመነሻ ቦታ እንደሆነች እግዚአብሔር በነቢያት አፍም እንደዚሁም በትንቢት መጽሐፎች ላይ አስረግጦ ተናግሮናል። ለዚህ ይሄንን ነገር ለማስፈጸም ነው እግዚአብሔር በዚህ ትውልድ መሐል ያስነሣን ብዬ አምናለሁ።"

በእኒህ ሐዋርያ፥ 'እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊሠራ ያሰበውን የመጨረሻ ዘመን ሥራ በኢትዮጵያውያን እንደሚሠራ በነቢያት አፍ አስቀድሞ ስለተናገረ . . .' ተብሏል። ነቢያት የተባሉት በቃሉ ውስጥ የተጻፉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናነኛቸው ነቢያት ናቸው ወይስ የዘመናችን ተንባዮች? በቃሉ የተጻፉት ከሆኑ ቀላል እኮ ነው፤ የተጻፈውን መጥቀስ ብቻውን በቂ ነው። ኢሳይያስ፥ ሶፎንያስና ዳዊት መጠቀሳቸው ነቢያቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ያስመስላል፤ ውዥንብሩ ግን ይህ ጉዳይ ከክርስቶስ ሙሽራ ዝግጅት ጋር መቆራኘቱና ሙሽሪቷን የሚያዘጋጀው ትውልድ ኢትዮጵያዊነት ነው።

እንደ እኒህ ሰው አገላለጥ፥ 'የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ይኸውም የክርስቶስ ሙሽራ የምትሆነው የሚያዘጋጀው ወይም የሚማልደው ትውልድ ከኢትዮጵያ እንደሚነሣ ነው።' ይህ ግራ የተጋባ አነጋገር ነው። የኢትዮጵያ ትውልድ የቤተ ክርስቲያን ወይም የሙሽሪቱ አዘጋጅ ከሆነ ትውልዱ ራሱ ከሙሽርና ውጪ ነው ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያንን የሚያዘጋጀው ቤተ ክርስቲያን ያልሆነ ትውልድ ነው ማለት ነው። እንደሚታወቀው በሠርጉ ቀን ሙሽራው ሙሽሪቷን ነው የሚወስደው እንጂ ሚዜዎችን አይደለም። ሙሽሪቷን የሚያዘጋጁት ኢትዮጵያውያን ከሆኑ እነርሱ ራሳቸው ሚዜ ናቸው ማለት ነው? ወይስ አጃቢዎች ናቸው? ክርስቶስ ሙሽሪቱን ሲወስድ ሚዜዎቹና አጃቢዎቹ ሸኝተው ኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖሩ የሚቀሩ ናቸው ማለት ነው? ኢትዮጵኞች ኢትዮጵያ ውስጥ ሊቀሩና ሊቀበሩ ቢመኙና ቢያስመኙ አያስገርምም፤ አገሪቱ ምድረ ገነት ሆናለቻ! ይህ የተዘባረቀ ትምህርት ነው። ሐዋርያው ከዚህ በፊት የጻፉትን ዝብርቅርቁ ዓለም የሚል መጽሐፍ ሳነብብ መጽሐፉ ራሱ የተዘበራረቀ ሆኖ እንዳገኘሁት ያለ ዝብርቅርቅ ትምህርት ነው እዚህም የሚታየው። ይህ የተዘበራረቀ ትምህርት ብቻ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ የሆነ ትምህርት ነው። እንዲህ ያሉ ጽሑፎችና ንግግሮች የተማሩባቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች የሚያስጠይቁ ወይም ጨርሶውኑ ከቃሉ አስተማሪዎች ያልተማሩ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

በዘመናችን ኢትዮጵኛ ተንባዮች እንጂ በቃሉ ውስጥ እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ለኢትዮጵያውያን የሰጠበትን ስፍራ አይገኝም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ የመጨረሻ ዘመን ሚና የተጻፈ ነገር የለም። እንኳን ስለ ኢትዮጵያ ስለ እስራኤልም የቤተ ክርስቲያን ሚና የተጻፈ ነገር አናገኝም። ቤተ ክርስቲያን አይሁድ ወይም አሕዛብ ሳትሆን ከሁለቱም የተሠራች አዲስ አካል ናት።

'ኢየሩሳሌም ለዓለም ሁሉ ለሚሄደው የትንሣኤ ምስክርነት የመነሻ ቦታ ነበረች፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ለትንሣኤው የመጠቅለያ አካል የመነሻ ቦታ እንደሆነች. . .' ለትንሣኤው የመጠቅለያ አካል? ራሱ ቃሉ ለማደናገር የተፈጠረ ቃል ይመስላል፤ ምክንያቱም ቃሉም አሳቡም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም። የትንሣኤ መጠቅለያ አካል የሚባል አንድ ሕዝብ የለም፤ ኖሮም አያውቅም። አንዳንድ ሰዎች ቃላትን አጋጥመው መንፈሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስመስለው የቀመሩ ይመስላቸዋል። ይህ መቀመር ሳይሆን በቃላት መቆመር ነው።



መጋቢ መርድ ኃይሉ፤ "እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ ተናግሮኛል፤ ሆኖም ግን አጠቃላይ የሆነ አሳብ ከእግዚአብሔር የሰማሁትን በአጭር እናገራለሁ። እግዚአብሔር በዚች ምድር ላይ በጣም ትልቅ ዓላማ አለው፤ ከዓላማዎቹ ዋነኛው ነገር፤ በሚቀጥለው ዘመን ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሆኑነገሮች አሉ፤ አሁን በፊታችን አጭር የሆነ የጨለማ ጊዜ አለ፤ ይሄ የጨለማ ጊዜ ፍርድ ሚካሄድበት ጊዜ ነው፤ ፍርድ ይደረጋል በኢትዮጵያ ውስጥ፤ በቤተ ክርስቲያንም በምድሪቱም ላይ ፍርድ አለ፤ የእግዚአብሔር ፍርድ ይመጣል፤ ይሄ የሚደረግበት ምክንያት ለሚቀጥለው ለወንጌል ሥራ እግዚአብሔር አመቺ ነገር ለመፍጠር ነው ይሄንን ያደርጋል፤

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተወሰኑ ፍርዶች አሉ፤ በመንግሥት ደረጃ፥ በአገር ደረጃ ፍርዶች አሉ፤ የሚመጡ ፈተናዎች አሉ፤ በኢትዮጵያ ላይ ሚመጡ ፍርዶች አሉ፤ ከዚያ በኋላ ግን እግዚአብሔር ታላቅ ሪቫይቫል ያስነሣል፤ የሚነሣውም ሪቫይቫል በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሣ ያየሁትን ራእይ ልናገር፤ ያየሁት ራእይ እንደዚህ ነው፤ በጣም ትልቅ በሆነ ሰፊ በሆነ ሜዳ ላይ ብዙ የኢትዮጵያ አገልጋዮች ቆሻሻ ልብስ ለብሰው አያለሁ፤ በጣም የተቦጫጨቀ ልብስ፤ ድንገት ግን ከሰማይ ትልቅ ብርሃን ይበራና ያንን ልብስ ያወልቀዋል፤ ያንኑ ልብስ ደግሞ ሌላ ልብስ ያለብሳቸዋል፤ ጌታ ሆይ ምንድነው ይሄ ነገር ስለው፥ እንደገናም ይሄንን ነገር እየጠየቅኩት እያለሁ እግዚአብሔር ትልልቅ ትልልቅ ቀለበቶች በሁለት ጣታቸው ውስጥ ያስገባል፤ ይሄ ብቻ አይደለም፤ እንደገና እግዚአብሔር የተለየ፥ የተለየ በጣም ሚያንጸባርቅ ነገር ያለው ልብስ ነው ልብሱ፥ እና እግዚአብሔር ሆይ ምንድነው ይሄ ስል፥ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ፥ እነዚህ በኢትዮጵያ ላይ የሚነሡ አገልጋዮች ናቸው፤ እነዚህ አገልጋዮች ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ድሃ፥ ተቸግሮ ሚያገለግል አገልጋይ አይኖርም፤ አንድ። ሁለተኛ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ከዚህ በኋላ አገልጋይ የሚከበርበት ዘመን ነው፤ ሁለት። ሦስተኛ ደግሞ፥ ነፋስ ይመጣና እነዚህን አገልጋዮች ለሁለት ይከፍላቸዋል፤ ግማሾቹ አላያቸውም ይሄዳሉ፤ ግን እነዚህ የቀሩት ሜዳ ላይ የቀሩትን ጌታ ምን አለኝ ስለነዚህ ሲናገር፥ እነዚህ በዚህ ምድር ላይ የሚቀሩ አገልጋዮች ናቸው፤ እነዚያ ግን የሌሉቱ በዓለም የሚበተኑ የኢትዮጵያ አገልጋዮች ናቸው አለኝ። . . . እነዚህ የኢትዮጵያ አገልጋዮች በተነሡ ጊዜ ነው የክርስቶስ ምጽአት ሚመጣው።

የኢትዮጵያ አገልጋዮች በዓለም ደረጃ፥ ዓለምን ሲሞሉ የክርስቶስ ምጽአት ይመጣል። የክርስቶስን ምጽአት የሚያቀርበው አለኝ እግዚአብሔር፥ የዚህ ምድር አገልጋዮች ናቸው አለኝ። . . . ከእንግዲህ ወዲህ በምድሬ ላይ፥ በዚህች ምድር ላይ ታላቅን እሳት አነድዳለሁ፤ ታላቅን ሪቫይቫል አስነሣለሁ፤ ቤቴን እሠራለሁ፤ አገልጋዮቼን አመጣለሁ፤ ሕዝቤን አጠናለሁ፤ ታላላቅ ተአምራቶችን በምድሩ ላይ እገልጣለሁ ነው ያለኝ፤ ታላቅ ለውጥ ይካሄዳል በኢትዮጵያ ላይ፥ የፖለቲካም ለውጥ ይካሄዳል ትልቅ ለውጥም ይካሄዳል፤ በጣም ሃብታም አገር፥ በጣም መልቲቢሊየነር የሆነች አገር ትሆናለች ኢትዮጵያ፤ ከሃብቷ ብዛት፥ ከኩበሯ ብዛት፥ እግዚአብሔር ከሚያደርግላት ቸርነትና ርኅራኄ ብዛት ይህቺ ምድር በጣም ትልቅ አገር ነው ምትሆነው፥ በጣም። የብዙ አገር ሰዎች፥ ነጮች እዚህ መጥተው መቃብራቸው እዚህ ይሆናል፤ ጥቁሮች መጥተው፥ ቢጫ ሕዝቦች መጥተው፥ መቃብራቸውን እዚህ ያደርጋሉ፤ ዜግነታቸውን ይለውጣሉ፤ ሞታቸውን እዚህ ያደርጋሉ፤ መቃብራቸውን እዚህ ያደርጋሉ፤ ብዙ የዓለማችን ሰዎች፥ ብዙ ትልልቅ የተባሉ ሃብታሞች፥ ብዙ ትልልቅ የተባሉ አዋቂዎች መቃብራቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ ያደርጋሉ። እዚህ ለመሞት፥ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለመሞት፥ እራሳቸውን ይለውጣሉ። ይሄ በኢትዮጵያ ላይ ይሆናል።"

'በኢትዮጵያ ውስጥ ተቸግሮ የሚያገለግል አገልጋይ አይኖርም፤ አገልጋይ ይከበራል።' ይህ ቀደም ሲል ከተባለው የመጋቢ ዳዊት ትንበያ ጋር ይዛመዳል። አገልጋዮች ሳይቸገሩ ቢያገለግሉ መልካም ነው። ቀድሞውኑ በብልጽግና ወንጌል የሰከሩ አገልጋዮችና የሚያስተምሩት አሳች ትምህርት ኢትዮጵያንም እያመሳት ይገኛልና፤ ደግሞም ብዙዎችን በአቋራጭ የመበልጸግ ምኞ እየመታቸው ይገኛልና አገልግሎትንና ምኞትን ማቆራኘት ተገቢ አይደለም። በምኞትም ባለመመኞትም አገልግሎት ይደረጋል። ከችግር የጸዳ አገልግሎት ተስፋ አልተሰጠም፤ ጌታም፥ እነ ጳውሎስም ተመኞቶአቸው አላገለገሉም። ዋጋው ይህ ከሆነ፥ ይህ ወንጌልን ማስቀረት የለበትም።

ዛሬ ተመኞቶአቸው ከውጊያው ሜዳ የኮበለሉትን ስናይ ተመኞቶ አለማገልገል ሳይመች ከማገልገል ጋር ለምርጫ መቅረብ እንደሌለባቸው ማጤን አያቅትም። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ወንጌሉን ለሌሎች ለታመኑ ሰዎች አሳልፎ እንዲሰጥ አደራ ካለው በኋላ፥ *እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል* ነበር ያለው፤ 2ጢሞ. 2፥3። በመከራ ውስጥ ችግር አለ። ተቸግሮ የሚያገለግል አገልጋይ ከሌለ አገልግሎት መኖሩ ያጠራጥራል። ይህ የብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎችን አይመለከትም። የሚያገለግሏቸው ሰዎች ጎድናቸውን ያስቅጥሩ እንጂ እነርሱ ቦርጭ እንደ ቦርሳ አንግቶ መሄድ መብታቸው ነው። 'ተቸግሮ የሚያገለግል አይኖርም' ለሚባለው ግን የብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች ምሳሌ መሆን አይችሉም።

እንደ እኒህ መጋቢ ራእይና ትምህርት የክርስቶስ ምጽአት መቼ መሆኑን እርግጠኛ ሆነን መናገር እንችላለን ማለት ነው። የሚመጣበትን ጊዜ እንኳ ባይሆን የማይመጣበትን ጊዜ መናገር እንችላለን። ቢያንስ አሁንና በሚቀጥሉት በርካታ ዓመታት ጌታ እንደማይመጣ እርግጠኛ እንሆናለን። ስለዚህ ክርስቶስ አሁን ይመጣል ብሎ መስበክ ውሸት ነው ማለት ነው። 'እነዚህ የኢትዮጵያ አገልጋዮች በተነሡ ጊዜ ነው የክርስቶስ ምጽአት የሚመጣው!' የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ በሰው ትንቢት ሊሻር ነው ማለት ነው! ከዚህ በፊትና በዘመናችንም ክርስቶስ በዚህ ጊዜ ይመጣል እያሉ ያልተሣኩ ቀኖችን የሰጡ ሐሰተኛ ተንባዮች እንደነበሩ ሁሉ፥ 'በዚህ ጊዜ ወይም ይህ ሳይሆን አይመጣም' የሚሉም አሉ።

የእኒህ መጋቢ አነጋገር ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ከሆነ መጀመሪያ የክርስቶስ ምጽአት ይሆንና ከዚያ በኋላ ነው የዓለም ታላላቆች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢትዮጵያዊ ሆነው መቃብራቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያደርጉት? እንዲህ ካልሆነም በረከቱ ይቀድምና ክርስቶስ ይመጣል።

አንዳንድ ኢትዮጵኞች በተለይ ስለ ኢትዮጵያ ሲናገሩ እግዚአብሔር የቀጠሮ ባህር መዝገብ እንዳለውና የዚህ መዝገብ ዐቃብያን የሆኑ ያህል ነው ስለሚቀጥሉት ዓመታት የሚናገሩት። የኢትዮጵያ አገልጋዮች የክርስቶስን ምጽአት የሚያቀርቡ አገልጋዮች ሆነው ቀርበዋል። የኢትዮጵያ አገልጋዮች ባይኖሩስ? ባይኖሩማ ክርስቶስ አይመጣም ነበር!!

ሃብቷ፥ ክብሯ፥ መልቲቢሊየነርነቷ፥ የሃብታሞች መካነ መቃብርነቷ የርኅራኄው ምስክርነት ነው ሆኖ የቀረበው። ኢትዮጵያ መጥቶ መሞትና መቀበርን ጥቂት ኢትዮጵኞች

አስምረውበታል። በአገራችን አንዳንድ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች አጥንታቸው ደብረ ሊባኖስ ቢጣል መንግሥተ ሰማያት የመግባታቸውን ቲኬት እንደቆረጡ ይቆጥራሉ። በክርስቶስ ሆኖ የትም መሞትን ሳይሆን ኢትዮጵያ ሄዶ መቀበርን የከበረ አድርገው የሚያዩት መጥተው ኢትዮጵያ የሚቀበሩት ሃብታሞች ሳይሆኑ መቀበራቸውን የሚያዩላቸው ኢትዮጵኞች ናቸው። ምናልባት ይህንን የሚያዩት ኢትዮጵኞች ቀድሞ ደብረ ሊባኖስ የሚደረገው ባህል ውስጥ ያደጉና ያ የሰረጸባቸው ይሆናሉ። ለክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር መሞትና መቀበር እንጂ የበድናቸው በኢየሩሳሌም ወይም ጎፋ ሠፈር መቀበር፥ ወይም ጭራሽ ሳይቀበሩ መቅረት ለውጥ የለውም። ለኢትዮጵኞች ግን ይህ ትልቅ ጉዳይ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶታል።



ወንጌላዊት ውዴ ገ/ማርያም፤ "ከተናገረኝ አንዱ፥ የሚያሳየኝ ነገር ቢኖር፥ ላም ለጥጃዋ ወይም የምትታለብ ላም ወተት ለሚያናራት ሰው እንደምትሰጥ የምትታለብ የወተት ላም፥ እንደገና ደግሞ ሰጥታ ወተቱን ቅፈታውን ለጥጃዋ እንደምትደብቅ ለዚህ ምድር እግዚአብሔር ቅፈታን ያስቀምጣል። እግዚአብሔር ተናግሮኛል፤ ይሄ ቅፈታ ደግሞ ላሚቷ ለጥጃዋ ደብቃ እንደምትደብቅ እግዚአብሔር ለዚህች ምድርና ለሕዝቡ የደበቀው ሰማያዊና ምድራዊ በረከት እንዳለ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ላሚቷ ጥጃዋን እንደምትሻ፥ በትንፋሿ ጥጃዋን እንደምታውቅ፥ ጥጃዋ ደግሞ እናቷን እንደምታውቅ፥ እግዚአብሔር ደግሞ ሕዝቡንም ያውቃል፥ ሕዝቡም ምድሩን ያውቃል፤ ሕዝቡም እግዚአብሔርን ያውቃል። ስለዚህ እግዚአብሔር በሚሠራበት ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን ያውቃል፤ ሕዝቡም እግዚአብሔርን ያውቃል። ለዚህች ምድር ቅፈታ እንዳለው እግዚአብሔር ተናግሮኛል። ስለዚህ ሰዉ እግዚአሔርን መፍራት እንዳለበት፥ እግዚአብሔርን ማክበር እንዳለበት፥ ይህንን የተሰጠንን ተስፋ፥ እግዚአብሔር የተናገረንን ተስፋ፥ ሕዝቡ እግዚአብሔርን መጠበቅ፥ እግዚአብሔርን መፈለግ፥ በቅድስና በእግዚአብሔር ፊት መመላለስ እንዳለበት ይሄንን ነገር ያፋጥነዋል፤ እግዚአብሔር ለምድራችን፥ ለሕዝባችን ያስቀመጠው ቅፈታ አለው።

እንደ እኒህ ወንጌላዊት ምክር እግዚአብሔርን መፈለግና በቅድስና መመላለስ ቃሉም የሚለው ቢሆንም ይህ ምንን እንደሚያፋጥን ግልጽ አይደለም።

እኒህ ወንጌላዊት ምስላዊ በሆነ መልኩ የጥጃንና የላምን ወተት ማስቀረት በማሳየት እግዚአብሔር ቅፈታ እንዳለው ተናግረዋል። ቅፈታ በመጽሐፍ ቅዱስ ለእስራኤል የተነገረ ቃል ነው። በአዲስ ኪዳንም ቃሉ ሲጠቀስ ስለ እስራኤል ነው የተነገረው፤ ሮሜ 9 እና 11። ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ ግን ቤተ ክርስቲያን መላዋ አካል እንጂ እግዚአብሔር ብዙው ጠፍቶ ጥቂቱ የሚቀር የአካሉ ቅፈታ የለውም።



ሐዋርያ ንጉሴ ሮባ፤ "ለረጅም ዘመን በክርስትና ስም ነው ስትጠራ የኖረችው፤ ይሁን እንጂ ውስጡ ሲመረመር ክርስትናን ከጎፋች አገር አንዷ አገር ናት። ጳውሎስ ሲናገር ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን ነው ሚለው በ1ቆሮ. 16፥22 ላይ እና የተረገመ ይሁን የሚለውን እንደ ቀላል የምናየው አይደለም። እርግማን ኢኮኖሚን ይይዛል፥ ትምህርትን ይይዛል፤ እርሻውን ይይዛል ሁሉን ነገር ነው ሚይዘው፤ ስለ እርግማን ሲናገር የእግዚአብሔር ቃል፥ ሰማይን ናስ አደርግብሃለሁ፤ ምድርን ብረት አደርግብሃለሁ ይላል። እና ስለኛ አገር ሲነገር በጣም ብዙ ፖቴንሻል፤ ማለት ሪሶርስ እንዳላት ነው ሚነገረው በሌላው ዓለም ሲተያይ የማይተናነስ ነገር

ነው ያለው፤ ስለዚህ፥ ይኼ ብረት ሆኗል አሁን ይኼ እርግማኑ። . . . በክርስትና ስም ለረጅም ዘመን ነው ያጭበረበርነው፤ ስለዚህ ብዙ ነገራችን ተይዟል፤ አሁን ስናየው ግን ብዙ ትውልድ እግዚአብሔርን በመፈለግ ላይ ነው የሚገኘው፤ . . . ስለዚህ በጣም ትልቅ አገር ካገኘሁት አንዱና፥ በቅርብ ጊዜ እኔ ኤሮፐ ሄጀ ነበርና በተለያዩ አገሮች ተዘዋውሬአለሁ፤ የዛሬ ሁለት መቶ፥ ሦስት መቶ፥ አምስት መቶ ዓመት እግዚአብሔርን የሚፈሩ ምድሪቱ ላይ እንዳሉ ከተማው ላይ የሚታይ ነገር አለ፤ ቸርቾች አሉ ዛሬ ማይመለከባቸው፤ ትልልቅ በዕብነ በረድ የተሠሩ ሕንጻዎች እና እነሱን አሁን ስታያቸው ከኛ የበለጠ የእንሰሳ ሥራ እየሠሩ ነው፤ ግን ያ ሺህ ትውልድ የሚለው የአባቶቻቸው በረከት፥ ዛሬም ጭምር ኪዳኑን እየበሉ ነው።

እኛጋ ስትመጣ ግን በክርስትና ስም ለረጅም ዘመን ነው ያጭበረበርነው፤ ስለዚህ ኢኮኖሚው አንዳንድ ነገር ሲታቀድ ሲመታ ነው ምናየው፤ . . . ይሄ ትውልድ እግዚአብሔርን የመፈለግ፥ እግዚአብሔርን የማምለክ ነገር ነው እያየን ያለነው፤ ስለዚህ ባጭሩ፥ ቅርብ ጊዜ እንኳን የማየው ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰማያዊ ዕቡነ በረድ፥ በዓለም የማይገኝ፥ ሰኔ ወር ነው ኤክስፖርት አድርጋለች ተብሎ ሚነገረው። ይሄ ዱሮ አልነበረም ወይ? ነበረ፤ ለ60 ዓመት የነዳጅ ፍለጋ እየተደረገ ነው፤ አሁን ፍንጭ እየተገኘ ነው፤ እየተሰማ ነው ያለው፤ ይሄ ምን ማለት ነው፥ በምድር ውስጥ በዚህ በመርገም ምክንያት የተዘጉ ነገሮች እንኳን እየተከፈቱ ነው፤ . . . ስለዚህ ይሄ ኢኮኖሚውንም ምድሪቱንም መዋጀት ይጠይቃል፤ ትልቅ ትልቅ መንፈሳዊ ጉልበት ይጠይቃል፤ የኢያሪኮን መርገም፥ ትዝ ይላችሁ ከሆነ፥ ኢያሪኮ ተረግማ ነው የነበረው፤ ሕዝቡ ያሻናል፥ ይለፋል ይደክማል፤ ግን ለኤልያስ ችግሩን አልነገረውም፤ ኤልያስ ትልቅ ቅባት የነበረበት ሰው ነው፤ እሳት ከሰማይ ያወረደ ያለገለ ሰው ነው፤ ከሱ እጥፍ ቅባት ተቀብሎ የመጣውን ኤልሳዕን ነው ለመጀመሪያ ጊዜ . . . ብዙ ሰው ይጨነግፋል፥ ደስተኛ አይደለም፤ ብዙ ሰው ያለቅሳል እና ምን ትላለህ ሲሉት፥ በዚያው ቅባት፥ ገብዶሃል አሁን በሽታን የመፈወስ፥ ምናምን ምናምን ብቻ አልነበረም የሱ፥ ኢኮኖሚውንም ጭምር የሚለውጥ ቅባት ነው በሱ ላይ የነበረው እና . . . ምንጩ ሄዶ ፈወሰው ይላል፤ ያ ምድር ሙሉ በሙሉ ተፈወሰ።

ስለዚህ አሁንም፥ መጀመሪያ እግዚአብሔርን ማምለክ ነው፤ እግዚአብሔርን ማምለክ ስንጀምር የእግዚአብሔር ቅባት በኛ ሕይወት ውስጥ መለቀቅ ይጀምራል፤ ከዚህ ቅባት የተነሣ ነው የረጅም ዘመን ቀንበራችን ሚሰበረው፤ እግዚአብሔርም ቃል እሱን ነው ሚናገረው እና፥ ከቅባቱ የተነሣ ቀንበሩ ይሰበራል ነው ሚለው። . . . ይሄ መጽሐፍ ጴንጤዎች ብቻ ያመጡት ሳይሆን ኢትዮጵያ ክርስትና ስትቀበል፥ አንድ ነገር ሳነብ ካገኘሁት ነገር፥ ሰባ ሰዎችን ወደ ኤሮፐ ልካ ነው መጽሐፍ ቅዱስን አስተርጉማ ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስትናን ተቀብያለሁ ብላ በመንግሥት ደረጃ ይሄ መጽሐፍ ተቀባይነት አግኝቶ እዚህች አገር ላይ ሊሠራ የጀመረው እንጂ አሁን የተወሰኑ ትውልዶች ያመጡት ነገር አይደለም። ስለዚህ ይሄ መጽሐፍ ራሱ ለረጅም ጊዜ ሣይነበብ ኖሯል . . . ይሄን ከዚህ አንጻር ሳየው ምድሪቱን አሁን ኃይለኛ፥ ኃይለኛ፥ ልክ ዘጸ. 23፥25 ላይ፥ ብታመልከኝ እህል ውኃህን እባርክለሁ፥ በሽታን ከመካከልህ አርቃለሁ፥ የዘመንህን ቁጥር እሞላለሁ፥ ባንተ መካከል የሚጨነግፍ ወይም መካን አይኖርም። አሁን ይሄ ትውልድ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ወደ ማምለክ ሲመጣ በምድሪቱ ያለው ይሄ እርግማን እየተገፈፈ ስለሚሄድ በኢትዮጵያ ትልቅ ነገር ይኖራል ብለን ነው፥ እኔ ብዬ ነው የማስበው ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ሳየው። ይሄ ሙሉ ልብ አለኝ፤ ደግሞም እየታየ ያለ ነገር ነው ፊዚካሊ እየታየ ያለ ነገር ነው፤ እንግዲህ በአጭሩ ስለ አገራችን ያለኝ ነገር ይሄ ነው፤ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።"

እኒህ ሐዋርያ እግዚአብሔር የተናገራቸውን ሳይሆን ከቃሉ በመነሣት የደረሱበት ቢሆንታዊ (conditional) ድምዳሜ ነው። ሰው በክርስቶስ ሲሆን እንደ አዲስ ፍጥረትነቱ በሕይወቱና በኑሮው የሚከሰቱ ድንቅ ለውጦች ይኖራሉ። ይህ እውነት ነው።

ቀደም ሲልም ስለ ትውልድ መርገም ትምህርት በመጠኑ ያነሣሁ ቢሆንም እዚህም በጥቂቱ ልድገመው። የኪዳናቱን ልዩነት አለማወቅ ኢትዮጵኞች ኢትዮጵያን እንደ ብሉይ ኪዳኗ እስራኤል እንዲቆጥሩ ያስገደዳቸው አንድ ስሕተት ነው። አንዳንድ ኢትዮጵኞች ኢትዮጵያን

እንደ ዳግማዊት እስራኤል ወይም የእስራኤል ምትክ አድርገው የሚያዩት ከዚህ የተነሣ ነው። እኛ የብሉይ ኪዳን የኪዳኑ ሕዝብ አይደለንም። እኛ አይሁድ ሳንሆን አሕዛብ ነን። የበረከቱ ተካፋዮች የሆንነው እንደ አገርና ሕዝብ ሳይሆን በነጠላና በክርስቶስ ሆነን ነው። ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን እግዚአብሔር ከአይሁድ ጋር በሲና እንደገባው ባለ ኪዳን ውስጥ እንዳሉ አድርጎ ማሰብ ስሕተት ነው። የሦስትና አራት ትውልድን እርግማን በቀጥታ የምንወስድ ከሆነ ሌሎቹንም የብሉይ ኪዳን ተስፋዎች ከድንጋጌዎቹና ከሕግጋቱ ሁሉ ጋር መውሰድ ሊኖርብን ነው። ኢትዮጵያን እንደ ዳግማዊት እስራኤል የሚያዩት ይህን ማስደረግ ይቃጣቸዋል።

የመርገም አስተምህሮ አዲስ ኪዳናዊ አይደለም። በሕግ ስር ሳይሆን በክርስቶስ ውስጥ ነን፤ በክርስቶስ ስንሆንም መርገምንና ኩነኔን በመፍራትና በመሳቀቅ የምንኖር አይደለንም። አገርን በሕግ ስር ማድረግ ወይም ክርስቲያኖችን በሕግ ቀንበር ስር ማድረግ የአዲስ ኪዳን ትምህርት አይደለም። በክርስቶስ ላለን ኩነኔ የለብንም። በክርስቶስ ውስጥ ስንሆን የሦስትና አራት ትውልድ እርግማን አያገኘንም። ካልሆንንም የሺህ ትውልድ በረከት መንፈሳዊ ድነትን አይሰጠንም። ምድራዊ፥ አካላዊ፥ ቁሳዊ፥ ዓለማዊ ብልጽግናን ልንወርስ ወይ ላናገኝ ግን እንችላለን። ይህንን የትውልድ መርገም ብለን አዲስ ኪዳን በማያስተምረው መልኩ ክርስቲያኖች ላይ መጫን ስሕተት ነው። ክርስቲያን ያልሆኑትማ ገና ከመርገም በታች ናቸው፤ መፍትሔውም ወንጌል መሆኑ እውነት ነው።

የኢያሪኮ ጭንገፋ በኤልሳዕ መገፈፍ እጥፍ ቅባት ስለነበረው ነው ማለት ቀደም ሲል የተጠቀሰው የተዛባ የቅባት ትምህርት ነው። እንደ መርገም ሁሉ ቅባትም መስመር የለቀቀ ትምህርት ነው። ይህ ቅባት የሚል ነገር የኤልያስና ኤልሳዕ ታሪክ ውስጥ አለመኖሩን ሳንረሳ ነው። መንፈስ የሚለው ቃል ተለውጦ ይሆን ቅባት የተባለው? መንፈስ የሚለውን ቃል ሁሉ ቅባት ካልነው የተሳሳተ ትምህርት ውስጥ ልንገባ እንደምንችል ማሰብ አይከብድም። ከቅባቱ የተነሣ ቀንበሩ ይሰበራል የሚለው ቃል እንደገና ተጠቅሶአል፤ የሌለ ቃልን ትልልቅ ሰባኪዎች ሲጠቅሱ ቃሉ ያለ እየመሰለን ልንወናበድ እንችላለን። የኢያሪኮን ውኃ መፈወስ ጉዳይ ወደ ኤልያስ አምጥተውት ኤልያስ፥ 'የኔ ቅባት አናሳ ስለሆነ ይህን አልችልም' ብሎ ቢሆን ይህ ቅባት ከሚሉት ነገር ጋር በተያያዘ ነበር።

ይህ ቅባት ኢኮኖሚን የሚለውጥ ቅባት ተብሎአል፤ ሰማያዊ ዕቡነ በረድ፥ ነዳጅ፥ ኢኮኖሚ፥ ፊዚካሊ . . . የሐዋርያው ትኩረትም ጉዳዩ ከመርገም ጋር ተያያዘ እንጂ እንደ ብዙዎቹ የኢኮኖሚው ጉዳይ ነው። በምድር ውስጥ ያሉ ማዕድናት፥ ዕብነ በረድ፥ ነዳጅ መውጣት የመርገም ሽረት ከሆነ ከመካከለኛው ምሥራቅ መርገም ተገፍፏል ማለት ነው። በዓለም ያሉትን ነዳጅና ዕብነ በረድ ላኪ አገሮችን መንፈሳዊ ይዞታ ስናይ ይህ አነጋገር ጥቂትም የማያስኬድ ሆኖ እናገኘዋለን። የነዳጅ ክምችት በአገራችን ተገኝቶ እኛም ላኪ ብንሆን ይህ ቁሳዊና ምድራዊ እጦታችንን ሊቀርፍልን ይችል ይሆናል እንጂ መንፈሳዊነታችንን አያጎለብተውም፤ ወይም የመንፈሳዊነታችን ምልክትም አይሆንም። ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን የበረከት በረት የሚያደርገው የብልጽግና ወንጌል ስሕተትና የኢትዮጵኞች ትምህርት አብረው መጠመዳቸው በግልጽ ይታያል።

ሰባ ሰዎች ወደ ኤሮፕ ተልከው መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉመው ያንን መጽሐፍ ኢትዮጵያ ተቀብላ ክርስትናን ተቀብያለሁ ብላ በመንግሥት ያወጀችበት ትርጉም የትኛው ይሆን? 'ይሄ

መጽሐፍ' ብለው ሐዋርያው በእጃቸው የያዙት መጽሐፍ የ1954ቱን ትርጉም ይመስላል። ይህ ትርጉምም ሆነ የግዕዙም ትርጉም ራሱ እስከ 200 ያህል ዓመታት በፊጂ ጊዜ ውስጥ እዚሁ በአገራችን የተተረጎመ እንጂ 70 ሰዎች ኤሮፕ ሄደው የተረጎሙትና ያመጡት አይደለም። ከ1954ቱ በፊት የነበረው የመጀመሪያው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራም የታወቀና የተጻፈለት ነው።[21] ይህ ያልተጨነ ጉዳይ 'ሳነብ ካገኘሁት' ተብሎ እንደ ቀላል መቅረብ የለበትም። ይህ ዋና ጉዳይ ባይሆንም እዚያም እዚህም እግረ መንገድ የቀረበ ነው። ኢትዮጵያ ከ50 ጊዜ በላይ ተጠቀሰች እንደሚባለው 70 ሰዎች ኤሮፕ ሄደው ተረጎሙትና አምጥተው አገሪቱ ክርስትና ተነሣች ማለት በቀላሉ መወርወር የሌለባቸው አሳቦች ናቸው።

* * * * *

ከዚህ የቪድዮ ዝግጅት ቀደም ሲል እንዳልኩት በጠቅላላው ከ35 በላይ ሰዎች የተጠየቁ ሲሆኑ ወደ 30 የሚጠጉትን ከአጫጭር ምላሾች ጋር እዚህ አካትቻለሁ። በቀጣዩ ክፍል ኢትዮጵያንና ኢትዮጵኝነትን በተመለከተ የተጠቀሱትን ጥቅሶች እንመለከታለን።

[21] በዚህ ጉዳይ ላይ ቀዳማዊ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በሚል ርእስ የጻፍኩትን ይመልከቱ።

3. ኢትዮጵኝነትና ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ

በኢትዮጵኞች የተነገሩትን በኢትዮጵያ የሚደረገውን ጉብኝት፥ "እግዚአብሔር ሊጀምር ነው፤ በእጅግ ቅርብ ጊዜ ይሆናል፤ በኔ ጀነሬሽን ይፈጸማል . . ." የሚሉት ቃላት የሚያሳምሙ ናቸው። በእግዚአብሔርና እስካሁን ወንጌሉን ለማዳረስ ደፋ ቀና እያሉ ባገለገሉ ሰዎች ላይ የተወረወሩ የንቀት ቃላት ይመስሉኛል። እግዚአብሔር እስካሁን ምንም እንዳላደረገ፥ በአፍሪቃም፥ በዓለምም ሥራውን ሊጀምር ገና ከእንቅልፉ እየተነሣ እንዳለ ያስመስላል። ተኝቶ የኖረበት አልጋም ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሆነ ሲነሣ ጫማውን አጥልቆ፥ ሸሚዙን ሰቅስቆ፥ ሥራውን የሚጀምረው ከዚሁ ከኢትዮጵያ ከኛው ቀየ እንደሆነ ያስመስላሉ።

ለራሳቸው ይህንን ለሚናገሩ ተናጋሪዎችም ወንጌልን ለመስበክ ዋጋ የከፈሉትን ያለፉትን ቅዱሳን እያዋረዱ ያሉ ይመስለኛል። ይህ ወይ ታሪክን ያለማወቅ ነው። ያለዚያም በድፍረት እየተናገሯቸው ያሉት እንዲህ ያሉት የፌዝ ቃላት ለራሳቸው የሰጡትን ልዩ ስፍራ የሚያሳይ ነው። ሁለቱም ስሕተት ነው፤ በዘመናት ውስጥ ወንጌል ወደኛ እንዲደርስ እየለፉ ያለፉት ቅዱሳን ምንም እንዳላደረጉ መቁጠር ውለታቢስነት ነው። ራስን እቆጥ ላይ መስቀልም ኋላ መውረጃ ማጣት እንዳይሆን ያስፈራል። እቆጥ ላይ የወጡት አንዳንዶቹ ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ተናጋሪዎቹ አገሪቱንም ነው አፈናጥረው ያወጧት። ያለፈውን ትውልድ የሚንቅ ትውልድ ወደ ፊት እያየ ወደ ኋላ የሚሄድ ትውልድ ነው።

የእግዚአብሔር ሥራ አሁን አልተጀመረም። ወይም ገና ሊጀምር አይደለም። የሚጀምረውም ከተናጋሪዎቹ አንዱ ልክ የመጀመሪያው የወንጌል ስርጭት ከኢየሩሳሌም እንደጀመረ ይህኛው ከኢትዮጵያ እንደሆነ እንደተናገረው አይደለም። ይህ ከብጉንጅ የከፋ እብጠት ነው። ኢትዮጵያ የመጨረሻው ዘመን ኢየሩሳሌም የሆነችው በተሳሳቱ ኢትዮጵኛ ተንባዮች አእምሮ ብቻ እንጂ በቃሉ ውስጥ አይደለም።

ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነትን በተመለከተ ከስሕተት ለመጠበቅ መስተዋል ያለባቸው በርካታ ነጥቦች አሉ። አራት ዋናና ትልልቅ የምላቸውን ነጥቦች ቀጥሎ አወሳለሁ።

1. ብዙ ጥቅስ?

አንድ አገር በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቀሰች ማለት ያቺ አገር ልዩ አገር ናት ማለት አይደለም። ብዙ ጊዜ ተጠቀሰች ማለትም ብዙ በረከት የተሰፈረላት ናት ማለት አይደለም። ከላይ ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል አንዱ፥ አሜሪካና ራሽያ ራሳቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልጎ ለማግኘት ትግል ላይ መሆናቸውንና እኛ ኢትዮጵያውያን ግን የተጠቀስንባቸውን ቦታዎች ለመፈለግና ለማግኘት ችግር እንደሌለብን ተናግሮአል። ብዙ ጊዜ ስለተጠቀስን ቃሉን ገለጥ ስናደርግ ራሳችንን እንደምናገኝ ተናግሮአል። ብዙ ጊዜ መጠቀስን በማውሳት አንድ ተናጋሪ ኢትዮጵያ ከ50 ጊዜ በላይ መጠቀሷን ተናግሮአል። አንዳንዱ አጠቃቀስ ለመናገር ሳይሆን ለመስማትም ያሳፍራል። ከ50 ጊዜ በላይ እንደተጠቀሰች የታሰበው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ

የ21ኛው መቶ ኢትዮጵኛ ተንባዮች የተናገሩትም እንደ ጥቅስ ተደርጎ ተጨምሮበት ነው ማለት ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ብዙ አገሮች ይገኛሉ። አገሮቹ ወይም ሕዝቦቹ ተጠቀሱ ማለት ወይም የመጠቀስ ብዛት ግን ሞገስ ማግኘት አይደለም። ቀደም ሲል እንዳልኩት የኢኮኖሚ ብልጽግና የመለኮታዊ ሞገስና ቡራኬ ምልክት እንዳልሆነ ሁሉ ማለት ነው። በቃሉ ውስጥ የመጠቀስ ብዛት የበረከት ዋስትና አይደለም። ጥቂት የአገሮችና ሕዝቦች ምሳሌ እንውሰድ። **ባቢሎን** ከ260 በላይ ተጠቅሳለች። **ፍልስጥኤም** እና ፍልስጥኤማውያን ከ250 በላይ፤ **ሶርያ** እና ሶርያውያን ከ120 በላይ ጊዜ ተጠቅሰዋል። **አሞን** (የአሁኗ ዮርዳኖስ) 120 ጊዜ፤ **ሊባኖስ** 65 ጊዜ፤ **ግብጽ** እና ግብጻውያን ከ650 በላይ ጊዜ ተጠቅሰዋል። ታዲያ እነዚህ አገሮች እንዴት አሉ? ብዙ ስለተጠቀሱ ብዙ የተባረኩ ናቸው ማለት ነው? ባቢሎንና ፍልስጥኤም ዛሬ የሉም። ፓለስታይን እና የመጽሐፍ ቅዱሷ ፍልስጥኤም አንድ አይደሉም። ፓለስቲና ሲሪያ የሚለው ስያሜ ሮም ኢየሩሳሌምን ከደመሰሰች በኋላ አገርነቷን ለማጥፋት የፈጠሩት ስም ነው። ሃይማኖታዊ ገጽታቸውን ብቻ እንኳ ብንመለከት ግብጽ 90%፤ ሶርያ 90%፤ አሞን (ዮርዳኖስ) 92%፤ ሊባኖስ 60% ሙስሊም አገሮች ናቸው። ብዙ መጠቀስ በረከት አድርገን ከጠቀስን መልኩ ይህ ነው።

እስራኤል ስንቴ ተጠቀሰች ማለቱ አስፈላጊ አይመስለኝም፤ የጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ስፍራ ናትና መቁጠርም የተገባ አይደለም። የራሷን የእስራኤልን ሃይማኖታዊ ይዞታ እንኳ ብንመለከት ለዘብተኞቹን ጨምሮ 97% ይሁዲዎች ናቸው። ክርስቲያኖች ከ2% ያነሱ ናቸው። ስደታቸውም ቀላል አይደለም። ጥቂት ያይደሉ መሢሓዊ አይሁዶች (አይሁድ ክርስቲያኖች) አሉ። በነዚህ ሰዎች ዘንድ እንኳ በኢትዮጵያውያን መካከል እንደሚነገረው ያለ ትንበያ ተሰምቶ አይታወቅም። የተጻፈው በጊዜው እንዲፈጸም በመጠበቅ ነፍሳት መሢሑን ያውቁት ዘንድ የድርሻቸውን ለመወጣት በወንጌል ማሳ ተሰማርተው ያገለግላሉ እንጂ ያለ እነርሱ ሕዝብ እንደሌለ ከኛ ወዲያ ላሳር ብለው አያውቁም። ዓለም የሚጠብቀው እኛን አይሁዳውያንን ነው፤ እኛ የእግዚአብሔር ፑልፒት ነን፤ መፍትሔ የሚመጣው ከኛ ነው፤ የከፍታ ዘመን ሊወድቅብን ነው፤ . . . አላሉም። አይሁድ ክርስቲያኖችም እንኳ ይህን ሲሉ አይደመጥም። ክርስቲያን ሲሆኑና መሢሑን ሲቀበሉ የአይሁድ ትምክህት ካባቸውን አውልቀው ወርውረው ነው። የኛዎቹ ደግሞ የተወረወረውን አንሥተው የኛን ቀለም ቀብተው ለብሰውት ከኛ ወዲያ የእግዚአብሔር መሣሪያ ይሉናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀስ ብቻውን የእግዚአብሔርን ሞገስ የማግኘት ጉልህ ምስክር አይደለም። ብዙ ጊዜ መጠቀስ ብቻውን የሚውለበለብ ባንዲራ አይደለም። ግብጽ የተጠቀሰችበት ከኛው ጋር ሲነጻጸር 15 ለ 1 መሆኑ ነው። እኛ የኛን 40 ያህል ጊዜ መጠቀስ እንቁልልጭ ካልን ባቢሎን ወዴት አለች? ለጥቂት አስሮች ጊዜያት መጠቀስ ብቻውን ውኃ አያነሣም። ዋናው ጥያቄ ስንቴ መጠቀስ ሳይሆን እንዴት መጠቀሱ ነው። ዛሬ፥ እንኳን ኢትዮጵያ እስራኤልም በእግዚአብሔር የደኅንነት ዕቅድ ውስጥ የተለየ ስፍራ አልተሰጣትም። አንድ ቀን ያ ሕዝብ ይታሰባል፤ ሮሜ 9-10። ደኅንነት ነጠላ እንጂ ብሔራዊ አይደለም፤ ሆኖም አያውቅም። ዛሬም ወደፊትም ግን አይሁድም አሕዛብም የምንድንበት መንገዱ አንድ ነው፤ እርሱም ኢየሱስ ነው።

ቃሉ ለሚለው ነገር ጆሮአችንን በጓጉንቸር ሸጉረን ተንባዮች የሚሉትን ብቻ ትንሺት ቀዳዳ በስተን የምንሰማ ከሆንን ማንንም ሳይሆን ራሳችንን እያሳትን ነን። ራሳችን ከሳትን ደግሞ ሌላውን ለማሳት የመጀመሪያውን ርምጃ ቀድሞውኑ ተራምደናል ማለት ነው። ቢያንስ አንድ ወይ ጥቂት ሰዎችን ሳናስት ወይም ሳናደናግር አንቀርም። ከዚያ የሚቀጥለው የቃሉ ትምህርት ሳይሆን ፕሮፓጋንዳ ነው። ኢትዮጵኝነትም ሆነ ክርስቲያናዊ ኢትዮጵኝነት ፕሮፓጋንዳ ናቸው።

2. ዐውድ የሚሉት ነገር አለ።

ምንም ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲጠቀስ አጠቃቀሱ እንዴት ነው ማለት ጥበብ ነው። ቆርጦ መደረት ወደ ስሕተት ይጥላል፤ ዐውድ የሚባል ነገር አለ። ጥቅሱና የተጻፈው ምንባብ ታሪካዊ/ትረካዊ ቃል ከሆነ ታሪክ ነው የተነገረው። በጊዜው የሆነ ወይም ያለፈ፥ የሆነ ጉዳይ ነው። እንደ ዜና ወይም ዜና መዋዕል የሆነ ትረካ ነው። ተስፋ ይዘን የምናውለበልበው አይደለም። ታሪክነት እንጂ ተስፋነት የለበትም። ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን የሚሉት ቃላት ከተጠቀሱባቸው ክፍሎች 84%ው ታሪካውያን፥ ዜናውያን፥ እና መልክዓ ምድራዊ ትረካውያን ናቸው። በጊዜው የሆነውን ብቻ የተናገሩ ናቸው እንኳን ተስፋነት ምንም ትንቢትነትም የለባቸውም። ወደ ቀጣዩ ወይም ወደ አሁኑ ዘመን ወይም ወደፊት ወደሚሆነው ነገር አመልካቾች ከቶም አይደሉም።

ለምሳሌ፥ አርጤክስስ ከሕንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ባሉ 127 አገሮች ነገሠ ማለት ስለ ኢትዮጵያ የተነገረ ቃል ነው ብሎ ማውለብለብ ስሕተት ነው። ይህ ስለ ኢትዮጵያ ሳይሆን ስለ አርጤክስስ ታላቅነት የተነገረ ታሪክ ነው። ይህ ቃል ስለ ኢትዮጵያ የተናገረው ነገር ቢኖር ኢትዮጵያ በቃሉ ውስጥ ስለተጠቀሰች ገናና አገር መሆኗ ሳይሆን የፋርስ ቅኝ ግዛት እንደነበረችና የግዛቱም የድንበር አገር እንደሆነች ነው። ይህ ቅኝነት ደግሞ የሚነፋት ቱልቱላ አይደለም፤ መሆንም የለበትም። ለአምስት ዓመታት ጣሊያን የያዘችን ዘመን እንደማያኮራው ያህል ይህም አያኮራም።

ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ብለው ኢሳ. 18 እና ሶፎ. 3 ሲጠቅሱ ማዶ የሚለውን ቃል ሰርዘን፥ ኢትዮጵያ ብቻ ብለን ማንበብ የለብንም። ይህ ጤናማ አነባበብ አይደለም። ነቢያቱ ማዶ ሲሉ ቃላት ተትረፍርፈውባቸው፥ 'ይህንን ማዶ የሚለውን ቃል የትጋ ባስገባው ይሻላል?' ብለው እንደ ዘበት የዶሉት አለመሆኑን ልንረዳ ያስፈልገናል። ማዶ ከተባለ ማዶ ነው። ስለ ኢትዮጵያ በቀጥታ የሚናገር ሳይሆን ከኩሽ ማዶ ስላሉ አገሮች የሚናገር ነው። አዲስ አበባ ሆኖ፥ 'ከአባይ ማዶ' ከተባለ ስለ ሰላሌ የተነገረ ነው እንደ ማለት ነው።

የቀሩት ወደ 15% የሚጠጉት በተነገሩበት ዘመን ትንቢታውያን ወይም ከዚያ ከተነገሩበት ዘመን በኋላ እንዲፈጸሙ የሚጠበቁ ናቸው። ይህ ማለት ግን አንድ ትንቢት በተነገረበት ዘመን ትንቢት ከሆነ ሁሌም ትንቢት ሆኖ ይኖራል ማለት አይደለም። ወይም ሁሉም ያልተፈጸሙና ገና ወደ ፊት ወይም በዘመናችን የሚፈጸሙ ናቸው ማለት አይደለም። ትንቢቶቹ ሲነገሩ ትንቢቶች ሆነው ግን ባለፉት ዘመናት ውስጥ የተፈጸሙ ሊሆኑ ይችላሉ። ከተፈጸሙ የተፈጸሙ ትንቢቶች መሆናቸው መረሳት የለበትም።

አንዳንዶቹ (እነዚህ 15% ያህሉ) እርግጥም ትንቢቶች ወይም ቢያንስ ትንቢታዊ ግሶችንን የተጠቀሙ ናቸው። ከነዚህ ትንቢቶች አብዛኞቹ አስደንጋጮች ናቸው። ከታች ቁ. 4 ላይ አነሣዋለሁ። እነዚህን የሚጠቅስ ኢትዮጵኛ አላየሁም። የኢትዮጵኝነት ስሜት እነዚህ አስፈራሪ ጥቅሶች እንዳይጠቀሱ ያስገድዳል፤ ያግዳል። ኢትዮጵኖች የሚወድዱትና የሚሄዱበት የአፈታት መንገድ መርጦ ጠቃሽነት ነው።

አንድ ነገር ሲደጋገም ጠልቆ ይገባል። ለተቀባይነትም ጥሩ እጩ መሆን ይችላል። ውሸትም እንኳ ሲደጋገም እውነት ይመስላል። መዝ. 68፥31 የኢትዮጵኞች ባንዲራና አርማ፥ መፈክርና አዝማች ነው። እጅግ ብዙ የተደጋገመ ጥቅስ ነው። ተዘምሮአል፤ ተዘፍኖአል፤ ተጽፎአታል፤ ተሰብኮአል፤ በኢጣልያ ወረራ ዘመን የመንግሥት ሰነዶች ማኅተም እንኳ ሆኖ ነበር፤ በመጀመሪያዎቹ ፓስፖርቶቻችንም ላይ ተጽፎ ነበር።[22] ጥቅሱ ከመዝሙሩ ተገንጥሎ የወጣ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ ማለት ከዐውዱ መውጣት ነው። እዚህ ላይ ነው ችግሩ።

ከላይ በቪድዮው ከተጠቀሱት መካከል መጋቢ በቀለ ወ/ኪዳን፥ "በጭራሽ! ከዐውዱ አላወጣነውም" ብለው በማስረገጥ ይህ የመዝ. 68፥31 ጥቅስ ትንቢታዊና ስለ አሁኒቱ ኢትዮጵያ የሚናገር ትንቢታዊ ቃል ስለመሆኑ ሦስት ጥቅሶችን (ቁ. 18፥ 25፥ እና 29ን) በመውሰድ እንዳስረዱ ከላይ ተመልክቶአል። እዚያ መጋቢ በቀለን ከሌሎቹ ሁሉ በላቀ መልኩ በቃሉ ስለሞገቱ ዓይነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኢትዮጵኛ በማለት ስላወሳሁ እዚህ እነዚህን ሦስት ነጥቦች እንደገና እንይ።

የመጀመሪያው፥"*ቁጥር 18 ላይ፥ ወደ ላይ ዓረግህ፥ ምርኮን ማረክህ፥ ሰጦታንም ለሰዎች ሰጠህ፥ ይላል። ይኼ በአዲስ ኪዳን በኤፌሶን ሐዋርያው ጳውሎስ ጠቅሶታል፤ . . . ስለዚህ ይኼ ነገር ፕሮፌቲክ ነው ማለት ነው። ወደፊት ስለሚሆን ነገር ነው ሚናገረው ማለት ነው።*" ብለዋል። በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰ የብሉይ ኪዳን ቃል እና አሳብ ሁሉ በብሉይ ኪዳን ቃልነቱና በስፍራው ትንቢት ነው ማለት ስሕተት ነው። ትንቢት ሊሆን ይችላል፤ ላይሆንም ይችላል። ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰባቸው ስፍራዎችም ምልክታዎች (allusion) ወይም ቀጥተኛ ጠቀሳዎች (direct quotes) ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ ጌታ በቀደመው እንዲህ ተጽፎአል እኔ ግን እላችኋለሁ ሲል (ማቴ. 5)፥ ትንቢትን መጥቀሱ አይደለም የተባለውን መጥቀሱ እንጂ። ጳውሎስ የጠቀሳቸው ጥቅሶች ትንቢቶች ቢኖሩባቸውም ሁሉም ትንቢቶች አይደሉም፤ ለምሳሌ፥ 1ቆሮ. 10፥1-11፤ 2ቆሮ. 9፥8-9፤ ኤፌ. 5፥14፤ ዕብ. 1 እና 2፤ ወዘተ። አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ትንቢት ብቻ ሳይሆን ለትምህርታችን የተጻፈ ነው፤ ሮሜ 15፥4። መዝ. 68፥18 ጌታ ከሞት በተነሣና ባረገ ጊዜ የተፈጸመ ትንቢት ከሆነ የኢትዮጵያ እጆቿን ማንሣት ከትንሣኤው በኋላ ሌላ 2ሺህ ዓመት ጠብቆ የሚፈጸምበት ስሌት ግልጽ አይደለም። የጳውሎስን የኤፌሶን መልእክት ጠቅላላውን ጭብጥ ሳንተው፥ ኤፌ. 4 ጠቅላላው ምዕራፍ የአካል ብልትነትንና አንድነትን በመግለጥ መታየት ያለበትን መንፈሳዊ የአንድነት ሕይወት ነው የገለጠው። እዚያ በመዝ. 68 እንደ ትንቢት አልተጻፈም እንዲያውም በኃላፊ

[22] ስሜ ታደሰ፤ ገጽ 153። በስሜ ታደሰ ለጳውሎስ እንቁም በተሰኘ የመጣጥፎች መድብል መጽሐፍ ገጽ 136-156 'ኢትዮጵያ እና አርባ ሁለቱ ጥቅሶቿ' በሚል ንዑስ ርእስ ስር ይህ የኢትዮጵያና የዐውዳዊነት አሳብ ጥሩ ሆኖ ቀርቦአል። እንዲያነብቡት አበረታታለሁ።

ጊዜ ግስ (ዓረግህ፥ ማረክህ፥ ሰጠህ ተብሎ) ነው የተጻፈው። እዚህም የትንቢት ፍጻሜ መሆኑ አይደለም የተጠቀሰው። ጳውሎስ ብዙዎችን የብሉይ ኪዳን አሳቦች እንደሚጠቅሰው የክርስቶስን ማንነትና ሥራ ለማሳየት ነው የጠቀሰው።

ሌላው በመጋቢ በቀለ የትንቢት ማረጋገጫ ተደርጎ የቀረበው ቁጥር 25 ላይ ያለው፥ *አለቆች ቀደሙ፥ መዘምራንም ተከተሉ፤ ከበሮን በሚመቱ በቈነጃጅት መካከል* የሚለው ጥቅስ አሰላለፉ የምድረ በዳውን ጉዞ አሰላለፍ ስለማይመስል መዝሙሩ ምንም ስለ ምድረ በዳው ጉዞ ቢናገርም ያንን ዘመን ሳይሆን ትንቢታዊ ሆኖ ወዲህ የሚያመለክት ፕሮፊቲክ ነው ብለዋል። ይሁን እንጂ፥ ይህ ጥቅስ 'ፕሮፊቲክ' መሆኑን ብቻ እንጂ አለቆች የቀደሙበትና መዘምራን የተከተሉበትን የትንቢት አፈጻጸም አልገለጠም። በራሱ በዳዊትም ዘመን ንጉሡ ዳዊት፥ የሠራዊቱ አለቆችና መዘምራኑ የተጣመረ አገልግሎት እንደነበራቸው በ1ዜና 25 እና7ኛለን። በ2ሳሙ. 6፥14-15 እና 20-22 ዳዊትና ሕዝቡ ሆ እያሉ፥ ቆነጃጅትም ባሉበት ታቦቱን ወደ ዳዊት ከተማ ያገቡበት ታሪክ ተጽፎአል። ይህ አሰላለፍ በራሱ በዳዊት ዘመንም መኖሩ ይታያል። መዝሙሩ የተጻፈውም በራሱ በዳዊት ዘመን፥ ጸሐፊውም ራሱ ዳዊት ነው። በዘጸ. 15 ሙሴና አሮን መርተው ማርያምና ሴቶች በኋላዋ ወጥተው ዘምረዋል። ይህ መዝሙር ያንንም የሚያሳስብ ነው እንጂ ወደፊት የሚመጣ አዲስ አሰላለፍም በመጠቆም ጠቅላላው መዝ. 68 ወይም፥ በተለይ መዝ. 68፥31 ትንቢታዊ ነው የሚያሰኝ አይደለም።

መዝሙረ ዳዊት አምስት አንጓዎች እንዳሉት አገዳ ያለ የመዝሙሮች ስብስብ ነው። ይህ መዝ. 68 የሚገኘው በሁለተኛው አንጓ (ከመዝ. 42-72) ውስጥ ነው። እነዚህ መሐሪነቱ፥ ጠባቂነቱ፥ ታዳጊነቱ የነላባቸው መዝሙሮች ናቸው። የጠቅላላውን የመዝሙረ ዳዊትን ዐውድ ስናጤን ከሁሉም በፊት መዝሙሮቹ መዝሙር መሆናቸው መረሳት የለበትም። የምስጋና፥ የውዳሴ፥ የልመና፥ የንስሐ፥ የአምልኮ መዝሙሮች ናቸው። ወደ መዝሙሮቹ አቀራረባችንም ያ ነው መሆን ያለበት። የትንቢት ወይም ትንቢታውያን መዝሙሮች የሉም ማለት ሳይሆን እነዚያንም ጨምሮ የመዝሙሮቹ ዋና ግብ ትንቢትነት ሳይሆን ዝማሬና አምልኮ ነው። በዚህ በመዝ. 68 ውስጥም በምስጋና ዝማሬና አምልኮ ውስጥ እግዚአብሔር በኃያልነቱና በጠባቂነቱ ሲወደስ ነው የሚታየው።

ሦስተኛው የትንቢትነቱ ማረጋገጫ ተደርጎ በመጋቢ በቀለ የቀረበው ሌላ ጥቅስ ቁጥር 29 ነው። *በኢየሩሳሌም ስላለው መቅደስህ ነገሥታት እጅ መንሻን ለአንተ ያመጣሉ።* ይላል። ይህ ቃል በዳዊት ዘመን የተነገረ ሲሆን በሙሴ ዘመን እንደተነገረ ወይም እንደተጻፈ ታስቦ፥ 'ኢየሩሳሌም ያኔ የለችም፤ መቅደስም የለም' ማለት ስሕተት ነው። መዝሙሩ ከዳዊት ዘመን በፊት ወይም በሙሴ ዘመን መጻፉን የሚያሳይ ነገር የለም። እንደ መወድስ መዝሙር ወደ ፊትም፥ ወደ ኋላም ተንሸራሸሯል። መቅደስ (הֵיכָל ሄይካል) ተብሎ በዚህ የተጠቀሰው ቃል በሰሎሞን የተሠራውን መቅደስ ሊወክል ይችላል፤ ቃሉም ተመሳሳይ ነው። ግን ቤተ መቅደሱን መናገሩ እንጂ ሰሎሞን ያሳነጸውን ሕንጻ ብቻ መናገሩ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ይህ ቃል በሌሎች ጥቅሶች፥ ከሰሎሞን በፊት የነበረው መቅደስ ተጠርቶበታል። ለምሳሌ፥ በ1ሳሙ. 1፥9 እና 3፥3 ከተጻፈው ቃል ጋር አንድ ነው። ስለዚህ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ ከመሥራቱ በፊት የነበረው መቅደስ ሊሆን ይችላል፤ ላይሆንም ይችላል። የሰሎሞን መቅደስ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም ከተባለም የሰሎሞን ቤተ መቅደስ የኖረው ከሰሎሞን ዘመን

ጀምሮ እስከተቃጠለበት እስከ 587 ዓ. ዓ. ድረስ ወደ 360 ዓመታት ብቻ የኖረ ሕንጻ ነው። ይህ ከፊረሰ በኋላ ሁለተኛው የሔሮድስ መቅደስ ተብሎ የሚታወቀውና በ70 ዓ. ም. የወደመው ለ80 ያህል ዓመት የኖረ ነው። ነገሥታት እጅ መንሻ ለእግዚአብሔር ካመጡ ከነዚህ ሁለት ዘመናት በአንዱ ነበር ማለት ነው። የጎረቤት ነገሥት ለይሁዳ ነገሥት እጅ መንሻ ማምጣታቸው ተጽፎአል። እንግዲህ ይህ ገና ወደፊት የሚሆን ካልሆነ ዳዊት ትንቢት ተናገረ ማለት ነው ተብሎ ይታሰብ ይሆናል። ነገር ግን እጅ መንሻ ያመጡት ለሰሎሞን እንጂ ለእግዚአብሔር አይደለም። እነዚህን ስንኞች ማየት ያለብን እንደ ትንቢቶች ሳይሆን እንደ ዝማሬ መወድሶች ነው።

የኢትዮጵያ እጅቸዋን ወደ እግዚአብሔር ማንሣት የተጠቀሰበት መዝሙር መዝሙሩን የጻፈው የዳዊት የምስጋና መዝሙር ነው። ትዘረጋለች የሚለው ቃል ትንቢታዊ ግስ ስለሆነ ያለፈ ታሪክን መናገሩ አይደለም። ከዳዊት ዘመን በፊት ኢትዮጵያ የተጠቀሰችው በዘፍ. 2፥13 እና ሙሴ ኢትዮጵያይቱን እንዳገባ በተጠቀሰበት ብቻ ነው። በዚህ መዝሙር ውስጥ ያለፉ ነገሮች አሉበት፤ የሁሌ የሆኑ እውነቶች አሉበት፤ ትንቢታዊም ቃላት አሉበት።

በምስጋና መዝሙር እነዚህም ይካተታሉ፤ በምስጋናው ውስጥ የእግዚአብሔር ገድል፥ መልካምነቱ፥ ኃያልነቱ ነው የታወጀው። ይህ መዝሙር ወደ እግዚአብሔር በምስጋና የቀረበ የድል አድራጊነቱ ውዳሴ ነው። ሲጀምር ሙሴ በምድረ በዳ ሕዝቡን ለጉዞ ሲያስነሣ በሚናገረው በዘኁ 10፥35 በሚገኘው ቃል ይጀምራል። ይህ መዝሙር ስለ ጠላቶች መበተን፥ ከፊቱ መሸሽ፥ እንደ ጢስ መበነን፥ እንደ ሰም መቅለጥ፥ እግሮቹ በደም ሲረገጡ፥ የውሾች ምላስ በጠላቶቹ ላይ ሲሆን፥ ነገሥታት እጅ መንሻ ሲያመጡ፥ አሕዛብ ሲበተኑ፥ የበሬዎችና የወይፈኖች ጉባኤ ሲገሰጽ፥ የጠላት ራስና የኃጢአተኛ አናት ሲቀጠቀጥ፥ እነዚህ የመሰሉ የድል ነሺ ተግባራትን ሐረግ የተሞላ ነው። ለድል አድራጊና ታዳጊ አምላክ የቀረበ ውዳሴ ነው።

እንዲህ ባለው መዝሙር ውስጥ ነው የመኳንንት ከግብጽ መምጣትና የኢትዮጵያ እጅ ማፍጠን ወይም ማንሣት የተጻፈው። ከዚህ ጥቅስ በፊት ያለው ቃል (ቁጥር 30) ሰልፍን ወይም ጦርነትን የሚወዱ አሕዛብ እንዲበተኑ የቀረበ ልመና ነው። ይህ መዝሙር በተጻፈበት ዘመን የኩሽ መልክ ቀደም ሲልም እንደተጠቀሰው የወራሪና የጠብ አጫሪ ነው። ከዚያ በኋላ፥ ከዳዊትና ከሰሎሞን ዘመናተ መንግሥት በኋላማ ይህ የወራሪነትና ጠበኝነት ስሜት የባሰ ነበረ። ዕድል ፈንታዋም በምዕራፉ ውስጥ ከተዘረዘረው ሸንፈት እንጂ ሌላ እንዲሆን አይጠበቅም። ይህ ጥቅስ የኢትዮጵያ ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ፥ የጸሎት፥ የምልጃና እግዚአብሔርን እንደ አንዱ እውነተኛ አምላክ የመቀበል እጅን መዘርጋት እንደሆነ ማሰብ የሚያስደስት ነው፤ ነገር ግን ዐውዱ በግልጽ የሚያሳየው በተሸናፊነት መማረክና እጆችን ማንሣትን ነው እንጂ አምልኮና መገዛትን አይደለም።

ለአንድ ሕዝብ፥ በተለይም ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያስፈልገውን ነገር መናገር የክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነት መሆኑን አምናለሁ። ከዚህ እኩል አጥብቄ የማምነው ሌላ ነገር ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ምኞታቸው ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ቃልነቱ መግለጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች የሚጠበቅ ኃላፊነት መሆኑን ነው። ለኢትዮጵያ ካለን ፍቅር የተነሣ መጽሐፍ ቅዱስን መጠምዘዝን እንደ ቀላል መውሰድ የለብንም።

ብዙ ወደተደጋገመው ጥቅስ እንምጣ። መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ፤ ኢትዮጵያ እጆቸዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለው ቃል በተጻፈበት ቋንቋ፥ כּוּשׁ תָּרִיץ יָדָיו לֵאלֹהִים׃ יֶאֱתָיוּ חַשְׁמַנִּים מִנִּי מִצְרָיִם (68:32) (ዬኤታዩ ኻሸማኒይም ሚኒይ ሚጽራዪም፤ ኩውሽ ታሪይጽ ያዳዩ ሌእሎሂይም) ሲል ብሉይ ኪዳን ወደ ጽርዕ በተመለሰበት የሰባ ሊቃናት ወይም ሰብትዋጅንት ትርጉም ደግሞ፤ (68:32) ηξουσιν πρεσβεις εξ αιγυπτου αιθιοπια προφθασει χειρα αυτης τω θεω ይላል። አቻ ቃላቱን ስንኮለኩላቸው፤

יֶאֱתָיוּ חַשְׁמַנִּים מִנִּי מִצְרָיִם כּוּשׁ תָּרִיץ יָדָיו לֵאלֹהִים׃

ይመጣሉ/ይወጣሉ መኳንንት/ኃይለኞች ከምስር፤ ኩሽ/ኢትዮጵያ ታስቸኩላለች/ትዘረጋለች/ታነሣለች እጆቸዋን ወደ እግዚአብሔር

ηξουσιν πρεσβεις εξ αιγυπτου αιθιοπια προφθασει χειρα αυτης τω θεω

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ግብጽን ወደ ጎን ትተን ኢትዮጵያን ብንመለከት ከሌሎቹ ሁሉ ቃላት ይልቅ አሻሚ የሚሆኑትና በሌላ አሳብ ሊተረጎሙ የሚችሉ ሁለት ቃላት ኢትዮጵያ እና መዘርጋት ናቸው። ኢትዮጵያ የሚለው ሰፊ ግዛት ሊሆን እንደሚችል በትንሹ ተመልክተናል። መዘርጋት ወይም ማንሣት የሚል ቃል ነው። ማንሣት (προφθάνω) ወደፊት መምጣት፥ መቅደም፥ መቅረብ፥ መጠባበቅ ማለት ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ (ማቴ. 17፥25) አንድ ጊዜ ብቻ ሲጻፍ ቃሉ 'አስቀድሞ' ተብሎ የተተረጎመው ነው። ቀድሞ መድረስ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ቋንቋም יָרַץ ወይም ታሪይጽ፥ ታርጣለች የሚለው ቃል በሌሎች ጥቅሶች ውስጥ ሲታይ፥ ለምሳሌ፥ ኢዩ. 2፥7-9፤ አሞ. 6፥12-13፤ ናሆ. 2፥4፤ ዕን. 2፥2፤ ሐጌ 1፥9፤ ወዘተ፥ መሮጥ፥ መቸኮል፥ መፍጠን፥ መጋለብ፥ መከነፍ ተሰኝቶአል יָרוּץ ሩውጽ፤ ወይም מְרוּץ መሮውጽ፥ መሮጥ፥ ሩጫ ከሚል ቃል የተሠራ ነው።

ብዙ ኢትዮጵያውያን እና ሁሉም ኢትዮጵኞች ይህንን እጅ መዘርጋት እንደ አምልኮ እጅ መዘርጋት አድርገው ነው የሚወስዱትም የሚያስተምሩትም። የሸንፈትና የመዋረድ፥ የምርኮም ቃል መሆኑን ለመቀበል ቀርቶ ለማሰብም እንኳ ከሩቅ ነው የሚያባርሩት። ይህንን ነጥብ እንደገና ለማብራራት ሁለት ነጥቦችን ላውሳ። አንደኛ፥ ከላይ እንዳየነው ብሉይ ኪዳን በግሪክ ቋንቋ በተጻፈበት ትርጉም ቃሉ προφθάνω ነው። ችኮላን፥ መፍጠንን የሚያሳይ ቃል ነው። የቀድሞው (የ1879) ትርጉም፥ መሳፍንቶች ከምስር ይወጣሉ፤ ኢትዮጵያም ፈጥና እጅዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ይላል። መፍጠን የሚለው አሳብ ማንሣት ወይም መዘርጋት ከሚለውም ይልቅ የጎላ ነውና ትርጉሙ ትክክለኛ ነው። ሁለተኛ፥ ጳውሎስ የሰባ ሊቃናትን ትርጉም የሚያውቅና ብዙም የተጠቀመበት መሆኑ ከብሉይ ኪዳን ጥቅሶች አጠቃቀሱ ይስተዋላል። ለአምልኮና ለጸሎት እጅ መዘርጋትን በጠቀሰበት አንድ ስፍራ የጻፈው ቃል ይህ ሳይሆን ሌላ ነው። በ1ጢሞ. 2፥8 *እንግዲህ ወንዶች በስፍራ ሁሉ አለ ቍጣና አለ ክፉ አሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሡ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ።* በዚህ ጥቅስ እጆችን ማንሣት የሚለው ቃል፥ ἐπαίρω ኤፓይሮ የሚል ነው። αἴρω (አይሮ) ከሚል ቃል የወጣ ነው። ቃሉ ሰፊ ሆኖ ማቅናት፥ ማንሣት፥ መዘርጋት፥ ከፍ ማድረግ፥ ከፍ ማለት፥ መክፈት ማለት ነው። በተለያየ መልኩ ወደ 70 ጊዜያት በሰባ ሊቃናት ትርጉም ተጠቅሶአል።

በብሉይ ኪዳን ወደ እግዚአብሔር ወይም ለአምልኮ እጅ መዘርጋትን የሚያመለክቱ፥ ለምሳሌ፥ 1ነገ. 8፥22፤ መዝ. 44፥20፤ ኢሳ. 1፥15፤ ሌሎችም ቃላት አሉ። ይህኛው ማሮጥ ወይም ማስቸኮል ከአምልኮ ጋር ከመጣበቅ ይልቅ መሸነፍና ምርኮ መሆኑ በኢትዮጵኞች ዘንድ ቢያንስ ታሳቢ ለመሆን የቃል ጥናት እንኳ ቢደረግ መልካም ነበር። ይህ የቃላት ጥናት የቃላት ስንጠራ ሊመስል ይችላል። ዋናው የሙግት ነጥቤ፥ 'ለኢትዮጵያ እጆችን ወደ እግዚአብሔር መዘርጋት ማምለክ ማለት ነው፤ ማምለክም የሚሆንበት ዘመን ሌላ ሳይሆን ይህ ያለንበት የ21ኛው መቶ መጀመሪያ ኢጋማሽ ዘመን ነው፤' ማለት ብዙም የማያስኬድ መሆኑ ነው። ኢትዮጵኞችም ሆኑ ሌሎች ሰዎች አንድን ጥቅስ ደጋግመው፥ አከርረውና አምርርረው ሲጠቅሱ ሊጠነቀቁበት የሚገባው ዐቢይ ጉዳይ ዐውድ ነው። ያ ጥቅስ ላዩን ብቻ የሚታየውን ያህል ተልጦ ውስጡም መታየት አለበት። ደግሞም በንጽጽር ቃሎቹና አሳቡ ያለባቸው ሌሎች ስፍራዎችም መጠናት አለባቸው። አንድን ጥቅስ እንደ ሰንበሌጥ መዝዘ ከዚያ እንደፊኛ ቢነፉት የትምህርት መሠረት የመሆን አቅም የለውም።

3. ያኔ፥ እዚያና ያ።

<u>አንድ ቃል፥ አገርም ይሁን ነገር፤ ሰውም ይሁን ትምህርት፤ በዛሬው ሳይሆን በዘመኑ ቋንቋና መረዳት፥ ምን እና ማን ነው ማለት ተገቢ ነው።</u> ኢትዮጵያ ማን ናት? ያኔ በተጠቀሰችበት ዘመን መረዳትና በቃሉ ትርጉም የትኛዋ አገር ናት? ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በአንድ የአዲስ ኪዳን ጥቅስ ውስጥ ብቻ ሲገኝ የቀሩት በሙሉ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ናቸው። በዕብራይስጥ ደግሞ ኢትዮጵያ የሚል ቃል የለም። ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ለአንዳንዶቻችን እንደሚመስለን የአማርኛ ወይም የግዕዝ ቃልም አይደለም። ኢትዮጵያ የሚለው ቃል የግሪክ ቋንቋ ቃል ነው።

በግሪካውያኑ አጻጻፍ Αἰθίοψ - አይቲአፕስ አንድ ወጥ ቃል ሳይሆን በሁለት ቃላት የተሰራ ሐረግ ነው። ሁለቱ ቃላትም ኤቶስ እና ኦፕሲስ ናቸው። ኤቶስ ማለት ዋዕይ ወይም ሐሩር ማለት ሆኖ በሐሩር የጠቆሩ መሆንን በማሳየት መጥቆር፥ መጠበስ፥ መከሰል እንደማለት ነው። ኦፕሲስ ማለት ደግሞ ፊት ማለት ነው። ሁለቱም ቃል ሲቆራኝ የተቃጠለ፥ የከሰለ ገጽ፥ የጠቆረ ፊት ማለት ይሆናል። ጥቁር ፊት ያለው ማን ነው? መልሱን ለማግኘት ማንንም ጥሬ አፍሪቃዊ መመልከት በቂ ነው። ስለዚህ አይቲዮፕስ ጥቁር ማለት ነው።

የዕብራይስጡ כּוּשׁ (ኩውሽ) ማለትም ተመሳሳይ ነው። ጥቁር ማለት ነው። ስያሜውን በጠባቡ ከወሰድነው የጥንታዊዋን ግብጽ ደቡብ ይዞ የላይኛው ዓባይ የሚሉትን አገር ይሸፍናል። ይህ መልከዓ ምድር በቀጣዮቹ በርካታ ዘመናት መርዌ እና ናፓታ የሚባለው ክፍል ነው። በሰፊው አገላለጥ ከሄድን ደግሞ ከጥንታዊቱ ግብጽ በደቡብ ያለው ሕዝብ በሙሉ ነው። ይህ የኋለኛው አገላለጽ ምናልባት በብሉይ ኪዳን የተጻፈው ግዛት እንደሚሆን ባይመስልም የቃሉ ትርጉም ጠቅላላውን ጥቁር ሕዝብም ሊያመለክት መቻሉም መታለፍ የለበትም። የብሉይ ኪዳን የሰባ ሊቃናት ትርጉም (ሰብትዋጅንት) ኩሽን ኢትዮጵያ እያለ ነው

የተረጎመው። ከ43ቱ ጥቅሶቻችን 42ቱ በብሉይ ከተገኙ ይህ ኩሽ እና ኢትዮጵያ የሚለው የብሉይ ቃል በጥንቃቄ መጤንና መጠናት አለበት።

ስለ ኢትዮጵያና ስለ ሕዝባችን ስጸልይ (በተለይ አሁን እንደሆነው የድርቅና የረሃብ አደጋ ሲያንጉጥብ) ደጋግሞ ማሰብና ማንበብ ከሚያስደስተኝ ጥቅሶች አንዱ መዝ. 74፥ 14 ነው። ቃሉ እንዲህ ይላል፥ *አንተም የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥህ ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው።* ከልቤ ጠቅሼዋለሁ፤ ያኔ የኢትዮጵያን ሰዎች እንደመገበ እንደገናም ያንን እንዲያደርግና ረኃቧ እንዲቀረፍ። እግዚአብሔርን በቃሉ ልሞግተውም ሞከሬአለሁ። የየዋህነት ሙግቴን እግዚአብሔር ፈገግ ብሎበት ይሆናል። አሁንም የዋኅነትን እመኛለሁ፤ ግን እውቀት ያልተነፈገው የዋህነት።

ይህንን ጥቅስ ከዓመታት በኋላ በተጻፈበት ቋንቋ ሳየው ኢትዮጵያ የሚል ቃል በውስጡ ጨርሶውኑ የለም። የጥቅሱ የመጨረሻው ስንኝ የሚለው תְּתָנֵנוּ מַאֲכָל לְעָם לְצִיִּים: (ቲትኔኑ ማአካል ለዓም ለጺዪይም - ሰጠሃቸው መብል ለምድረ በዳዎች ሰዎች)። የምድረ በዳዎች ሰዎች የሚለው አራዊትንም ሊሆን ይችላል፤ ከቁ. 13 ጋር ሲታይ ዐውዱ እንዲያውም አራዊት ያስመስለዋል፤ የዘንዶውን (ሌዋታን) ራሶች ቀጥቅጠህ ለበረሃው አራዊት ይበሉት ዘንድ ሰጠሃቸው ነው ቀጥታ ትርጉሙ። ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ወደ አማርኛ ትርጉም የገባው የአማርኛው ትርጉም የሰባ ሊቃናትን ትርጉም የተከተለ ስለሆነ ነው። የሰባ ሊቃናት ትርጉም ይህንን ቃል፥ εδωκας αυτον βρωμα λαοις τοις αιθιοψιν (ሰጠሃቸው መብል ለኢትዮጵያ ሰዎች) ብለው ተርጉመዋል። צִיִּים (ጺዪይም) የሚለው ቃል ከምድረ በዳ ወደ ኢትዮጵያ (αιθιοψ - አይቲዮፕስ) መምጣቱ የዘመኑን የቃሉን ትርጉም ያሳያል። አይቲዮፕስ በፀሐይ የከሰለ ፊት ማለት ነው። የምድረ በዳ ሰውን፥ የዘላን ፊትን ያመለክታል። ይህ ቃሉን እንደ አራዊት ሳይሆን እንደ ሰው ከወሰድን ማለት ነው። እንግዲህ ይህ ከዚህ ጥቅስ የሚስተዋለው የሰባ ሊቃናት አተረጓጎም አስፍቶ የመድረስና ተቀባይ ተኮር አተረጓጎም ነው እንጂ ለምንጩ ቋንቋ ሳይዛነፍ መተላለፍ የተጨነቀ አተረጓጎም እንዳልነበር ነው። ታዲያ የሌለ ቃልንም እንዳለ አድርገን እንድንቀበል ተደርገናል ማለት ነው። እኔም ያልተጻፈ የፍትሐ ብሔር አንቀጽ እንደሚጠቅስ ጠበቃ ሆኜ ነበር ማለት ነው።

መዝ. 72፥9ም ከላይ እንደተጠቀሰው እንደ መዝ. 74፥14 ያለ ቃል ነው። በሰባ ሊቃናት ትርጉም አድርጎ ወደ አማርኛ በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ ተብሎ እንደ ኢትዮጵያ ሰዎች የተጠቀሰው በዕብራይስጥ የምድረ በዳ ሰዎች ወይም የምድረ በዳ ዘላኖች የሚል ነው። እንግዲህ ጥቂት ውድ ጥቅሶችን ለመጣል ልንገደድ ነው።

የብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ኩሽ (כּוּשׁ ኩውሽ) የሚለው ነው። ሕዝቡም ኩሺይ፥ ኩሺይት፥ ኩሺይም ናቸው። ኩሽ ከላይ እንዳልኩት በዕብራይስጥ ጥቁር ማለት ነው። በዘፍ. 10፥6-8 እና 1ዜና 1፥8-10 ኩሽ የሚለው ቃልና በሌሎች የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ኢትዮጵያ የሚሉት ቃላት አንድ ናቸው። ኩሽ ከኖኅ ልጅ ከካም አራት ልጆች አንዱ ነው። ብሉይ ኪዳን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ በተመለሰበት የሰባ ሊቃናት (ወይም ሰብትዋጅንት) ትርጉም ኢትዮጵያ (αιθιοπιας አይቲዮፒያስ) ተብሎ ተተርጉሞአል። ኩሽ ወይም ጥቁር የሚለው ቃል ቀጥታ ትርጉም ነው።

ኩሽ ከአይሁድ አገር በስተደቡብ ያለው አገር በሰፊው፥ ሊያካትት ይችላል። ወይም ከግብጽ ደቡብ ያለውን አፍሪቃ ሊይዝ ይችላል። ወይም በጠባቡ በኋላ ኢትዮጵያ የተባለውን አገር ሊወክል ይችላል። ደግሞም ኢትዮጵያ እንደ አገር ወይም ሕዝብ እና እንደ ፖለቲካዊ አካል በተጻፈችባቸው ስፍራዎች 14 ጊዜ ከግብጽ ጋር አብራ ተቆራኝታ ነው የተጻፈችው። ሁለቱ አገሮች አንድ ነበሩ ማለት ሳይሆን የተቆራኙበት አሐዳዊ ሥርዓት ያለ ይመስላል። ይህ 14 ጊዜ ማለት በጠቅላላ ከተጠቀሰችባቸው ሚሶው ማለት ነው። ለምሳሌ፥ ኢሳ. 20፥3-5፤ ሕዝ. 30፥4 እና 9፤ ዳን. 11፥43፤ ናሆ. 3፥9። መዝ. 68፥31ም በዚህ ውስጥ ይጨመራል።

ከላይ ካየናቸው መጋቢዎች አንዱ አሞ. 9፥7ን በመጥቀስ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤል ጋር ተነጻጽረን በልጠን መገኘታችንንና ልዩና ሞዴል መሆናችንን መናገራቸውን አይተናል። "የእስራኤል ልጆችን እናንተ እኮ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች ናችሁ ለኔ" በማለት ኢትዮጵያን እንደ ሞዴል፥ እንደ ምሳሌ ሲያያትና ኢትዮጵያ ላይ ያለው አመለካከት ጥሩ እንደሆነ . . ." በማለት ተናግረዋል። ይህ ጥቅስ በበርካታ ኢትዮጵኞች ዘንድ ብርቅዬ የእንቁልልጭ መጫወቻ ነው። ዐውዱን እንደሌለ በመቁጠር ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ከእስራኤል ይልቅ የተወደደች፥ የቀረበች፥ በእቅፉ ውስጥ ያለች መሆኗን መናገሩ እንደሆነ አድርገው ያስተምራሉ። ግን በእቅፉ ሳይሆን እጅግ መራቋን መናገሩ ነው።

ጠቅላላውን ምዕራፍ (አሞ. 9ን) ማንበብ ብቻውን ግን እግዚአብሔር እስራኤልን እያጥላላና ኢትዮጵያን እያሞካሸ መናገሩ አለመሆኑን ያስረዳል። እስራኤል በዘመናቸው እንደሚያውቋት የሩቅ የሆነች ኢትዮጵያ፥ እስራኤልም በመንፈስና በግብር ከእርሱ የተየለሌ የራቁ ሰዎች መሆናቸውን መናገሩ ነው። እዚያው ሆነው፥ ግን የራቁ ሰዎችን ሁኔታ መናገሩ ነው። አሞ. 9 የሚናገራቸውን የርቀት ቃላት ብናጤን፥ ወደ ሲዖል ቢወርዱ፥ ወደ ሰማይ ቢወጡ፥ በቀርሜሎስ ራስ ቢሸሸጉ፥ በጥልቅ ባሕር ውስጥ ከዓይኔ ቢደበቁ፥ በጠላቶቻቸው ፊት ተማርከው ቢሄዱ የሚሉት ሐረጎች ይህ አሳብ ኢትዮጵያን እያደመቀና እያደነቀ ሳይሆን አይሁድን እየወቀሰ መሆኑን መረዳት አይሳነንም። ኢትዮጵያ እዚህ መጠቀሷ የአድናቆት ማነጻጸሪያ ሆና ሳይሆን የርቀት መለኪያ ሆና ነው። ኢትዮጵያ የሩቅ የምድር ዳርቻ አገር ናት። ሳባና ኢትዮጵያ አንድ እንደሆኑ ወይም የተቆራኙ ናቸው ብለን ብናምን የሳባ ንግሥት የመጣችበትን አገር ጌታ ሲጠቅስ የምድር ዳርቻ ብሎታል፤ ማቴ. 12፥42፤ ሉቃ. 11፥31።

ይህ መዝሙር በተጻፈበት በዳዊት ዘመንም ሆነ ቀጥሎ በነበሩት ዘመናት፥ በሰሎሞን ዘመን ሰላም ከመሆናቸው በቀር፥ ኢትዮጵያና ግብጽ የአይሁድ ወዳጆች አልነበሩም። ሰሎሞን በሞተ በ5ኛው ዓመት ግብጽ ይሁዳን ስትወጋ ኢትዮጵያ ረዳቷ ነበረች (2ዜና 12፥1-3)። በቀጣዩ 20 እስከ 30 ዓመት ደግሞ ኢትዮጵያዊው ዝሪ 1 ሚሊዮን ሠራዊቱን ይዞ ሊዋጋ ወጣ፤ ሠራዊቱም ፈጽሞ ወደመ።

ይህ እንግዲህ የከብረ ነገሥቱ ተረታችን (የሰሎሞንና የንግሥተ ሳባ) ሠርግና ጫጉላ ማግሥት መሆኑ ነው። በሕዝቅያስ ዘመን ደግሞ ቲርሐቅ የተባለ የኢትዮጵያ ንጉሥ ለወረራ ይሁን ለእርዳታ ባይታወቅም ሠራዊቱ በዚያ መሆኑ ተወርቶ ነበር፤ 2ነገ. 19፥9። ከነዚህ ጦርነቶች የምናየው አንድ ጉልህ ነገር፥ በግለ ሰብ ደረጃ የተጠቀሱ ሰላማውያን ኢትዮጵያውያን ከመኖራቸው በቀር ኩሽ እና እስራኤል ወይም ወይም ኩሻውያንና አይሁድ የወዳጅነት ሳይሆን የጦርና የጠላትነት ታሪክ እንደነበራቸው ነው። ይህንን ከታሪክ ጀርባ ያለ በጦርነት መሰላለፍ

ግምት ውስጥ ካስገባን የመኳንንት ከግብጽ መምጣትና የኢትዮጵያ እጆቿን ማንሣት የሸንፈትና የምርኮ እንጂ ኢትዮጵኞች እንደሚያስተምሩን 3ሺህ ዓመታት ጠብቆ አሁን በኛ ትውልድ ዘመን የሚሆን የአምልኮ እጅ ማንሣት የክርስቶስ ምጽአት ኢጋፋሪነት አለመሆኑን መረዳት አይሳነንም።

አንድ ቀን በሰማይና በምድር፥ ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከካሉ፤ መላስም ሁሉ ለአብ ክብር ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክራሉ (ፊል. 2፥10-11)። ያ የኛንም ሕዝብ ይጠቀልላል። ከዚያ ወዲህ ግን፥ በተጠቀሰው የቪድዮ ዝግጅት ከተነበዩት አንዱ እንደተናገሩት 90% አማኝ 10% ደግሞ ተመልካች የሚሆኑበት አንዲት አገር እንደ አገር ክርስትና እንደምትነሣና ሕዝቡም ሁሉ በወል አምላኪ እንደሚሆን ቃሉ አልተናገረም። ክርስትና ሃይማኖት ከሆነ ብሔራዊ ሃይማኖት አይደለም። ክርስትና የግል የአማኝና የክርስቶስ ግንኙነት ነው። በታሪክ ውስጥ ክርስትና ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ ያውቃል። በ4ኛው ምዕት ዓመት ክርስትና የሮም መንግሥት ብሔራዊ ሃይማኖት የተደረገበት ዘመን ነበረ፤ በአሳዛኝ መልኩ ግን ያ ዘመን የቤተ ክርስቲያን መበስበስና መውደቅ የሆነበትም ዘመን ነበረ።

4. ለቅሞ መጣል።

<u>አንድ ቃል ወይም ጽንሰ አሳብ ከቃሉ ሲወሰድ ቃሉ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚያ ቃል የሚናገረው ነገር በከፊል በመልቀም፥ በመረጣና በቁራጭ ሳይሆን በሙሉው ነው መወሰድ ያለበት።</u> ስለ ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ተብሎ ሲጠና ልክ ሌላ ርዕስ እንደሚጠናው ቃሉ በስፋቱም በጥልቀቱም ነው መጠናት ያለበት። የዐውዳዊ አጠናንን ጉዳይ ከላይ ያነሳነው ስለሆነ እዚህ አልደግመውም። እዚህ የስፋትና የጥልቀት አጠናን የምለው ቃሎቹ ያሉበትን ስፍራዎች ሁሉ ሳያስቀሩ መውሰድን ነው።

ጥቅሶቹ ስለ ኢትዮጵያ ከተናገሩት መልካም የመሰለንን አንድ ወይ ሁለት ብቻ ነው የምንመርጠው? ወይስ ጠቅላላውን መርምረን ሁሉንም እንቀበላለን? ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ርዕስ ሲጠና በርዕሱ ዙሪያ ያሉት ጥቅሶች በሙሉ መታየት፥ መመርመርና መጠናት አለባቸው እንጂ አንድ ወይም ሁለት ጥቅሶች ብቻ መመረጥ የለባቸውም። ለምሳሌ፥ ስለ ቤተ መቅደስ ወይም ስለ ጥምቀት የሚያስተምር አንድ ሰው አንዲት ጥቅስ ብቻ አውጥቶ ቢያውለበልብ፥ 'ይኼ ዝናን ነው' ብለው ዝናን እንዲዳስስ ያደረጉት ዓይነ ስውር የዝናኑን ኩምቢ ከዳሰሰ በኋላ፥ "ዝናን ማለት ትልቅ ቱቦ ነው" እንዳለው መሆን ነው።

ኢትዮጵያን በተመለከተ በኢትዮጵኞች እስከዛሬ የሚዥንደኃደው አንድና አንድ ብቻ ጥቅስ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የሚለው የመዝ. 68፥31 ቃል ነው። ሌሎች አንድ ሁለት እንደ ምርቃት ጣል ይደረጋሉ። ከተቀሩት ብዙዎቹ፥ በተለይ አፍራሽና አሉታዊ የሚመስሉቱ ከቶም አይታሰቡም። ለምሳሌ፥ እነዚህን ጥቅሶች እንመልከት፤

> ኢሳ. 20፥4 እንዲሁ የአሦር ንጉሥ የግብጽንና የኢትዮጵያን ምርኮ፥ ጕበዛዝቱንና ሽማግሌዎቹን፥ ራቁታቸውንና ባዶ እግራቸውን አድርጎ ገላቸውንም ገልጦ፥ ለግብጽ ጕስቍልና ይነዳቸዋል።
>
> ኢሳ. 20፥5 እነርሱም ከተስፋቸው ከኢትዮጵያ ከትምክሕታቸውም ከግብጽ የተነሣ ይፈራሉ ያፍሩማል።

> ኢሳ. 45፥14 እግዚአብሔርም እንዲህ ይላል። የግብጽ ድካምና የትዮጵያ ንግድ ቁመተ ረጅሞችም የሳባ ሰዎች ወደ አንተ ያልፋሉ ለአንተም ይሆናሉ እጆቻቸውም ታስረው ይከተሉሃል በፊትህም ያልፋሉ፥ ለአንተም እየሰገዱ። በእውነት እግዚአብሔር በአንተ አለ፥ ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም ብለው ይለምኑሃል።
>
> ኤር. 46፥8-10 ግብጽ እንደ ግብጽ ወንዝ ይነሳል ውኃውም እንደ ወንዙ ይናወጣል እርሱም፡-እነሣለሁ ምድርንም ሁሉ እከድናለሁ ከተሞችንና የሚኖሩባቸውን አጠፋለሁ ብሎአል። ፈረሶች ሆይ፥ ውጡ ሰረገሎችም ሆይ፥ ንዱ ጋሻም የሚያነግቡ የኢትዮጵያና የፉጥ ኃያላን፥ ቀስትንም ይዘው የሚስቡ የሉድ ኃያላን ይውጡ። ያ ቀን ጠላቶቹን የሚበቀልበት የሥራዊት ጌታ የእግዚአብሔር የበቀል ቀን ነው ሰይፍ በልቶ ይጠግባል በደማቸውም ይሰከራል፥ ለሥራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር በሰሜን ምድር በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ መሥዋዕት አለውና።
>
> ሕዝ. 29፥10 ስለዚህ፥ እነሆ፥ በአንተና በወንዞችህ ላይ ነኝ፥ የግብጽንም ምድር ከሚግዶል ጀምሮ እስከ ሴዌኔና እስከ ኢትዮጵያ ዳርቻ ድረስ ውድማና ባድማ አደርጋታለሁ።
>
> ሕዝ. 30፥4 ሰይፍ በግብጽ ላይ ይመጣል፥ ሁከትም በኢትዮጵያ ይሆናል የተገደሉትም በግብጽ ውስጥ ይወድቃሉ፥ ብዛትዋንም ይወስዳሉ፥ መሠረትዋም ይፈርሳል።
>
> ሕዝ. 30፥5 ኢትዮጵያና ፉጥ ሉድም የተደባለቀም ሕዝብ ሁሉ ኩበም ቃል ኪዳንም የገባችው ምድር ልጆች ከእነርሱ ጋር በሰይፍ ይወድቃሉ።
>
> ሕዝ. 30፥9 በዚያ ቀን መልእክተኞች ተዘልለው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያንን ለማስፈራት ከፊቴ በመርከብ ይወጣሉ እንደ ግብጽም ቀን ሁከት ይሆንባቸዋል እነሆ፥ ይመጣልና።
>
> ሕዝ. 38፥3-6 እንዲህም በል፥ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የሞሳሕና የቶቤል ዋነኛ አለቃ ጎግ ሆይ፥ እነሆ፥ እኔ በአንተ ላይ ነኝ። . . . ፋርስንና ኢትዮጵያን ፉጥንም ከእነርሱ ጋር ጋሻና የራስ ቍርን የለበሱትን ሁሉ፥ . . . ብዙዎችንም ሕዝቦች ከአንተ ጋር አወጣለሁ።
>
> ዕን. 3፥7 የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ የምድያም አገር መጋረጃዎች ተንቀጠቀጡ።
>
> ሶፎ. 2፥12 እናንተም ኢትዮጵያውያን ደግሞ፥ በሰይፌ ትገደላላችሁ።

መርጠው ለሚጠቅሱ ይህ አይስማማቸውም። ለምን? በረከት አልተነገረባቸውም፤ የኢኮኖሚ ወይም የፖለቲካ ስኬት የለባቸውም። አዎንታዊነትና ገንቢነት አልተቋጠረባቸውም። ከሌሉባቸው ደግሞ አይጠቅሷቸውም። ጥቅስን በመርጦ መጣልና ቆርጦ በመደረት ካስተማሩት ቃሉ ሳይሆን የራስ ስሜት በመደመጥ ላይ የመሆኑ አመልካች ነው። እነዚህ ጥቅሶች የሚጠቅስ አንድም ኢትዮጵኛ አናገኝም።

 ቶች እነዚህን ምናልባት ከጠቀሱ በደፈናው የተፈጸሙ ትንቢቶች አድርገው ሊወስዱ ይሞክሩ ይሆናል። መዝ. 68፥31 የትንቢት ሳይሆን የመዝሙር መጽሐፍ ሆኖ የዚህ ዘመን፥ በተለይ የ21ኛው ሙዶ ተፈጻሚ የሆነበት መስፈርትና እነዚህ ሁሉ ደግሞ ከነቢያት መጻሕፍት የተወሰዱ ሆነው የማይጠቀሱባቸውና ጨርሶውኑ የማይታወቁባቸው ምክንያት የሚያስደንቅ ነው።

4. ኢትዮጵያ ወይስ ዩቶፒያ?

ከላይ እንደተመለከትናቸው ሰዎች ትንበያዎች በቅርቡ የምትፈጠረው ኢትዮጵያ መልክ ከሙሉ በከፊሉ ይህንን ይመስላል፤ ብዙዎቹ የተናገሩት ፖለቲካዊ፥ ኢኮኖሚያዊ/ኢኮሎጂያዊ፥ ሃይማኖታዊ፥ ተብሎ በቀላሉ በሦስት ሊፈረጅ ይችላል።

<u>ሃይማኖታዊ፤</u> ኢትዮጵያ ክርስቲያን አገር ትሆናለች፤ ከሕዝቧ ቢያንስ ከ90% በላይ ክርስቲያን ይሆናል። ይህ ከሕዝቧ ብዛትና ከመቶኛ ስሌት አንጻር ሲታይ በዓለም የመጀመሪያዋ ክርስቲያን አገር ያደርጋታል።

ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም ኢትዮጵያዊ እስኪመስል ድረስ ይደረሳል። ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ከመታሰቧ የተነሣ በመጨረሻው ዘመን (በጥቂት ዐሠርታት) የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ተክታ የክርስቶስን ምጽአት የምታፋጥን ብቸኛና ዋና አካል ትሆናለች።

የእግዚአብሔር ፑልፒት ኢትዮጵያ ውስጥ ይሆናል። እግዚአብሔር ለዓለም ሕዝብ የሚናገረውን ማናቸውንም ነገር የሚናገረው ከኢትዮጵያ ስለሆነ የዓለም ሕዝብ አትኩሮ የሚያየው ወደ ኢትዮጵያ፥ አጥብቆ የሚሰማውም ከኢትዮጵያ የሚተላለፈውን ድምጽ ነው። የኢትዮጵያን ነቢያት መስማት የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ይሆናል። ለዓለም ችግሮች ሁሉ መፍትሔ የሚነደፈውና የሚወጣው ከኢትዮጵያ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚፈስሰው መንፈሳዊ ቅባት የተነሣ የዓለም ሕዝብ ወደ ኢትዮጵያ ማየት ብቻ ሳይሆን ለመምጣትና ቅባቱን ለመቀበል የሚያደርገው ርብርብ ከፍተኛ ይሆናል። በእግዚአብሔር በኩል ያለው ዝግጅት ተጠናቅቆአል።

የኢትዮጵያ እጆቿን መዘርጋት የዓለምን መልክ የሚቀይር መንፈሳዊ ሪቫይቫል ከኢትዮጵያ መንጭቶ ወደ ዓለም ይደርሳል። የመጀመሪያው ወንጌል ከኢየሩሳሌም እስከ ይሁዳ፥ ሰማርያ፥ የምድር ዳርቻ እንደተስፋፋው የመጨረሻው ወንጌል ከኢትዮጵያ ይጀምርና እስከ ዓለም ዳርቻ ሲደርስ ያኔ የክርስቶስ ምጽአት ይሆናል። የኢትዮጵያ የተቀቡ አገልጋዮች እስከ ዓለም ዳር እስኪደርሱ ድረስ ክርስቶስም ይጠብቃል እንጂ ዳግም አይመጣም።

<u>ፖለቲካዊ፥</u> ኢትዮጵያ ከኃያላን መንግሥታት ቁንጮዋ ትሆናለች። ይህ ማለት የቪቶ ድምጽ ይኖራታል፤ ክርስቲያን አገር ስለሆነች በዚህ ድምጽ እየታገዘች ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ነገሮች እንዲወገዱ ታደርጋለች። ይህ ኃይለኛ ተጽዕኖ አፍሪካን ብቻ ሳይሆን የዓለምን መልክም ይቀይራል። አፍሪካውያንማ የኢትዮጵያን መነሣት ተቀምጠው እየተጠባበቁ ናቸው።

መንግሥትም ክርስቲያን መንግሥት ይሆንና ፓርላማው በጸሎት ይከፈታል፤ ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት በጀታም ትሆናለች። የፖለቲካው ሥርዓት የተረጋጋ ይሆናል። የፓርቲዎች ሽኩቻ አይኖርም፤ የሕዝቡን አብላጫ ድምጽ የሚቀዳጀው አንድ የክርስቲያን ፓርቲ የበላይ ሆኖ

ይመራል። ይህ አገዛዝ የተወደደ ስለሆነ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ የመምራት ሥልጣን ይሰጠው ይሆናል። ሰይጣን በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም የመሰልጠን ዕድል አይኖረውም።

የዓለም ታላላቅ ሰዎች ሞታቸውንና መቃብራቸውን እዚህ ለማድረግ ዜግነታቸውን ወደ ኢትዮጵያዊነት ይለውጣሉ። ኢትዮጵያዊ ዜግነትና ኢትዮጵያዊ ፓስፖርት ሞገስ ያለውና የተከበረ ይሆናል።

ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ስትሰግድ የእግዚአብሔር ጠላቶች ፊርተው አፈር ይልሳሉ፤ ዓለምም ኢትዮጵያን ተከትላ የእግዚአብሔር ተገዢ ትሆናለች። ይህንን ጀማሪዋ ኢትዮጵያ ስለምትሆን ታሳቢ ጽድቅ ይያዝላታል።

<u>ኢኮኖሚያዊ / ኢኮሎጂያዊ ብልጥግና፤</u> ኢትዮጵያ እጅግ የናጠጠች ባለጠጋ ትሆናለች። የሃብቷ ብዛት የማይሰፈር ስለሚሆን ክብሯም ሃብቷን ስለሚከተል የዓለም ዘውድ ትሆናለች። ልመና ቋንቋውም የማይታወቅ ይሆናል።

የኢትዮጵያ አየርና አፈር የተለየ ይሆናል። በሽታ የሚባል ነገር ከምድሪቱ ስለሚነቀል የመታከሚያ ተቋማት የማምለኪያ ቦታና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ኮሌጆች ይሆናሉ። አገሪቱ ከበሽታ ስለምትጸዳ አየሯን ለመተንፈስና አፈሯን ለመውሰድ የዓለም ሰዎች ነጭ ጥቁር ቢጫ ሁሉም ይረባረቡባታል፤ ከአራቱም ማዕዘናት መጥተው ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖርና ለመሞት ወረፋው መጨረሻ አይኖረውም፤ ብዛቱም ከቁጥር ይበዛል።

መሬቷ የእህል ምርት ለመስጠት መታረስ እንኳ የለበትም። ልክ እነ አዳም ሳይወጡ እንደነበረችው እንደ ዔድን ገነት ትሆናለች። እህል በእንስሳ እንኳ እስከማይበላ ድረስ ተንቆ መሬት ላይ ይዝረከረካል። ፍሬዋ በዓለም ዙሪያ ክቡርና ተፈላጊ ይሆናል። ከሃብቷ የተነሣ የሕዝቡ አማካይ ገቢ ይህ ነው ብሎ ለመተመን እንኳ አይቻልም።

ኢትዮጵያ ወይስ ዩቶፒያ?

እንግዲህ እንዲህ ያለችውን ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ እንበላት? ወይስ ዩቶፒያ? ዩቶፒያ ሁሉም ነገር ፍጹም ትክክል፥ ምንም እንከን የሌለበት ቦታ ማለት ነው። ዩቶፒያን በመጀመሪያ የተጠቀመው ሰር ቶማስ ሞር የተባለ እንግሊዛዊ ጸሐፊ ሲሆን በምናቡ የፈጠራት አንዲት ደሴት ስም ነው። የፖለቲካውና የመንግሥቱ፥ የሕጉና የማኅበራዊው፥ የሥጋዊውና የአእምሮአዊው ሁሉ ሁኔታ የተሟላና የተመቻቸ ምናባዊ ስፍራ ነው ዩቶፒያ። ቃሉ የግሪክ ቃል ሲሆን ኡ እና ቶፖስ ከሚሉ ሁለት ቃላት የተሠራ ነው። ቶፖስ ስፍራ ማለት ሲሆን ኡ ደግሞ አፍራሽ ቃል ነው። ሁለቱ ቃላት አንድ ላይ ሲሆኑ (ኡ ቶፖስ) የሌለ ስፍራ እንደማለት ነው። እንዲያ ያለ ስፍራ የሚመኙት እንጂ በምድር ሊኖር እንደማይችል ለማመልከት ነው ሰያሜው የተመረጠው።

ኢትዮጵያ ክርስቶስ ሳይመጣ በፊት ከላይ ተንባዮቹ ያሳዩንን አገር ከሆነች ዩቶፒያ የሚለው ቃል ኢትዮጵያ በሚለው እንደሚለወጥና፥ 'ዩቶፒያ የኢትዮጵያ ትንቢት ነው ለካስ?!' እንደሚባል መገመት ይቻላል።

ተርታሪ፥ ጠርጣሪ፥ በርባሪ

ከላይ የተነበቡት ነገሮች በተለያዩ ሰዎች ዘንድ እንደ ተለያዩ ነገሮች ሊወሰዱ ይችላሉ። የሌሎቹን፥ የራሴንም ልናገር።

1. አንዳንዶች እነዚህን 'ትንቢቶች' እንደ እግዚአብሔር ቃልና፥ ከተጻፈው ቃሉ ጋር እኩያ ሥልጣን እንዳለው መለኮታዊ ትንቢት አድርገው የሚወስዱት አሉ። የተጻፈው ትንቢት ፍጻሜ ነው ብለው የሚተነትኑም አሉ። እነዚህ ተርታሪዎች ደርዳሪዎች ናቸው። አንዲት ደብዛዛ ገጽ ካገኙ በእርሳስ አድምቀው በፎቶ ኮፒ የሚያባዙ ዓይነት ሰዎች ናቸው። ይህ ጉልህ ስሕተት ነው። እግዚአብሔር በእጃችን እንዲሆን የፈቀደው የተጻፈ ቃሉ እኩያ ሥልጣን የሌለው፥ ሌሎቹ ሁሉ ቃሉች የሚፈተሹበት መፈተሺያ፥ መበርበሪያ ነው።

2. ጠርጣሪዎች ደግሞ አሉ። እነዚህ 'ትንቢቶች' ለአንዳንዶች የሰዎች አስተያየትና አመለካከት ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። ልክ ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ፤ ቸኩለን መፍረድ የለብንም። በጊዜ ውስጥ የሚረጋገጡ ስለሚሆኑ መታገስም ተገቢ ነው። ደግሞም አዎንታዊ ስለሆኑ ምንም ጉዳት የለባቸውም፤ ጸለምተኛ መሆን ጥሩ አይደለም።' የሚል እይታ አላቸው።

ከነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ ተንሳፋፊዎችና ነፋስ ወደሚወስዳቸው የሚሄዱ ናቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ ለመናገርና ድምጻቸውን ለማሰማት ይፍሩ እንጂ የተንባዮቹ ቋንቋ የስላቅ ተስፋውም ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንደሆነ የገባቸው ናቸው። ግን መጋፈጥ አይወድዱም። ኮስተር ብለው ቃሉን መርምረው ለመረመሩትና ላወቁት መገዛትንም አይለማመዱም።

3. ሦስተኞቹ በርባሪዎችና መርማሪዎች ናቸው። የሚሰሙትን እንደ ቤርያ ሰዎች (ሐዋ. 17፥11)፥ 'ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን?' እያሉ መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ የሚቀበሉ ናቸው። መመርመሪያው ቃሉ በእጃችን ስላለ ትምህርቶችንና ስብከቶችን፥ ወይም ትንቢተኞች የሚሉት ነገር እንደ ቃሉ ከሆነ ማየት እንችላለን። ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበልና ለመንቀፍ ቃሉን መሠረት የሚያደርጉት ናቸው በርባሪዎችና መርማሪዎች።

በኔ አተያይ እነዚህ የኢትዮጵኝነት 'ትንቢቶች' ፍላጎትና ጉጉት፥ የአገር ፍቅር ስሜት፥ እንዲሁም በግማሽ ከፍለ ዘመን ውስጥ የተጠራቀሙ ብዙ ተንባዮች አርግዘውና አምጠው የወለዷቸው ተምኔታዊ ምኞቶች ናቸው። በምሳ. 31፥7፥ *ይጠጣ፤ ድህነቱንም ይርሳ፤ ጉሰቁልናውንም ከእንግዲህ ወዲህ ሊያስብ።* ተብሎ እንደተጻፈው መከራን የሚያስረሳ ብርቱ መጠጥ ነው። ለዚህም ነው ኢትዮጵኝነት ከታማኝ ዘግኑትና ከአገር መውደድ ስሜት ወደ ብሔራዊ ኩራት፥ ከብሔራዊ ኩራት ወደ አገራዊ ስካር፥ ከአገራዊ ስካር ወደ አገር ጣዖትነት ያለፈ ሆኖአል ያልኩት። ብርቱ መጠጥ ጉስቁልናን ያስረሳል እንጂ አይቀርፍም። ያዘናጋል እንጂ አያነቃም። ያደነዝዛል እንጂ አያበረታም። የድለላ ትንቢት 'ዶሮ ማታ' እየተባልን እንደምንጠጣው ኮሶ

ያህል እንኳ የሚያሸር ቢሆን በተጠጣ መልካም ነበር። በተስፋ ችግራችን በተረሳ ነበር። ችግሩ እጥፍ ነው፤ የማያሸር ኮሶ እየተጠጣ ነው፤ ማታ ደግሞ ዶሮው የለም።

ፍላጎትና ጉጉት ትንቢት ሊወልድ ይችላል። ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለሁ አንድ ዓመት ከአንድ ጓደኛዬ ጋር የጠረጴዛ (ቴኒስ) ኳስ *መጫወት* እንደ ሱስ ሆኖብን ነበር። የጠረጴዛ ኳስ *መጫወቻ* ክፍሉ የጂያግራፊ *መማሪያ* ክፍላችን አጠገብ ነው። ጂያግራፊ ክፍል ሆነን እየተማርን ልጆች ቴኒስ ሲጫወቱ፥ ኳሷ ጠረጴዛውን ቋ ቋ ስታደርግ ይሰማናል። እንደጨረስን ቶሎ ወጥተን ወደ ቴኒስ ክፍል እንሄዳለን። በሩ ዝግ ነው። ወደ በሩ እስክንመጣ ሁሉ ድምጽ ይሰማናል። ጆሮአችንን እበር ላይ ስንተክል ድምጽ ይጠፋብናል። ማመን ተስኖን አንዳችን በር እየጠበቅን ሌላችን በጀርባ ሄደን በመስኮት እናያለን። ማንም የሚጫወት የለም። በመስኮት ወጥተው ሄዱ እንዳንል መስኮቱ ለብርሃን እንጂ ለሰው መውጫ የማይሆን ነው። ድምጹ ከየት መጣ? አንዳንዴ ከመጻጻታችን የተነሣ የምንሞኘውን 'ድምጽ' እንሰማለን። የስነ ልቡና ጠበብት ስለዚህ መሳይ ነገሮች የተለያዩ ስሞች አሏቸው። ኢትዮጵኞች ስለ ኢትዮጵያ ከመጻጻታቸው የተነሣ የሚሰሟቸው ድምጾች ቢኖሩ አያስገርምም። ተሰምቷቸው ትንቢት ተናግረው ሲያፋጥጧቸው ስሜታቸው መሆኑን የተናገሩ ሰዎችን አውቃለሁ።

ይህን ማለት ሊያስነቅፍ ይችላል። እኒህን ያህል (አንዳንዶቹ ጉምቱ የሆኑ) አገልጋዮች ተቀበልን ያሉትን ትንቢት ማጥላላት ሊያስነቅፍ ብቻ ሳይሆን ሊያስኮንንም ይችላል። በጊዜ ውስጥ የሚታዩ ብቻ ሳይሆኑ ውሸትነታቸውን ለመግለጥ ጊዜ መጠበቅ የማያስፈልጋቸው ነገሮች ፈጥጠው እየታዩ የይሉኝታ ዝምታ ወግ አይደለም። መስማትና ማንበብ ያለብን የማይገሰሰውን ቃሉን እንጂ የራሳችንንም ሆነ የሌሎችን ስሜትና ራእይ አይደለም። ማስጠንቀቅ አንዳንዴ ጊዜው ያለፈበት ሊመስልም፥ ሊሆንም ይችላል። ቢመስልም ወይም ቢሆንም እንኳ፥ ጅብ ከሄደ እንደጮኸ ውሻ ቢኮንም እንኳ፥ ጅቡን አርቆ ለማባረር ወይም ከሌላ ጅብ ለማስጠንቀቅ ይቻል ይሆናል። ወይም ማን ያውቃል? የሳተውን ለመመለስ ይቻል ይሆናል።

ነበዝ፥ ስተናል! የተንባዮቹን ትንቢቶች አጢናችሁ ከሆነ ትኩረታቸው ምድራዊና ቁሳዊ፥ ኢኮኖሚያዊና ንዋያዊ፥ ፖለቲካዊና ሥልጣናዊ ነው። ለሥጋዊ ሰው የሚመቹ ቃላት ናቸው። አንዳንዶቹ ከስማቸው በፊት ያለው ማዕረግና ከስማቸው በታች ያለው ቢሮ የሚያመለክተው ነገር እያለም እንኳ፥ 'ክርስቲያኖች ናቸው ወይ?' የሚያሰኙ ናቸው።

ዩኒቨርሲቲ ሳለሁ ረዘነ ሀብተ ማርያም (በኋላ ዶ/ር) የሚባል የሳይኮሎጂ ፕሮፌሰር ነበረን። በሆነውም ባልሆነውም ክርስቲያኖችን ማንቋሸሽ፥ ማጥላላት፥ መዘበት ያስደስተዋል። በክፍሉ ክርስቲያኖች እንዳለን ብቻ ሳይሆን አንዳንዶቻችንን በስምም ያውቀናል። አንዳንዴ ቀጥተኛ ሒላማው ነን። በኢየሱስ የፌዝ ቃላት እየወረወረ ይዘብታል። ዘመኑ የደርግና የኮሚኒዝም ስለሆነ ፌዙን እንደ አገልግሎት ሳይቆጥረው አልቀረም። በዓመቱ መጨረሻ የግምገማ ፎርም በሚሞላበት ቀን ሁሌም ያደርጋል እንደሚባለው፥ 'እዚህ ክፍል ውስጥ ሳስተምር ያስቆጣኋችሁና ያስቀየምኳችሁ ሰዎች ብትኖሩ ይቅርታ። በተለይ በሃይማኖታችሁ የቀለድኩ ከመሰላችሁ እኔም እራሴ ሃይማኖት አለኝ፤ ልቀልድባችሁ አይደለም፤ እና ይቅርታ።' አለ። ቃል በቃልም ባይሆን ይህን የሚመስል ነገር ነው የተናገረው።

እኔም እንደ ፕሮፌሰር ረዘነ ይህን ስጨርስ ጽሑፌ ላስቆጣቸው የቡልኮ ይቅርታ ለመጠየቅ ሳይሆን ያደረግሁበትን ግፊት ቀደም ሲል ብገልጽም እንደገና ላስረዳ ልሞክር። በመግቢያዬ ላይ፥ 'አገራዊ ስሜትንና ሕዝባዊ ትንቢቶችን ከቃሉ እኩል ለሚያዩ ሰዎች ይህ ጽሑፍ ሊያስቆጣ ይችል ይሆናል። ለማስቆጣት ስል አልጽፍም፤ ስለሚያስቆጣ ደግሞ ከመጻፍ አላፈገፍግም። ላለማስቆጣት ሲባል ዝም ማለት እውነትን የማቀጨጭም፥ ስሕተትን የማፋፋትም ድርብ ጥፋት ነው።' በማለት ጽፌ ነበር። ይህ ጽሑፍ የሚያስቆጣቸው ሰዎች ይኖራሉ። ተናጋሪዎቹን ሊያስቆጣ ይችላል። የተናጋሪዎቹን ታዳሚዎች ሊያስቆጣ ይችላል። የቪድዮ አዘጋጆቹንና በአጠቃላይ ኢትዮጵኞችን ሊያስቆጣ ይችላል።

ለማስቆጣት ብዬ ባልጽፍም ቁጣ መልካም ነው። ቁጣ ገንቢ ገንቢ ገጽታ እንዳለው ስለማውቅ ነው መልካም ነው የምለው። መጽሐፍ ቅዱስ ጨርሶ እንዳንቆጣ ሳይሆን ትክክለኛ ያልሆነ ቁጣን እንዳንቆጣ ነው የሚያስተምረን። ቪድዮውን ሳይ እኔም ተቆጥቻለሁ፤ ስለዚህ ነው ይህን የጻፍኩት። ትክክለኛ ቁጣን ለማወቅ ቁጣ ወደ ሕይወታችን ሲመጣ፥ 'ለምን ተቆጣሁ? ያስቆጣኝ የኔ መብት ስለተነካ ነው ወይስ አይደለም? የእግዚአብሔር ቃልና ሥርዓት ተጥሷል?' ብለን እንጠይቅ። የዚህ ጽሑፍ ወይም ትምህርት አንባቢ ተቆጥቶ ከዚህ የተሻለ ሊጽፍ እንዲችል፥ እንዲያስተምርም እመኛለሁ።

የዚህ ጽሑፍ ወይም ትምህርት ዒላማ ሰዎቹ አይደሉም። ዒላማዬ የተላለፈው ኢትዮጵኛ ትምህርት ነው። ኢትዮጵኝነት ሃይማኖት እየሆነ ነው። የአገር ጣዖት አምልኮት ነው። ጣዖት በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነገር ነው። ኢትዮጵኝነት አሁን አላደገና እውነተኛ ገጽታው ግጥጥ ብሎ አልታየ ይሆናል። በመግቢያው ገጽ ላይ እንደተቀመጡት ሰዎች የሕፃናት ስዕል[23] የሚስብና የሚማርክ፥ ጨዋና ንጹሕ ሊመስል ይችል ይሆናል።

እኔ እንደምረዳው ከላይ ያየናቸውም ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵኞች ያስተላለፉት የትንቢት ቃል በእግዚአብሔር ስም የተናገሩት ከሆነ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሁሉ ሊወሰድ የተገባው ነው ማለት ነው። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በእውነት እግዚአብሔር ዓለምን የሚጎበኝባቸው ብቸኛና የመጨረሻ አገርና ሕዝብ ናቸው ካሉ ቃላቸውን በተጻፈው ቃሉ ለመፈተን መፍቀድ አለባቸው። ካልሆነ ደግሞ በመጀመሪያም መናገር የለባቸውም፤ ወይም ኢትዮጵኝነት ስሕተት ነውና በስሕተት ያስተማሯቸውን ነገሮች ለማረምና ያሳቷቸውን ሰዎች ይቅርታ ለመጠየቅ መድፈር አለባቸው።

[23] ፎቶዎቹ የጀርመኑ ሂትለር፥ የሩስያው እስታሊን፥ የጣሊያኑ ሙሶሊኒ፥ እና የካምቦዲያው ፖልፖት ናቸው።

የማስታወሻ ምንጮች

Budge, E. A. Wallis, *The Queen of Sheba and Her Only Son Menyelek*, Oxford University Press, London, 1932.

Skowera, Jennifer; Holy Zion! A Study of Ethiopianism in Rastafarianism with a Focus on the Concept Of Ethiopia as Zion; online version, http://www.uvm.edu/~debate/dreadlibrary/skowera.html

ሀብተማርያም አሰፋ፥ ዶ/ር፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች፤ 1986፤ አዲስ አበባ።

ስሜ ታደሰ፤ ለእውነት እንቁም፤ የሚሊኒየሙ መርዶና ብስራት፤ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት፤ 2004።

በሊና ሰርካ፥ ቄስ፤ የከፍታ ዘመን ለኢትዮጵያ፤ የኡዲዮና የቪድዮ ቃለ ምልልስ። በወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ የምሥራች ድምጽ የተሰናዳ።

ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደኢየሱስ፤ ኢትዮጵያ፥ የዓለሙ መፋረጃ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፥ አዲስ አበባ፥ 2001 (1993 ዓ.ም.)።

ክብረ ነገስት፥ ግእዝና አማርኛ፤ እትምና ትርጉም፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፥ አ አ ዩ፥ አዲስ አበባ፥ መስከረም 1994።

አማረ አለፈ ብሻው፤ *ኢትዮጵያ የሰው ዘር የተገኘባት የእምነትና የሥልጣኔ ምንጭ ናት*፤ St. George Union Printing PLC, Addis Ababa, Ethiopia, 2004።

ከበደ ተሰማ፥ ደጃዝማች፤ የታሪክ ማስታወሻ፥ [illegible]።

ዮናስ ሰይፉ፤ እምነትና ፍርሃት፤ ኢትዮጵያና አስደናቂው ትንቢት፤ 2000።